ምዕራፍ አንድ 5
ትምህርተ ኖሎት /ትምህርተ አበ ነፍስ/ 5
1. መግቢያ 5
1.1. ትምህርተ ኖሎት /አበ ነፍስ/ ምንድን ነው? 5
1.1.1. ትምህርት ምንድን ነው? 5
1.1.2. ኖሎት 6
1.1.3. ትምህርተ ኖሎት ማለት 6
1.2. የትምህርተ ኖሎት ዓላማ 6
1.3. የትምህርተ ኖሎት ጥቅም 7
1.4. የትምህርተ ኖሎት ምንጮች 7
1.5. የትምህርተ ኖሎት ማዕቀፍ 7
1.5.1. ሰው 7
1.5.1.1. በቅድስናና በጽድቅ እንዲኖር:- 8
1.5.1.2. የፍጥረታት ገዥ አስተዳዳሪ እንዲሆን:- 8
1.5.1.3. በህብረት እንዲኖር:- 8
1.5.1.4. በበረከት እንዲኖር: 8
1.5.1.5. በመልካምነት እንዲኖር:- 8
1.5.1.6. ተገዥ ወይም ታማኝ እንዲሆን :- 9
1.5.2. ቤተክርስቲያን 9
1.5.2.1. ሰዋስዋዊ ፍች 9
1.5.2.2. ምስጢራዊ ፍች 10
1.5.3. የቤተክርስቲያን ባሕርያት 11
1.5.3.1. ቤተክርስቲያን አንዲት ናት 11
1.5.3.2. ቤተክርስቲያን ቅድስት ናት፡- 11
1.5.3.3. የቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊት የሁሉና በሁሉ ያለችናት ናት 11
1.5.3.4. ቤተክርስቲያን ሐዋሪያዊት ናት (Apostolic) 12
1.6. የትምህርተ ኖሎት መስራች 12
1.7. የትምህርተ ኖሎት ተግዳሮቶች 12
1.7.1. በመንፈስ መዛል 12
1.7.2. በስነ-መለኮትና በአመክንዮ ላይ ቅይጥ መረዳት መኖር 12

በሰ.ቅ.ዳ.ቅ.ኮሌጅ የትምርተ ኖሎት መማሪያ በመ/ር ጌታባለው (B.Th. MA. Adm)

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

1.7.3. ሉላዊነት 13
1.7.4. ብዝኃ ሃይማኖትና ባህል 13
1.8. የትምህርተ ኖሎት ባሕርያት 13
1.8.1. በመንፈስ ተመሪነት 13
1.8.2. አበ-ነፍሳዊ ጥባቆት 13
1.8.3. ምስጢር ፈጻሚነት 14
1.9. ማጠቃለያ 14
ምዕራፍ ሁለት 15
2. ክህነት፣ካህንና ጥሪው 15
2.1. ካህን ማለት ምን ማለት ነው? 15
2.1.1. የካህን ዋናዋና ተልእኮዎች፡፡ 15
2.1.2. የክህነት አስፈላጊነት፡- 16
2.1.3. ክህነት በዘመነ ሕገ-ልቡና፡- 16
2.1.4. ክህነት በዘመነ ሕገ-ኦሪት 17
2.1.5. የክህነት ተልዕኮ በሕገ-ኦሪት፡- 18
2.1.6. የሕገ- ኦሪት ካህናት የት ያገለግላሉ? 18
2.1.6.3. ቅድስት 21
2.1.6.4. ቅድስተ-ቅዱሳን 24
2.2. ክህነት ሐዲስ ኪዳን 26
2.2.1. ክህነት በሐዲስ ኪዳን 26
2.2.2. የሐዲስ ኪዳን ካህን ለመሆን የሚያስፈልጉ መሥፈርቶች 26
2.2.3. ለክህነት የሚያበቁ ሁኔታዎች 27
2.2.4. የሐዲስ ኪዳን የክህነት ደረጃዎች 28
2.2.5. የሐዲስ ኪዳን ካህናት ተግባር 28
2.2.5.3. ካህን በምእመናን ቤት (በነፍስ ልጆቹ ቤት) 33
2.2.5.4. ካህን በአደባባይ (ሕዝብ በሚሰበሰብበት ስፍራ) 35
2.2.5.5. ካህን በማህበራዊ ሕይወት 36
❖ ካህን ከኃጢአተኞች ጋር 38
2.2.6. መሥዋዕተ ሐዲስ 39
2.2.6.1. መንፈሳዊ መስዋዕቶች 39

በሰ.ሐ.ብ.መ.ኮሌጅ መማሪያ በመ/ር ጌታባለው (B.Th. MA Adm)

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

2.2.6.2. የምስጋና መስዋዕትነት 40
2.2.6.3. አማናዊ መሥዋዕት (ቅዱስ ቁርባን) 40
2.2.7. የካህናት መብትና ግዴታ 40
2.2.7.1. መብት 40
2.2.7.2. ግዴታ 41
2.2.8. ካህናት ከመፈጸም ሊታቀቡባቸው የሚገቡ ጉዳዮች 41
2.2.9. ካህን ከሹመቱ የሚሻርበት ምክንያቶች 41
2.2.9.1. ዲያቆናት ከክህነት የሚሻሩበት ጥፋት (ፍ.ነ አንቀጽ 7) 41
2.2.9.2. ቀሳውስት ከክህነት የሚሻሩበት ጥፋት 41
2.2.9.3. ኤጲስ ቆጶሳት (ፓትርያርክ) ከሹመት የሚሻርበት ምክንያት 43
2.2.10. ካህናት ለአገራዊ ሰላምና አንድነት የሚኖራቸው ሚና 43
2.2.10.1. ካህናት ለአገር ሰላምና አንድነት ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና በአግባቡ ለመወጣት የሚፈጸሙ ጉዳዮች 43
2.3. ማጠቃለያ 43
ምዕራፍ ሦስት 44
3. ኖላዊነት 44
3.1. የኖላዊነት አይነቶች 44
3.1.1. አምላካዊ እረኝነት 44
3.1.2. መልአካዊ እረኝነት 45
3.1.3. ሰበአዊ እረኝነት 45
3.2. መልካም እረኛ 45
3.2.1. የእረኛ ተግባር 45
3.2.1.1. በጎችን ማወቅ 46
3.2.1.2. በጎችን ማሰማራት (መጠበቅ) 47
3.2.1.3. የጠፋውን መፈለግ 47
3.3. መልካም እረኛ ማነው? 48
3.4. የመልካም እረኛ ባሕርያት 48
3.4.1. ለበጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ መስጠት 48
3.4.2. በጎቹን ከፊት ሆኖ ይመራል 49
3.5. እረኛ ያላቸው በጎች 49
3.6. ምንደኛ እረኛ 50

ቅ.ጳ.ል.መ.ኮ.ት.ኖ.መ.ማ.ቤ.በ.መ/ር ጌ.ባ.አ (Bth. MA Adm)

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

3.6.1. ምንደኛ እረኛ ባሕርይ 50
3.7. እረኛ የሌላቸው በጎች (መንጋ) 50
3.7.1. ለሌባ እና ለዱር እንስሳት የተጋለጡ ናቸው፡- 51
3.7.2. ባዘነው ይጠፋሉ ከባድ ችግር ውስጥ ይገባሉ 51
3.8. እረኝነት በብሉይ ኪዳን 51
3.8.1. የብሉይ ኪዳን የኖላዊነት አገልግሎት 53
3.8.2. የብሉይ ኪዳን ኖላውያን አይነቶች 53
3.9. እረኝነት በሐዲስ ኪዳን 55
3.9.1. የሊቀ ኖሎት ኢየሱስ ክርስቶስ ኖሎታዊ አገልግሎት 56
3.9.2. የሐዲስ ኪዳን እረኝት ዓላማ 56
3.10. የኖላውያን ወቀሳዎች 56
3.11. የኖላውያን ዋጋ 57
3.12. ማጠቃለያ 57
3.13. ዋቢ መጻሕፍት 57

በሰ.ቅ.ጳ.መ.ኮ.የት.ኖሎት መማሪያ በመ.ር ጌታባለው (B.Th. MA Adm)

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ምዕራፍ አንድ

ትምህርተ ኖሎት /ትምህርተ አበ ነፍስ/

1. መግቢያ

“ወአንትሙኒ ጽንኡ ከመ እብን መንፈሳዊ ወኩኑ ታቦተ መንፈሳዊ ለክህነት ቅድስት ወንጽህት ከመ ታቅርቡ ወታዕርጉ መስዋዕተ መንፈሳዊ” እናንተ ደግሞ እንደ ሕዋን ድንጋዮች ሆናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መስዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ። (1ኛ ጴጥ፡2፡5) ትምህርተ ኖሎት በብሉይ ኪዳንም ይሁን በሐዲስ ኪዳን ሕዝብን ያገለገለ ቁልፍ ትምህርት ነው። የፍጥረታት ፍጻሜ ከሆነ ጊዜ አንስቶ (አዳም ወደ ገነት ከገባበት ጊዜ አንስቶ) የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ተቋም ኖላዊነት ነው። ቤተክርስቲያን ሕዝቦቿን የምትመራበትና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገቡ የምታደርግበት ቁልፍ መሣሪዋ ኖላዊነት ነው ። ቤተክርስቲያን እና ኖላዊነት ጥርስና ከናፍር ሆነው ለዘመናት ዘልቀዋል ፤ አሁንም እቀጠሉ ነው። ትምህርተ ኖሎት እንደ ቃል መኖርን ስለሚያስተምር የስነ-መለኮት ነው ትምህርት ነው። ጥባቆትንና እንክብካቤን መሠረት ስለሚያደርግ የኖላዊነት ትምህርት ነው። የካህንን እና የምዕመናንን ትስስር የሚጠይቅ በመሆኑ ተግባራዊ የሰነ-መለኮት ትምህርት ነው።

1.1. ትምህርተ ኖሎት /አበ ነፍስ/ ምንድን ነው?

1.1.1. ትምህርት ምንድን ነው?

ትምህርት ማለት አዕምሮን በመጠቀም እግዚአብሔር በጥንተ ተፈጥሮ በህሊናችን ጽላት የሳለውን ወይም በተፈጥሮ የሰጠንን ችሎታ ለማግኘት የሚደረግ ጥረትና ዉጤት ነው። ይህንን ስንል አስቀድሞ ፈጣሪ በተፈጥሮ አዋቂ አድርጎ ስለፈጠረን ማንኛውንም የእውቀት ደረጃ ማወቅ እንችላለን ማለታችን ነው። በተፈጥሮ አዋቂ ሆኖ ያልተፈጠረ ማንኛውም ፍጡር መቼም ቢሆን አዋቂ መሆን አይችልም። ሰው በተፈጥሮው ከመለኮት እስትንፋስ በአፍንጫው የተቀበለ በመሆኑ አዋቂ የመሆን እድል ነገር ግን እንደየጥረቱ ከተሰጠው እውቀት ላይ በጥረቱ ልክ ማወቅ ይችላል። ይህም ማለት ብዙ የጣረ ብዙውን ከውስጡ እንዲያንሰራራ ወይም አንዲጎለብት ማድረግ ይችላል ካልሆነ ግን እንደያዘው ወደ መቃብር ይዞት የወርዳል ማለት ነው። ስለዚህ ትምህርት ከውጪ አዲስ ሐሳብ ለመቀበል የምናደርገው ጥረት ሳይሆን የነበረንን እንዳለን ለመረዳትና እንዲያንሰራራ የሚደረግ ጥረት የምናደርግበት ነው።

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

1.1.2. ኖሎት

ኖሎት፡- ኖሎት ኖለወ ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ጠበቀ መበቀ ማለት ነው። ኖላዊ ደግሞ ጠባቂ

1.1.3. ትምህርተ ኖሎት ማለት

አእምሮን እና ህሊና በመጠቀም እግዚአብሔር አስቀድሞ በሕሊናችን ጽላት የጻፈውን ከሃሊነት ፣የመጋቢነት እና የጠባቂነት እውቀት አንዲንሠራራ ጥረት ማድረግ ነው። ነው። ስለዚህ ትምህርተ ኖሎት ማለት የኖላውያን ትምህርት ወይም ደግሞ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የጠነከረ እንዲሆን የሚያስተምሩ ፡የሚንከባከቡ፡የሚመክሩ መንፈሳውያን መምህራን ወይም አባቶች የሚማሩት ትምህርት ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ እረኞች ስለ መንፈሳዊ እረኝነት እወነተኛ እረኛ ክርስቶስን አብነት በማድረግ ከእረኞች እንዲማሩ የሚያደርግ ትምህርት ነው። በሌላ አገላለጽ ደግሞ ትምህርተ ኖሎት ማለት እረኞች የእግዚአብሔር እንደራሴ እና ባላደራ መሆናቸውን ለማወቅ የሚማሩት ትምህርት ማለት ነው።

1.2. የትምህርተ ኖሎት ዓላማ

በማንኛውም ዘመን ቤየትኛውም ቦታ ወንጌል የሚሰበከው ልዑል እግዚአብሔር የሕዝቡን ልቦና ዙፋን መላ ሰውነታቸውን ደግሞ ማደሪያ አድርጎ እንዲያድርበት ለማድረግ ነው። በመሆኑም ደቀ መዛሙርት ይህንን ስልጠና ከጨረሱ በኋላ

- የቤተክርስቲያንን ሥልጣን በሚገባ ያውቃሉ
- የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን ማለት ምን እንደሆነ ይገነዘባሉ
- የኖላዊነት ምንነትና ተግባር በሚገባ ይረዳሉ
- የክህነት ደረጃዎችንና ኃላፊነታቸውን በደንብ ይገነዘባሉ።
- ካህናት ዘመኑን የዋጀ የወንጌል ትምህርት አሰጣጥንና የነፍስ ልጅን አጠበባበቅ ዘዴን በሚገባ ይረዳሉ።
- እግዚአብሔር በካህናት በኩል ለሕዝቡ የሚሰጠውን በረከትና መመሪያ በተብራራ መልኩ ግንዛቤ ይጨብጣሉ።
- የክህነትን ክብርና የካህናትን ኃላፊነትና ግዴታ ይለያሉ።
- የምዕመናንና የካህናት መስተጋብርን ለይተው ማሳየት ይችላሉ
- የካህናትን መብታና ግዴታ ይለያሉ።
- ኖላውያን የእግዚአብሔር እንደራሴ እና ባላደራ መሆናቸውን ይረዳሉ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

1.3. የትምህርተ ኖሎት ጥቅም

ይህ ዓለም ክርስቲያኖች በንጽህና እንዳይኖሩ መሰናክል የሞላበት በመሆኑ መውደቅ መነሳት ይበዘበታል። "ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ፤ ይነሳማል...(ምሳሌ 24፡16) ተብሎ በጠቢቡ እንደተጻፈ መውደቅ መነሳት የጻድቃን አንዱ ጌጣቸው ነው። በመውደቅ መነሳት ውስጥ መተዳደፍና መንጻት ያለ ነው። የኖላዊነት ትምህርት ወድቆ ሲነሱ የሚታጠቡበት ፤ በንጽሕና ሲኖሩ የመንግሥተ ሰማይ ቁልፍ የሚሰጥበት ነው። ይህን ወሳኝ ትምህርት የተማሩ ካህናት ባለ ማወቅ ከመጠየቅ ይድናሉ። ካህን የእግዚአብሔር እንደራሴና ባላደራ በመሆኑ እንዴት አደራዉን መወጣትና እንደ ባለሥልጣን መምራት እንደሚችል ማወቅ ይኖርበታል። በመሆኑም ትምህርተ ኖሎትን መማር በድግዝግዝ ህዝብን ከመምራት እና ከአላዋቂነት ተጠያቂነት ይጠብቃል። በተጨማሪም ምዕመናን ሃማኖትን ተምረው መጽደቂያቸው፣ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን መቀበያቸው ስርዓተ ቤተክርስቲንን መማሪያቸውና መፈጸሚቸው እንዲሁም የተመሩትን መጻህፍት በተግባር መግለጫቸው ነው። ትምህርተ ኖሎት ጠላትም ወዳጅም ዓይኑን የሚጥልበት ትምህርት ነው። ጠላት የቤተክርስቲያን ቀጣይ ህይወት ለማምከን በካህናትና በምዕመናን መካከልያለውን ግንኙነት በተለያየ ምክንያት እንዲሻክር ያደርጋሉ። በዚህ ምክንያት ንስሐ የሚገቡ መልካም ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ቁጥርን ይቀንሳሉ። ወዳጅ ደግሞ ይህንን ግንኙነት እንዲቀጥል ጥረት ያርጋሉ። ስለሆነም ትምህርተ ኖሎትን መማር የቤተክርስቲያን ቀጣይ ዕጣ ፋንታ ላይ መወሰን ሥራ ለመሥራት ወሳኝ ጉዳይ ነው።

1.4. የትምህርተ ኖሎት ምንጮች

ትምህርተ ኖሎት በድንገት የተገኘ ሳይሆን እንደ መሠረተ ሃይማኖት ትምህርት ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን በምንጭነት የሚጠቀም እና በተጨማሪ የሐዋርያት ትምህርት እና ተግባር መነሻው ያደርጋል። ኖላዊነት በየዘመናቱ በእግዚአብሔር ተመርጠው የተነሱ ጠባቂዎችን ሁሉ የሚገልጽ ቃል ነው። እግዚአብሔር ሰዉን የፈጠረዉ በዓላማ ነዉ። ማንኛውም ፍጥረት የክብሩ መግለጫ ነው። "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል" ። (መዝ 19:1) ሰዉ ሲፈጠር በእግዚአብሔር መልክ ሆኖ ስለተፈጠረ የእግዚአብሔርን ሁለተናዊ ማንነት በዉስጡ የያዘ ነው።

1.5. የትምህርተ ኖሎት ማዕቀፍ

1.5.1. ሰው

ሰው በእግዚአብሔር አርዓያና ምሳሌ የተፈጠረ የእግዚአብሔር እንደራሴ እና ባላደራ ሆኖ እንዲኖር የተፈቀደለት ክቡር ፍጡር ነው። ሰው ከሥጋ እና ከነፍስ የተሠራ እና እንደ እግዚአብሔር ዓላማ እንዲኖር መመሪያ የተሠጠው ፍጡር ነው። ከዚህ በመቀጠል በሰው አኗኗር ላይ የእግዚአብሔር ዓላማ ምድነው የሚለውን እናያለን።

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

1.5.1.1. በቅድስናና በጽድቅ እንዲኖር:-

እግዚአብሔር እራሱን የሚገልጠዉ በቅድስና ነዉ:: “እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ”። (ዘሌ.19:2) ቅድስና የእግዚአብሔር የባህሪ መገለጫ በመሆኑ ልጆቹም በዚህ መገለጫነት እንዲኖሩ ይፈልጋል ::ለዚህም ነዉ “ቅዱሳን ሁኑ” የሚለን:: በሐዲስ ኪዳንም ጥሪዉ ለዚሁ ነዉ::”ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናልና”። (1ተሰ. 4:7)ተብሎ ተገልጿል። ጽድቅና ቅድስና በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተገኙ ናቸዉ:: “ለእዉነትም በሚሆን ጽድቅና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረዉን አዲሱን ሰዉ ልበሱት”( ): ሰዉ በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ ክብሩ ከፍ ያለ ነዉ ሰዉ ከመፈጠሩ በፊት ልዩ የሆነ አምላካዊ ከፍጥረታት ሁሉ ሰዉ ብቻ በእግዚአብሔር መልክ መፈጠሩ ከፍ ያለ አጽንኦትና እቅድ በሰዉ ልጅ ላይ እንዳለዉ ይገልጣል

1.5.1.2. የፍጥረታት ገዥ አስተዳዳሪ እንዲሆን:-

እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው”። (ዘፍ.1:28) ይህዉም ጥቅም እንዲያገኝበት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ጽድቅ እንዲፈጽምና ክብሩን እንዲገልጥ ነዉ::

1.5.1.3. በህብረት እንዲኖር:-

ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸዉ:: በእግዚአብሔር እቅድ ወንድ እና ሴት በእግዚአብሔር መልክ በእኩልነት ይሳተፋሉ::1ኛ ዮሐ1፡3

1.5.1.4. በበረከት እንዲኖር:

ሰዉን በእግዚአብሔር የተወደደ በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ አምላክ ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በላይ የተደሰተበት ነው።እግዚአብሔር ሰዉን በበረከት ሞልቶታል:: በቃል ኪዳንም ከእግዚአብሔር ጋር መግባባቱ ከማንኛዉም ፍጥረት እድለኛ እና ሞት በማይገኝበት የዘላለም ሕይወት ተስፋ ቃል ማግኘት እና በንጽህና መኖኖር ይህ ሁሉ የፀጋ ስጦታ ከእግዚአብሔር የተገኘ በረከት ነበር::

1.5.1.5. በመልካምነት እንዲኖር:-

ሰዉ እጅግ መልካም ሆኖ በመፈጠሩ ከሌሎች ፍጥረታት ልዩ ያደርገዋል:: እያንዳንዱ ነገር ሲፈጠር እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ አየ:: በመልኩ የተፈጠረዉን ሰዉ ካየ በኋላ ግን ያደረገዉን ሁሉ ሲያይ እጅግ መልካም ነበር:: በመልካምነቱም እንዲኖር እቅዱ ነበር:: እንግዲህ ሰዉ ማለት በእግዚአብሔር ዓላማ የተፈጠረና በዕቅዱም የሚኖር፣ በድንገት ያልተፈጠረ፣ በዘግመተ ለዉጥም ያልመጣ፣ ራሱ እግዚአብሔር በመልኬ ልፍጠር ብሎ የፈጠረዉና ከሌሎች ፍጥረታት ይልቅ የእግዚአብሔር ጥልቅ ጥበቡ የታከለበት

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ከአስደናቂ ዕቅድ ጋር ወደዚህ ዓለም ያስገባዉ ፍጥረቱ ነዉ:: ስለሆነም በዚህ ፍጥረቱ ለክ እንዲኖር ግድ ይለዋል፡፡

1.5.1.6. ተገዥ ወይም ታማኝ እንዲሆን :-

እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረታት እንዲያውቁት ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ለራሱ ጥቅም ሳይሆን ፍጥረታት እርሱን ካለማወቃቸው የተነሳ እንደሚጠፉ ስለሚያውቅ ነው፡፡ ሰውም ፍጡር ስለሆነ ፈጣሪውን ማወቅ እና የሚገባውን ትእዛዛትን የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡ ይህም ለራሱ ጥቅም ስለሆነ ነው እንጂ እግዚአብሔር የክብር ጉድለት ኖሮበት አይደለም፡፡ ስለዚህ ሰው እግዚአብሔርን ያስታውስ ዘንድ ትእዛዛትን አስቀምጦለታል፡፡ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካም እና ክፉውን ከሚያሳውቀውን ዛፍ አትብላ ከእርሷ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ>>ዘፍ2;16-17 ይህን ትእዛዝ በልቦናው ተስሎ ስለተቀመጠ ዘወትር ከአምላኩ ጋር እየተገናኘ እና እያሰበው እንዲኖርና አታድርግ ያለውን በመከልከል አድርግ የተባለውን ደግሞ በመፈጸም የሚኖር ነው፡፡ ከእግዚአብሔር የሚገኙት ማንኛውም ነገሮች ተፍጻሚነት የሚያገኙትም በእነዚህ ትእዛዝ አማካኝነት ነው፡፡

ስለዚህ ይህንን ትእዛዝ ሰዎች በህይወት ለመኖር ይችሉ ዘንድ መፈጸም እንዳለባቸው የእግዚአብሔር እቅዱ ነበር፡፡ አዳም ሞትን የሚያሳውቀውን ዛፍ ሲበላ እንደሚሞትና ላለመሞትም ከህይወት ዛፍ ብቻ እየበላ እንዲኖር በዚህም ዘላለማዊነትን የታወጀለት መሆኑን እንዲረዳ ነው፡፡ ያለ ትእዛዝ መኖር ፈሩን የለቀቀ ህይወት መምራትን ያመጣል እግዚአብሔር ለሰዎች በትእዛዝ እንዲኖሩ ያቀደውም መረን የሆነ ኑሮ እንዳይኖሩ ነው እንጂ አዳም እንዲሞት ወይም ሊፈትነው ስለሚፈልግ አይደለም ::

1.5.2. ቤተክርስቲያን

1.5.2.1. ሰዋስዋዊ ፍች

“ቤተ” የሚለው ቃል የግእዝ ቃል ሲሆን “አደረ” የሚል ፍች አለው፡፡ ክርስቲያን የሚለው ቃል ደግሞ “የክርስቶስ” የሚል ፍች አለው፡፡ ሁለቱን ስናጣምራቸው ማለትም “ቤተክርስቲያን” ማለት የክርስቶስ ማደሪያ የሚል ፍች አለው፡፡ ምዕመናን በጎብረት ሥርዓተ አምልኮአቸውን የሚገልጽበት፣ አንድ ላይ ተሰባስቦ ጸሎት የሚያደርስበት.ምሕረትና ይቅርታን ለማግኘትፈጣሪያቸውን ደጅ የሚጠኑበትና የጌታችንን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ለሚቀበሉበት ቦታ የተሠጠ ሥያሜ ነው፡፡ ይህ ሕንጻ ቤተክርስቲያንን ይመለክታል የሐዋ.ሥራ 20÷28፣1ኛ. ነገ.9÷3፡፡ ይህ በመጸሐፍ ቅዱስ ቤተመቅደስ ተብሎ ይጠራል፡፡ ቤተመቅደስ የሚለው ስያሜ በመጸሐፍ ቅዱስ 548 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡

“ቤተ” የሚለው ቃል ወገንን ሚግልጽ ሲሆን “ቤተክርስቲያን” የክርስቶስ ወገን፣ አካል እና መሰል ፍች ይኖረዋል፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ የዓለም መድኃኒት መሆኑን የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ቤተክርስቲያን ይባላሉ፡፡የያዕቆብ /የእስራኤል/ ወገን

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

የሆኑ በሙሉ ቤተ እስራኤል እንደሚባሉ በክርስትና የክርስቶስ የሆኑ የክርስቲያን ወገኖችም ቤተ ክርስቶስ፣ ቤተክርስቲያን ይባላሉ። የሐዋ.ሥራ5÷11፣ የሐዋ.ም12÷1፣ 1ኛቆሮ.3÷16፣ ዮሐ.14÷23፣ የሐዋ.ሥራ.9÷3።የክርስቲያኖች ጉባኤ፣የክርስቲያኖች ሰብሰባ /አንድነት/ ቤተክርስቲያን ይባላል። መጽሓፍ እንዲል ሮሜ.16÷1፣1ኛ.ጴጥ.5÷13። ቤተክርስቲያን የሚለውን ስያሜ በጌታ አማካኝነት በወንጌል የተሰጠ ነው። በማቴ.18÷17 "እነርሱንም ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት ቤተክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔ እንደ ቀራጭ ይሁንልህ" ቤተክርስቲያን የሚለው ስያሜ በመጸሐፍ ቅዱስ ውስጥ 328 ጊዜ ተጠቅሷል። የቤተክርስቲያን የሚለውን ስያሜ የተለያዩ መናፍቃን በዚህ ስም እየተጠቀሙ ስላስቸገሩ እውነተኛይቱን ለመለየት እንዲችል አባቶች በኒቅያ፣ በቆስጠንጥንየ፣ በኤፌሶን፣ ጉባኤዎች በተላለፈው የሃይማኖት ቀኖና መሠረት በመነሳት የተለያዩ ቅጽል ስሞች ለቤተክርስቲያን ተሰጥቷታል።

1.5.2.2. ምስጢራዊ ፍች

ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን የአምልኮ ማዕከል አድርገው ህብረት ያደረጉ የቅዱሳን መላእክት፣ የቅዱሳን አባቶችና እናቶች እንዱም በምድር የሚኖሩ ሰዎች ስብስብ ነው። ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የተገኘው "ኤክልሲያ" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ማኅበር ፣ጉባኤ አንድነት ማለት ነው።

- ቤተክርስቲያን የቅዱሳን መላእክት ኅብረት አንድነት
- ቤተክርስቲያን የቅዱሳን ኅብረት አንድነት ማለት ነው። 1ኛቆሮ 1÷2
- ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤት ናት። /ማር- 11:17 ግብ.ሓዋ33:1። ኢሳ ፶፮፡፯። መዝ.133፡2/
- ቤተ ክርስቲያን የስግደት ቤት ናት መዝ:28፡2። 5፡7/
- ቤተ ክርስቲያን ንስሐ ማቅረቢያ የኃጢኣት ስርየት መቀበያ ናት። /ሉቃ 18:9-14/
- ቤተ ክርስቲያን የመስዋእት ቤት፣ የቁርባን ቤት ናት፣ ክርስቲያን ምእመናን መሥዋእት ያቀርቡባታል፣ ቆርባን ይቆርቡባታልና።
- ቤተ ክርሰቲያን የንጽህና እና የቅድስና ቤት ናት፤ ንጹህና ቅዱስ ሁነው ነው የሚገቡባት፤ (/ዘጸኣት 29:44/
- ምእመናን የመንፈስ ንጽህና እና ቅድስና ያገኙበታል።
- ቤተ ክርስቲያን የእግዚኣብሔር ቤት ናት /መዝ. 121፡ መክ.5፡1ን ተመልከቱ/

ስሙ ይጠራበታል፣ እግዚኣብሔር ያድርበታል ተኣምራቱን ያሳይበታልና፤

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

- ቤተ ክርስቲያን የእግዚኣሔር መገናኛ ናት፣ ክርስቲያን ምእመናን ከእግዚኣብሔር ጋር ይገናኙባታል /ዘጸ፡ 29፡42-43/

- ቤተ ክርስቲያን የበረከት ቤት ናት፣ እግዚኣብሔር ሕዝቡን ይባርክባታልና /ዘጸ፡ 20፡ 24/ ቤተ ክርስቲያን በሰማይ ያለች የቅድስት ኢየሩሳሌም ምሳሌ ናት:: /ራእ:21:2፤ ቀ:10-27፡: ዘጸ፡25፡40፤ ዕብ፡ 8:5፡/ ጥቅስ ከመጽሐፈ ሰዓታት: ቤተ ክርስቲያንስ ትትሜስል በጽርሐ ኣርያም ዘላዕለ" ማለት "ቤተ ክርስቲያን ግን በላይኛው ጽርሐ ኣርያም ትመስላለች፤" እንዳለ፤ መጽሐፈ ሰዓታት::

1.5.3. የቤተክርስቲያን ባሕርያት

ቤተክርስቲያን ከሁሉ በላይ ልቃ የምትገለጽባቸው፣ ከዓለም ማኅበራት የተለየችባቸው ፍጹም ማንነቷን የሚገልጹ ባሕርያት አሏት እነዚህን ባህርያት በዝርዝር እንመልከታቸው።

1.5.3.1. ቤተክርስቲያን አንዲት ናት

ቤተክርስቲያን በወርቅ በአፈር በከተማ በገጠር ከሀገር ውጭ ከሀገር ውስጥ ብትሠራም ክብሯ አንድ ነው።ምዕመናንም እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ምዕመናንም ሃይማኖታቸው ይመሰክሩባታል።የአንድ የክርስቶስ አካል ናት።ሮሜ 12÷4-5፣ 1ኛቆሮ.12÷12-27፣ ኤፌ.4÷4-5 ቤተክርስቲያን መሥራቿ እና ሠሪዋ አንድ ስለሆነ፣ዓላማዋ አንድ ስለሆነና ኅብረቷ አንድ ከመሆኑ የተነሣ ቤተክርስቲያን አንዲት ናት።

1.5.3.2. ቤተክርስቲያን ቅድስት ናት፡-

ቤተክርስቲያንን ቅዱስ እግዚኣብሔር መሥረቷል ። ክርስቶስ በቅዱስ ደሙ ሠርቷታል፣አንጽቷታል፣ቀድሷታል ስለዚህ ክርስቶስ ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ አካሉ ቤተክርሥቲያንም ቅድስት ናት ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው “ባሎች ሆይ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ በውኃ መታጠብ ከቃሉ ጋራ አንጽቶ እንደቀደሳት ስለ እርሷ እራሱን አሳልፎ ሰጠ” ኤፌ.5÷26፣ የሐዋ.20÷28። ቅድስና የባሕርዩ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናት 1ኛ.ቆሮ.3÷10። ቤተክርስቲያን ቅድስት በመሆኗ መንፈስ ቅዱስ ተከታዮቿን ይቀደሳቸዋል። ጠቅለል ባለ አነጋገር መሥራቿ፣ የተመሠረተችበት እና የተመሠረተችላቸው ቅድስና አንጻር ቤተክርስቲን ቅድስት ናት።

1.5.3.3. የቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊት የሁሉና በሁሉ ያለችናት ናት

ቤተክርስቲያን በቦታ በዘርና በቋንቋ አትከፋፈልም አትወሰነም ወይም የእነገሌ ናት የእነገሌ አይደለችም አትባልም።ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በክርስቶስ ደም ነው። ክርስቶስ የተሰቀለው ለዓለም ሁሉ ድኅነት ነው ክርስቶስ ለሁሉም ነው የሞተው። ገላ.3÷25-28፣ቆላ.3÷11፣ማቴ.28÷19:: የቤተክርስቲያን አባላት በየትኛውም ቦታ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ይገኛሉ በመሆኑም ጎብረታቸው በዜግነት፣በዘር፣በቋቋ፣በስልጣን ደረጃ እና በመልክዓ ምድር የሚወሰን አይደለም በአምልኮም አንዲት ናት።

1.5.3.4. ቤተክርስቲያን ሐዋሪያዊት ናት (Apostolic)

ቤተክርስቲያን ሐዋሪያዊት ናት የተባለችው ፣የሐዋሪያትን እምነት፣ትምህርትና ትውፊትን ተቀብላ የምታስተምር ስለሆነች ነው። 1ኛ. ዮሐ.1÷1-3፣ማቴ.10÷18፣ሉቃ. 22÷30።

- ተከታዮቿም የሐዋርያትን አስተምህሮ አምነው ተቀብለው በቅዱሳን ሐዋርያት እምነት የሚጓዙ በመሆናቸው።
- አሠረ ክህነቷ ከሐዋርት ጀምሮ ያልተቋረጠ በመሆኑ ሐዋርያዊት ትባላለች
- አሠራሯ አስተማሪ መሥካሪ በመሆኑ ሐዋርያዊት ትባላለች።

1.6. የትምህርተ ኖሎት መስራች

እግዚአብሔር 22 ስነ-ፍጥረታትን ሲፈጥር ሃያዎቹ ለአንክሮና ለተዘክሮ ሲሆን ሁለቱ ፍጥረታት ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ነው። እነዚህ ሁለት ፍጥረታት (ሰውና መላእክት) በእግዚአብሔር ፊት መስዋዕትን የሚያቀርቡ ናቸው። የኖላዊነት ሥራ እነዚህ ፍጥረታት ከተፈጠሩበት ጊዜ የጀመረ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። በየዘመናቱ የኖላዊነት ሥራ ባሕሪው የተለያየ ቢሆን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ገነትን እንዲጠብቃትና እንዲንከባከባት ትዕዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የተጀመረ መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

1.7. የትምህርተ ኖሎት ተግዳሮቶች

ትምህርተ ኖሎት ተግባራዊ ስነ-መለኮት በመሆኑ ከውስጥም ከውጭም ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች አሉበት። ሁሉንም ተግዳሮቶች ለመግለጽ የጊዜና ሁኔታ ገደብ ስላለብን ከዚህ በታች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ እንሞክራለን።

1.7.1. በመንፈስ መዛል

መንፈሳዊ ሥራ የሚሠራው በተንቀለቀል መንፈስ እንጂ በዝለት ውስጥ ሆኖ አይደለም። ለመንፈሳዊ ነገር ተነሳሽነት መላሸቅ ምክንያት የሆነው ቁሳዊነት በአገልጋዮች ላይ ሲነግስ የመንፈስ መዛል ይከሰታል። በበዚህ መልክ ሆኖ ስለ ትምህርተ ኖሎት ማሰብ አዳጋች ነው። (ማቴ 8፡22) ትውልዱ ለቁስ የሚያደርገውን ተነሳሽነት ለመንፈሳዊ ሥራ ቢጠቀምበት እጅግ መልካም ነበር። ነገር ግን አይደልም ትውልዱ በክህነት ዓለም ያለን ህዝቡ አደራየ ነው ብሎ መነሳሳት ላይ ድክመት ይታያል፡ ፡ ይህ መንፈሳዊ ዝለት የትምህርተ ኖሎት አንደኛው ተግዳሮት ነው።

1.7.2. በስነ-መለኮትና በአመክንዮ ላይ ቅይጥ መረዳት መኖር

ስነ-መለኮት እግዚአብሔርን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን ያጠቃልላል። ይህም ያለ አመክንዮ ማብራሪያ በእምነት ብቻ የሚኖሩት ነው። በዘመናችን ይህንን ኑሮ በምክንያት ለማስረዳት ወይም ለመሞገት መሞከር እየትለመደ መጥቷል። የሃይማኖት ጥያቄ በሁለት መንገድ ይመለሳል። አንደኛው በእምነት ሌላኛው በእውቀት ነው። ነገር ግን በእምነት መመለስ የሚገባንን

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

በእውቀት በእውቀት መመለስ የሚገባንን በእምነት ለመመለስ የምንጥር ባለ ቅይጥ መረዳቶች ስለበዛን ለትምህርተ ኖሎት አዳጋች በር ከፍቷል።

1.7.3. ሉላዊነት

ሉላዊነት መገናኛ ቴክኖሎጂ ማደግና ግንኙነትን ማቅለል ያመጣው ኢኮኖሚያዊ ትሥሥር ፣ነጻ የድንበር ዘለል ንግድና ካፒታል ዝውውር፣የዓለም ሀገሮች በመሠረታዊ ሰው ልጆች መብቶች ዙሪያ በተወሰነ ዓለም አቀፍ ድንጋጌ እና ደንብ መገንባት ነው። ሉላዊነት ከመዋዕለ ነዋይ ባሻገር መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ እጁን እያስገባ መንፈሳዊ እሴቶቻችን ፈራቸውን እንዲለቁ እያደረገ ነው። ሉላዊነትን እንደ ተግዳሮት የወሰደ አንድ ኖላዊ ልጆቹን ከቅይጥ ማንነት ማዳን ይችላል። ስለዚህ ሉላዊነት ሌላኛው ችግራችን መሆኑን ልብ ይሏል።

1.7.4. ብዝኃ ሃይማኖትና ባህል

ሃይማኖትና ባህል የአንድ ማኅበረሰብ የኗኗር ዝየውን የሚቃኙ፣ ህይወቱን በጤናማ መንገድ እንዲመራ የሚረዱ ሁኔታዎች ናቸው። ሐዋርያው ቅዱን ጳውሎስ አንዲት እምነት ብሎ ያስተማረ ቢሆንም አዳዲስ አማኞችን ደግሞ ቀንበር መጫን እንደሌለብን መክሮናል። ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ብዙ ባህልና የአምልኮ ተቋማት ያሉባቸው ሀገሮች ይህንን ለማቻቻል ሲቸገሩ እናያለን። ስለሆነም አንድ ኖላዊ የልጆቹን ባህልና የእምነት ደረጃ ማየት ካልቻለ ትልቅ ተግዳሮት ይሆናል።

1.8. የትምህርተ ኖሎት ባሕርያት

ትምህርተ ኖሎት ከሌሎች ትምህርቶች ለየት የሚልባቸው ሚከተሉት ባሕርያት አሉት።

1.8.1. በመንፈስ ተመሪነት

ትምህርተ ኖሎት ከእምነት እና ከእውቀት በተጨማሪ የመንፈስ ቅዱስን እገዛ ይፈልጋል። ኖላውያን በመንፈስ ቅዱስ እገዛ መሠረት ልጆቻቸውን መጠበቅ ከላቻሉ በዘመኑ እውቀት ብቻ መዳኘት አዳጋች ይሆንባቸዋል። ምክያቱም መንፈስ ቅዱስ ከብሌት የሚያነጻ፣ ከፍርሃት የሚጠነክር ሐይል ነው። በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ ኖላውያን በምድራዊ ምርምር ከሚመሩ መሪዎች የተለየ ጸጋ አላቸው። ለዚህም ከበዐለ ሃምሳ በኋላና በፊት ያለውን የሐዋያት ህይወት ማየት በቂ ማስረጃ ነው።

1.8.2. አበ-ነፍሳዊ ጥባቆት

እግዚአብሔር አምላክ ይህንን ዓለም ፈጥሮ እንዲሁ ሜዳ ላይ አልተወውም። የሚጠብቀው እና የሚያበጃጀው ሰው መድቦለታል። በዚህ ዘመንም ለምንኖር ክርስቲያኖች በቃሉ አማካኝነት የሚያስሩና የሚፈቱ አባቶችን በመስጠት ታድጎናል። “ኢሐደጋ ለምድር እንበለ ካህናት ወዲያቆናት” ምድርን ያለ ካህናትና ዲያቆናት አልተዋትም በማለት እንደተነገረው ካህናት ምድር ለተባለው የሰው ልጅ ጠባቂዎች ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን መለዕክቱ ምዕራፍ 2:11 ላይ “እንዳንዶቹን ሐዋርያት ፣ሌሎችን ነቢያት

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ሌሎችንም እረኞችና አስተማሪዎች አድርጎ ሰጠ" በማለት ለቤተክርስቲያን አበ ነፍሳዊ ጥባቆትና አስተምህሮ የተሰጠ መሆኑን ገልፆልናል።

1.8.3. ምስጢር ፈጻሚነት

ትምህርተ ኖሎት ከማስተማርና በመልካም መንገድ ከማሰማራት ባሻገር ክህነታዊ ምስጢራትን ይፈጽማል። ምስጢር ማለት የኔ ለምትለው እና ለመረጥከው የምትነግረው እንዲሁ በየሜዳው የማይዘራ ማለት ነው። ክህነትም ለተመረጡና ለተለዩ ሰዎች እግዚአብሔር የሰጠው ድንቅ ስልጣን ነው። ካህናት በዚህ ስልጣን አማካኝነት ያስራሉ ይፈታሉ። ከበደል ማሰሪያ ነጻ ያወጣሉ። ምስጢር ማለት በሚታይ ነገር የማይታይ ጸጋን ማግኘት ማለት ነው። ምስጢር ፈጻሚነት ስንል በሚታይ ካህን የማይታይ እግዚአብሔርን ማየት መቻል ማለት ነው፡

1.9. ማጠቃለያ

ትምህርተ ኖሎት ጠላትም ወዳጅም የሚመለከተው ትምህርት ነው። የእግዚአብሔርና የህዝቡን ግንኙነት ለመቁረጥ የትምህርተ ኖሎትን ቅቡልነት ማመናመን ለመቀጠል ደግሞ ማጠናከር ግድ ነው። ስለዚህ ጠላት ትምህርተ ኖሎትን ለማቀዛቀዝ ይሠራል። ወዳጅ ደግሞ ከዚህ በላይ የካህናትና የምዕመናን ትስስር እንዲጎለብት ይሠራል።"በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው ሐሳቡም በሰማይና ምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው"። ኤፌ ፡፲ እንዲል መጽሐፍ ኖላውያን የዚህ የመጠቅለል ሥራ ላይ በመሳተፍ የአንበሳውን ድርሻ ይወጣሉ። ከበረት ወጥታ የጠፋችን በግ በበረት ውስጥ አይደለም የምንፈልጋት። ይልቁንም ከበር ውጪ ወጥተን ፈልግን ወደ በረቷ እንመልሳታለን እንጂ። በመሆኑም ኖላውያን በበረትም ከበረት ውጪ ያሉት በክርስቶስ እንዲታቀፉ የማድረግ ሥራ ይጠበቅባቸዋል።

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ምዕራፍ ሁለት

2. ክህነት፣ካህንና ጥሪው

2.1. ካህን ማለት ምን ማለት ነው?

ካህን ማለት ተክህነ፣ አገለገለ ካለው ከግእዝ የወጣ ቃል ነው፡፡ ፍችውም አገልጋይ ማለት ነው፡፡ ትርጉሙ ይህ ሲሆን አንድ ሰው ስልጣነ ክህነትን ከተቀበለ ጀምሮ ራሱን ለህዝብ የሚያስገዛ የሚያገለግል ማለት ነው፡፡ ካህን የሚሆን ሁሉ የካህን ስራ ምን ሊሆን እንደሚገባ ኃላፊነቱን የቱን ያህል እንደሆነ ማወቅና የካህናትን ታሪክንና ትምህርቱንም ማወቅ የግድ ያስፈልገዋል፡፡ ክህነት ማለት ከሰው ልጆች መካከል በልዩ ጥሪ ተጠርተው ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን መስዋዕት በማቅረብ ለርስቱ የተለየ ወገን እንዲሆን የሚደርግ ኩነት ነው፡፡

2.1.1. የካህን ዋናዋና ተልእኮዎች፡፡

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የተሠራች የክርስቶስ የፀጋው ግምጃ ቤት ስለሆነች ሦስት አደራዎችን ከክርስቶስ ተቀብላለች እነዚህንም፡-

ማስተማር፡- ማሰማት፣ ማሳወቅ፣ ማስረዳት ማለት ነው። ይህ ማለት ሰውየውን ማሳመን ማለት ሲሆን ብዙ ውጣ ውረድን ሊኖረው ይችላል *"እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፡፡"/ማቴ. ፳፰፡፲፱*

መመገብ፡- በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የተገኘውን በረከት ለምዕመናን ማደል ናቸው፡፡ የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ ያልሰሙ ከሰሙ በኃላ ያላወቁ ካወቁ በኋላ ያልተረዱ ከተረዱ በኋላ የሚቀርብ የሚሰጥ ነው/ዮሐ. ፮፡፶፮ ፡፳፩፡፭፡፡

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

መጠበቅ ካህናት ልጆቻቸው በአውሬ እንዳይበሉ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡እነዚህ ሦስት ትእዛዛት መነሻነት ነው ከላይ ማስተማርና መመገብ የቤተክርስቲያን ተልእኮ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

2.1.2. የክህነት አስፈላጊነት፡-

ክህነት መቀበል ለክርስቲያን ሁሉ መለኮታዊ ተዕዛዝ መሆኑን መረዳት ያሻል፡፡ ምክንያቱም ያለ ክህነት የሃጢአት ሥርየት ከእግዚአብሔር ዘንድ አይገኝምና፡፡ ክህነት አገልግሎት ማለት ከሆነ ማን ማንን ያገለግላል?ብለን ስንመለስከት ደግሞ ከሰው ልጆች መካከል የተመረጡ ሰዎች ልዑል እግዚአብሔር ያገለግሉታል፡፡ አገልግሎታቸውም ዘወትር በመካከላቸው እግዚአብሔርነቱ ለማያውቁት ሰዎች ማሳወቅ፣ ሕግና ትዛዙንም ማስተማርን ያጠቃልላል፡፡ አገልጋዮች/ ካህናት/ በሦስቱመ ዘመናት የሰጡትንና እየሰጡ ያለውን አገልግሎታቸውን በአጭሩ እንመልከት፡፡

2.1.3. ክህነት በዘመነ ሕገ-ልቡና፡-

ሕገ-ልቡና ማለት የልቦና ሕግ ማለት ሲሆን የሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ኑሮአቸውን በዚህ ምድር ላይ እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው፣ እንዲሁም ከአምላካቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በልባቸው የሐሳብ ሕግ ብቻ የሚተዳደሩበት ጊዜ /በጽሑፍ የሆነ መመሪያ ያልነበረበት ዘመን/ ማለት ነው፡፡ ግንኙነታቸውንም በልቡና ሕግ ይፈጽሙት ነበር፡፡ ከእነዚህ አገልግሎቶች ውስጥም አንዱ የክህነት አገልግሎት ነው፡፡ ክህነት በሕገ-ልቡና አገልግሎቱ ሲፈፅም ቢታይም ሹመቱ ግን ለእከሌና ለዚህ ነገድ ተሰጠ በዚህም መልክ ይከናወን ነበር የሚል የተገለፀ ታሪክ የለም፡፡ ማለትም የተጻፈ መመሪያም ሆነ የመተዳዳሪያ ደንብ አልነበራቸውም፡፡ የክህነት አገልግሎት በኋለኛው ዘመን/ በሕገ-ኦሪት/ በተገለጠ ጊዜ ዋና ዓላማው መስተዋፅኦትን ማቅረብ መሆኑ በቅዱሳት መጻሕት ተጽፎአል፡፡ ለምሳሌ የመጀሪያዎቹ ሰዎች አቤልና ቃየል መስዋዕትን ለእግዚአብሔር እንዳቀረቡ በዘፍ 4÷3-4 እናነባለን፡፡ በኋላም እንደእነ ኖህ መልከ ጼዴቅ፣አብርሐም፣ኢዮብ ያሉ አባቶች ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ይህንን አገልግሎት ያከናውኑት ነበር አውቀናል፡፡ ዘፍ8÷20 12÷7 ኢዮ 1÷5፡፡

ከእነዚህ አባቶች መካከል በዘመነ ሕገ-ልቡና የክህነትን ሹመት ከማንና እንዴት እንደተቀበለ የትውልድ ሀረገ-ዘሩም የማይታወቀውን ለዘለዓለምም በልዑል እግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ የሚኖረውን መልከ-ጼዴቅን እናገኛለን ዕብ 5÷6፡፡ መልከ ጼዴቅ ሹመቱን በውርስ ያላገኘውና የእርሱን ክህነትም ወደ ሌላ አካል ስላላስተላለፈው የሐዲስ ኪዳኑን ሊቀ-ካህናት ሹመት ሊመስል ተገባው፡፡ ይህ ካህን የነገደ እስራኤልን አባት አብርሐምን የባረከ ከእርሱም አሥራትን የተቀበለ ሰው ነበር፡፡

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ታናሽ በታላቅ ይባረካልና አሮንና ዘሮቹ /ነገደ-ሌዋውያን/ ከእዚህ አባት በአባታቸው ጉልበት /ዘር/ ውስጥ ሆነው እንደተባረኩ አስራትንም ለመልከ ጼዴቅ እንዳቀረቡ ተቆጥሮላቸዋል ይላል ቅዱስ መጽሐፍ ዕብ 7÷7-10። ይህም ስለ ሊቀ ካህናት አሮን ሊቀ-ካህናቱ መልከ-ጼዴቅ ነበር ማለት ነው። ከዚህ የተነሳ ከሌዋውያን የክህነት ማዕርግና አገለግሎት ይልቅ የተሻለ መሆኑን መመልከት ይቻላል።

2.1.4. ክህነት በዘመነ ሕገ-አሪት

ክህነት በዚህ ዘመን የተጀመረው እግዚብሔር ቃል ኪዳን የተገባለትን የተስፋን ዘር ከባርነት ነፃ ባወጣበት ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት በብዙ ድንቅና ተዓምራት ከንጉሥ ፈርዖን የጭካኔ አገዛዝ ነፃ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲወስዳቸው በሲና ተራራ ላይ 10ቱን ሕግጋት የያዘ 2ት የድንጋይ ፅላትን ለሙሴ ሰጠው። ህዝቡ ግን ጣዖትን ሰርተው ሲያመልኩ ተገኙ እግዚአብሔር አምላክም ሕዝቤ ብሎ በሚጠራው ትውልድ ውስጥ እንዲህ አይነቱን አመንዝራነት /ጣኦትን ማምለክ/ በማየቱ ተቆጣ።

ሙሴም የእግዚአብሔር ቁጣ ለማብረድ የእግዚብሔር ወገን የሆነ ወደኔ ይምጣ ብሎ ሲጣራ የሌዊ ልጆች ሁሉ "እኛ የእግዚአብሔር ወገን ነን" በማለት ወደ ሙሴ ተጠጉ ዘፀ 32÷19-20። ሙሴም የእስራኤል አምላክ እግዚብሔር እንዲህ ይላል " የእናንተ ሰው ሁሉ ሰይፍን በወገቡ ላይ ይታጠቅ በሰፈርም ውስጥ በዚህና በዚያ ከበር እስከ በር ይመላለስ... የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ብሎ ያልመጣውን ሁሉ ወንድሙን ወዳጁን ጐረቤቶቹን ይግደል..."አላቸው።የሌዊ ልጆችም ሙሴ እንዳላቸው አደረጉ ዘፃ 32÷26+29። እነዚህ የሌዊ ልጆች /የነገዶች/ ሁሉ በራሳቸው ፈቃድ የእግዚአብሔር ወገንተኝነትን መርጠው ስለተጠጉ እግዚአብሔር ያገለግሉት ዘንድ በእርሱና በሕዝቡ መካከል "መካከለኛ" እንዲሆኑ የክህነትን ስልጣን ሰጣቸው ዘፀ 28÷1። ከዚህ ታሪክ እንደምንገነዘበው ክህነትን ወይም የአገልግሎትን ሹመት ለማግኘት፡-

ሀ. የእግዚአብሔር ወገን መሆን

ለ. የታመኑ ሆኖ መገኘት /መታመን/

ሐ. ከራሳቸውና ከቤተሰቦቻቸው ክብር ይልቅ የእግዚአብሔርን ክብር ማስቀደም፣

መ. ሁሉን ትተው ርስታቸው እግዚአብሔር ያደረጉ የሚል ጥቂቶቹ ናቸው።

❖ *የእግዚአብሔር ወገን የሆኑ፡-*

እስራኤላዊያን ከግብፅ የባርነት ቀንበር ያወጣቸውን አምላክ ትተው በእጃቸው ለሠሩት ጣዖት ሲሰግዱ ተገኝተዋአል። በዚህ በደል ውስጥ የሌዊ ነገድም ቢሆን ንፁህ ሆኖ አልተገኘም። ነገር ግን የእግዚብሔር ሰው ሙሴ የእግዚአብሔር ወገን ወደ እኔ ይመጣ

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

የሚል ጥሪን ባስተላለፉ ጊዜ ስህተታቸውን አምነው ወገንነትን ሽተው የእግዚአብሔር ሰው እንዳዘዛቸው አድርገዋል። እግዚአብሔር ከሚያስደስተው ውስጥ ሃጢያትን ተናዝዞ በንሰሐ ወደ እርሱ መቅረብ ነው። በዚህ የንስሐ አካሄዳቸው ለሌሎች ነገዶች ከእግዚብሔር እርቅን የሚለምኑ አገልጋዮች እንዲሆኑ ተመረጡ።

❖ የታመኑ፡-

መታመን ሁል ጊዜ ከወገናዊነትና ከሚያምኑበት ነገር ጋር መጣበቅን ያሳያል። ነገደ ሌዊ "የእግዚአብሔር ወገን ነን" ብለው ከቀረቡበት ጊዜ አንስቶ ለእግዚአብሔር ታማኞች ከመሆናቸው የተነሳ በእግዚአብሔር ቤትና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሹመትን ሊያገኙ ችለዋል።

❖ የእግዚአብሔር ክብር የሚያስቀድሙ፡-

አንድ አገልጋይ በእግዚብሔር ና በመረጠው ሕዝብ ላይ አገልጋይ ሆኖ ለመሾም የእግዚአብሔርን ክብር በሚገባ የማወቅ ግዴታ አለበት። ምክንያቱም የመሾሙ ዓላማ የእግዚአብሔርነ ክብር ለመግለጥ ነውና። የእግዚአብሔርን ክብር ለመውሰድም ሆነ ለመካፈል በሚሻ ማንኛውም አካል ላይ ርምጃን ለመውሰድ የማያቅማማ አገልጋይ ከራሱ ክብርም የአምላኩን የሚያስቀድም እርሱ ካህን ሊሆን የተገባው ነው። ነገደ ሌዋውያንም ያደረጉት ቢኖር የእግዚአብሔር ወገንነታቸውን ባልሰጡት ነገዶች ላይ እርምጃን ሊወስዱ ከእራሳቸውና ከቤተሰቦቻቸው ክብር ይልቅ የእግዚአብሔር ክብር በማስቀደማቸው የእግዚአብሔር ውክልና ለመቀበል በቁ ዘፀ 32÷28-29።

❖ ሁሉን መተው፡-

ሌዋውያን ሁሉን ትተው በመከተላቸው ሁሉ ያለው እግዚአብሔር ርስታቸው ሆነላቸው። ዘፀ 33÷6።

2.1.5. የክህነት ተልዕኮ በሕገ-ኦሪት፡-

ተልዕኮ ሲባል ራዕይን ለማስፈፀም ካህኑ ወይም ተሿሚው የሚያልፍባቸው የግብ መስመሮች ማለት ነው። የሕገ-ኦሪት የክህነት ተልዕኮን በምናይበት ጊዜ እስራኤል በጊዜው ከሚደርስባቸው መከራና ችግር ምሕረትን ለማግኘት የሚያከናውኗቸው ሥርዓቶች ናቸው። ተልዕኳቸውን ለመመልከትም ልዑካኖች የሚያገለግሉበትን ቦታና አገልግሎታቸውን በስፋት መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

2.1.6. የሕገ- ኦሪት ካህናት የት ያገለግላሉ?

ነገደ ሌዊ የሕገ-ኦሪት ካህናት/ የሚያገለግሉት እግዚአብሔር ክብሩን በሚገልጥበት ቦታ ነው። ይህም ቦታ የማደሪያው ድንኳን ይባላል። ይህንን ድንኳንና በውስጡ ያሉትን ንዋየ-ቅዱሳት ምሳሌያው እና አማናዊ ትርጉማቸውን ስንመለከት፡-

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዧት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

2.1.6.1. የመገናኛው ድንኳን/ ደብተራ ኦሪት/

የመገናኛ ድንኳን ማለት አብረው ያልቁዩ ይልነበሩ አካላት የሚገናኙበት በጋራ የሚከትሙበት ማለት ሲሆን ድንኳን በመባሉም ጊዜያዊነቱን ይገልጣል። የመገናኛው ድንኳን እስራኤላዊያን በጉዞ ላይ እያሉ ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ለእርሱም ስግደትንና አምልኮን የሚያቀርቡበት ሥፍራ ነበረ ዘሌ 26÷11። የመገናኛው ድንኳንና በውስጡ የሚገኙት ቁሳቁሶች የተሠሩት እስራኤላውያን በፈቃዳቸው ላይ በተመሰረተ የጌጣጌጥ ስጦታዎች ነው። ይህም ከጽላቱ በቀር ማለት ነው ዘፀ 25÷1-291፣36÷3-6 ድንኳኑ የሚተከለው ሁል ጊዜ በሕዝቡ መካከል ሲሆን ይህም አምላካቸው በመካከላቸው መገኘቱ የሚገልጥበት ነበር።እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ለመገናኘት ለምን በድንኳን ማደር አስፈለገው? ስንል ከአዳም እዳ በደል የተነሳ የሰው ልጆች ሁሉ ሃጢአተኞች በመሆናቸው ሃጢአትን የማይወድ ባህርይው በሰዎች ማደር ስላላስቻለው ነበር። ቢሆንም በድንኳኑ ያደረው በጊዜያዊነት ነው ኤር 3÷16 ፣32÷38 ዕብ 8÷6+7። ጊዜው በደረሰ ጊዜ አንድያ ልጁ ከሴት እንዲወለድ ከሕግም በታች እንዲሆን ፈቀደ ገላ 4÷4። የአዳም እዳ በደልም በኢየሱስ ሕማምና ሞት ምክንያት ከሰው ልጆች ተንከባልሎ ወደቀ። ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔርንና ሰውን ያገናኘ የመገናኛ ድንኳናችን የቤተክርስቲን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነልን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝብንና አሕዛብን፣ጥቁር ነጩን፣ ጨዋና ባሪያውን አዋህዶ አንድ ካደረገን በኋላ ከአባቱ ጋር አገናኘን። በወንጌልም "... እለ የአምኑ ብየ በቃሎሙ ከመ ይኩነ አሐደ ኩሎሙ በከመ አንተ አብ ብየ ወአነሂ ብከ ከመ ይኩኑ እሙንቲሂ አሐደ ብነ ከማነ ከመ ይእመን ዓለም ከመ አንተ ፈነውከኒ- ከመ ይኩኑ አሐደ ከማነ ከመ አሐዱ ንህነ.."ዮሐ 17÷20-23። እንዳለ ከእርሱ የተነሣ ከአብ ጋር እንድንገናኝና አንድ እንድንሆን የመገናኛ ድንኳናችን መሆንን ወደደ። ሙሴ በምድረ-በዳ የሠራት ድንኳን ከሰማያዊቷ ድንኳን ጋር በንጽጽር ስንመለከት ሶስ ዋና ዋና ክፍሎች እንዲልት እንመለከታለን እነርሱም፡-

1. ዓውደ ምሕረት
2. ቅድስት
3. ቅድስተ ቅዱሳን ??

2.1.6.2. ዓውደ-ምሕረት፡-

ዓውድ ማለት ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው አደባባይ ቦታ ስፍራ እንደማለት ሲሆን ምሕረት ማለት ደግሞ ይቅርታ ማለት ነው። ሁለቱን ቃላት አዛረፈን ስናነብ ዓውደ መሕረት እንላለነ ትርጉሙም ይቅርታ የሚገኝበት /የሚደረግበት/ ስፍራ /ቦታ/ ማለት ነው። በዚህ ስፍራ ውስጥ እንደገባን የንሰ መሰዊያውን እናገኛለን።

2.1.6.2.1. የነሐስ መሰዊያ፡-

ነሐስ ማለት ከሰማያዊና ከአረንጓዴ አፈር መሰል ማዕድን ተነጥፎ የሚወጣ ብረት ነክ ቁስ ነው።* [29] መሰዊያ ማለት ደግሞ ሰው ለሚያመልከው ወይም ለሚፈራው አንዳች ነገር አክብሮቱን የሚገልፅበት /የሚያቀርብበት/ ዕቃ ነው። ስለዚህ የነሀስ መሰዊያን ከመጽሐፍ ቅዱስ

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

አንጻር ስንመለከተው ከግራር እንጨት ተሰርቶ በነሀስ ስለተለበጠ የነሀስ መሰዊያ የሚለውን ስያሜ ሊያገኝ ችሏል።

አገልግሎቱም ለአንድ ኃጢተኛ ሰው ለሀጢያቱ ስርየት የሚሆነውን በግ በተለዋጭ /በምትክ/ አቅርቦ ስለሀጢያቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚሰዋበት ንዋየ ቅድሳት ነው ዘሌ 5÷14-19። ሀጢያተኛው ለመስዋዕት የሚቀርበው በግ ይዞ በዚህ ሥፍራ ከሊቀ-ካህናቱ ጋር መገናኘቱ እጅ አስፈላጊ ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሀጢያተኛው ሰው እጅ የይቅርተውን መስዋዕት ስለማይቀበል ሀጢያት ተለዋጭ ወይም ምትክ በሆነ በግ ላይ ሀጢያተኛው እጁን እንዲጭን ያዝዘዋል። በዚህ አድራጎቱም በእግዚብሔር ፊት መስዋዕት ሊሆን ከቀረበው በግ ጋር ለቅጣት እንደቀረበ ሆኖ ይታያል። ምክንያቱም ደም ሳይፈስ የሀጢያተኛው ደሙን ባየጊዜ የሀጢያት ሥርየት እንደተደረገለት ስለሚሰማው በልቡ ሀሴትን ያደርጋል ምንም እንኳን ሀሰቱ ፈጹም ባይሆንም""

ምንም እንኳን ይህ ሀጢያተኛ ሰው የሀጢያቱን ስርየት ተመልክቶ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ ነውና የቆመ መስሎ ቢሰማውም በቀጣዩ ቀን ለሚበድለው በደል/ መተላለፍ/ ዳግመኛ መስዋዕትን እስካላቀረበ ድረስ ያው ሀጢያተኛነቱ ግልፅ ነው።

2.1.6.2.2. የበጉ ደም በመሠዊያው ላይ መረጨቱ

ሊቀ ካህናቱ የበጉን ደም በአራቱ ማዕዘናት የመሰዊያ ገጽታ ደሙን እንደሚረጨው ሁሉ ጌታችን ኢየሱም በቀራንዮ አደባባይ በተመስቃለ እንጨት በተሰቀለ ጊዜ የፈሰሰው ደም በአራቱ ማዕዘናት- ዓለም ለሚገኙ የሰው ልጆች ሁሉ ስለሀጢያታቸውና ስለበደላቸው የፈሰሰውን ደም ያሳያል።

2.1.6.2.3. የበጉ አካልና ቆዳው/ ቀሪ አካሉ/ ከሰፈር ውጭ መቃጠሉ

አሪታውያን ሰዎች ለሀጢአት ቅጣት የታረደውን በግ ቀሪ አካል ከሰፈር ውጭ አውጥተው ካቃጠሉት በኋላ ልብሳቸውንና ገላቸውን በውሃ ታጥበው ይመለሱ ነበር። ይህም ሀጢአትን ከመፀየፋቸው የተነሣ እንደበር እናነባለን ዘሌ 6÷11፣ዘሌ 16÷27። ክርስቶስም ስለ ሰው ልጆች ሀጢአት ሲለ ሀጢአት ያላወቀው ስለእኛ ሀጢአት ባደረገው ጊዜ ከሰፈር ውጭ /ከበር ውጭ/ ተጣለ። መጽሐም እንዲህ እንዳለ " ወበእንተዝ ኢየሱስኒ ከመ ይቀድሶሙ ለሕዝብ በደሙ በአፍአ እምትዕይን ተቀትለ" ዕብ 13÷12 ትርጉም ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ። ሊቀ ካህናት ስለ ሀጢአት ወደ ቅድስት የእንስሶችን ደም ያቀርባልና ሥጋቸውን ግን ከሰፈሩ ውጭ ይቃጥላል።

2.1.6.2.4. ሰን /የመታጠቢያ ሳህን/

በአደባባዩ ወይም በዓውደ ምሕረቱ ከምናገኛቸው ንዋየ ቅዱሳት መካከል በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው የመታጠቢያ ሰን ይበላል። ስን፡- ከነሐስና ከመዳብ አንዳንዴም ከብረት ሊሠራ ይችላል። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚገኘው ሰን ግን ከነሐስ እንዲሰራ ታዝዟአል ዘፃ 30÷18። አገልግሎቱም ካህናት ወደ ቅድስት ከመግባታቸው በፊት እጅና እግራቸቸውን

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

የሚታጠቡበትን ውሃ የሚይዝ ነው። የአሮን ልጆች ወደ ቅድስት ለአገልግሎት ከመግባታቸው በፊት ወደ እዚህ መታጠቢያ ስን ቀርበው ሊታጠቡ ይገባል። ሳይታጠቡ ቢገቡ እንደሚሞቱ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል ዘፃ 30÷20። ይህንን የመታጠብ ስርዓትም /ህፅበት/ ዕለት ዕለት በማከናወናቸው ወደ ቅድስት ይገቡ ዘንድ ድፍረት የሆንላቸው ነበር።

የአሮን ልጆች ወደ ቅድስት ለመግባት በውሃ መታጠባቸው ድፍረስ እንደሆናቸው ሁሉ ለእኛም የሐዲስ ኪዳን ካህናት/ አማኞች/ ወደ ሰማያዊቷ ድንኳን /መንግስተ-ሠማያት/ ለመግባት በእግዚአብሔር ልጅ ደም ከሀጢአታችን በመታጠብ እንደምንጸድቅና በዚህም ድፍረትን እንደምናገኝ እንረዳለን "የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሀጢያት ሁሉ ያነፃል" 1ኛ ዮሐ 1÷8። ይህንን ቃለ ሰምተንና አምነን በሙሉ ፈቃደኝነትም ከተቀበልን እና ሥጋውን ከበላንና ደሙን ከጠጣን ድፍረት ይሆንልናል "ወአንትሙስ ወዳዕክሙ ንፁህን አንትሙ በእንተ ቃል ዘነገርኩክሙ "ትርጉም፡- እናንተ ስለነገርኳችሁ ቃለ አሁን ንፁህን ናችሁ እንዳለ ጌታ በወንጌል ዮሐ 15÷3።ይህንን በዕምነት የተገኘ የፀጋ ድፍረት ይዘን ወደ አባታችን መንግስት ገብተናል።

2.1.6.3. ቅድስት

<u>+ ቅድስት፡-</u> የመገናኛው ድንኳን ወይም የማደሪያው ድንኳን ሁለተኛው ክፍል ነው። ቅድስት ምንድን ነው? እንዴትስ የአገልግሎት ሥርዓቱ ይከናወንበታል?የሚለውን ሰፊና ልብ አንጠልጣይ ታሪክ ስንመለከት።ቀደሰ ለየ ቅዱስ ልዩ ቅድስት የተለየች ከሚለው የግዕዝ ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን ቅድስት ከቦታ ሁሉ የተለየች ቦታ ማለት ነው፡

ወደዚህ ቦታ ከአሮን ለጆች በቀር ማንኛውም ሰው የመግባት መብት የለውም። እነርሱም ወደዚህ ቦታ እንዲገቡ ያስቻላቸው የክህነትን ስልጣን ከእግዚአብሔር ያገኙ በመሆናቸው ነበር። ክህናት ይህችን በር አልፈው እንደገቡ በቀጥታ ዓይናቸው የሚያርፈው ከድፍን ወርቅ ተቀጥቅጦ ከተሰራው የወርቅ መቅረዝ ላይ ነው።

2.1.6.3.1. መቅረዝ፡-

ከወርቅ የተሠራ በከፍታ ቦታ የሚቀመጥ፣ክህነት በሚያገለግሉባት ቦታ ጨለማን የሚያስወግድ አይነተኛ ነዋየ ቅዱሳት ነው። በተለይም በመጋረጃ ከላይ እስከታች ለተሸፈነችው ቅድስት ጠቀሜታው የጎላ ነው። ምክንያቱም ካህናት በቅድስት ውስጥ ሲገቡ መቅረዙ ባይኖር ኖሮ የትና እንዴት? እንደሚያገለግሉ አያውቁም ነበር። ዛሬም በነቢያትና በሐዋርያት የአስተምህሮ ፍጻሜ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ የማይኖሩ የሐዲስ ኪዳን አማኞች ማንን? እንዴትና የት? አገልግሎታቸውን መፈፀም እንዳለባቸው ሊረዱ አይችሉም።

ጌታችንም በወንጌል "በጨለማ የሚመላለስ ወዴት እንዲሄድ አያውቅም የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃኑ እመኑ" ዮሐ 12÷35 እንዳለን ልብ ልንል ያሻል። በሌላ

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ክፍልም አጋር ከየት መጣሽ? ወደየትስ ትሄጃለሽ? ብሎ የእግዚብሔር መላክ በጠየቃት ጊዜ የመጣችበትን ከመናገር በቀር ወዴት እንደምትሄድ አላወቀችም። ነበር ዘፍ 16÷8-9።

ዛሬም አኛ ማን ፈጠራችሁ ስንባል ሥላሴ ከማለት በቀር የት ትሄዳላችሁ?ስንባል የምንሄድበትን የምናውቀው ከሞት በኋላ ነው እንላለን። እንዲህ ያለው መልስ የመጣው ካለማመን ነው። እንደዚህ በማለታችን እግዚአብሔርን የመፍራት ራስን ዝቅ የማድረግ መንፈስ እንዳለን ይመስለናል። ነገር ግን ይህ እግዚብሔር የመፍራትና እራስን ዝቅ የማድረግ መንፈስ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተን መጻሕፍትን የመመርመር ችግርና አለመታመንን እንዲሁም ሙታንን ያድን ዘንድ በሞቱ ሞትን ባጠፋልን መድኃኔዓለም ላይ ትምክህት እንደሌለን የሚያሳይ ለመሆኑ ብዙ መጥቀስ አያሻውም። ቅዱስ ወንጌል “በክርስቶስ ኢየሱ ያሉ አሁን ኩነኔ የለባቸውም “ የሚለውን መለኮታዊ ቃል ሽረንና አቃለን እኔ በአምላኬ ትምክህት ሞት ድኛለሁ እንዳንል ትህትናን በተላበሰ የሰይጣን አዚም ሥር ወድቀን እንገኛለን።

ወደ ቅድስት በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ታጥበንና ታጥነን በሥጋው መጋረጃነትም በድፍረተ የገባን ዕብ 10÷19 ክርስቲያን የተባለን ሰዎች የዓለም ብርሃን በሆነው መድኃኔዓለም ዮሐ 12÷46 ላይ ዓይናችንን በማሳረፍ መዳረሻችንን አውቀን ተስፋ ስለምናደርገው መንግስተ ሰማያት ታምነን ልንኖር ያስፈልጋል። መቅረዙ ከአንድ ወጥ ወርቅ ተቀጥቅጦ የተሰራ ሲሆን አንዱ የወርቅ ግንድ ሲቀጠቀጥ ቅርንጫፎች እንደ ተገኙበት ሁሉ በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ /በሁለተኛው አዳም/ መከራ መቀበል ቅርንጫፍ የመሆን ብቃት አግኝተናል። በዚህም ከዘላለም ሞት ድነናል። ጌታም በወንጌል “ አነ ውዕቱ ጕንደ ወይን ወአንትሙሂ አኀጹቂሁ” ማለት እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ እንዳለን ዮሐ 15÷5። እርሱ የወይን ግንድ ሆኖ እኛን ቅርንጫፎቹ አድርጐናል። አያይዞም ቅርንጫፍ ከግንዱ ተለይቶ ምንም ማድረግ ስለማይችል ያለ እኔ ምንም ልታደረጉ አትችሉም ብሎና ዮሐ 15÷5 ስለዚህ ያለእርሱ ምንም መድረግ አንችልም።

ማንኛውም ሰው በባህርይው ብርሃን መኖርና መመላለስ ይወዳል። የወደደን የሚያገኘው ደግሞ በኢየሱስ ክርቶስ የሕይወት ብርሃንነት ሲያምን ነዉ። ብርሃን ባለበት ጊዚያው ጨለማ እንደማይኖር ሁሉ ዘለዓለም የሆነው የሕይወት ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለበት ደግሞ ዘለዓለማዊው ጨለማ አያገኘውም። የብሉይ ኪዳን ካህናት በቅድስቲቱ ውስጥ በመቅረቡ ብርሃን እንደተመላለሱ ሁሉ፣ ለሰማያዊቷ ቅድስት ደግሞ ሰማያዊ መቅረዝ እርሱም የእግዙአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖልን እንኖራለን ራዕ 21÷23። ለዚህም መጽሐፍ ሲመሰክር “ጨረቃ ይታወካል ፀሐይም ያፍራል” ኢሳ 24÷23 እንዲሁም “ቅዕርሽን መዳን በሮችሽንም ምስጋና ብለሽ ትጠሪያለሽ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የዘለዓለም ብርሃንሽ አምላክሽም ክብርሽ ይሆናልና ፀሐይ በቀን ብርሃን አይሆንልሽም የጨረቃ ብርሃንም በሌሊት አያበራልሽም እግዚአብሔር የዘለዓለም ብርሃንሽ ይሆናልና የለቅሶሽንም ወራት ታልቃለችና ፀሐይሽ ከዚህ በኋላ አትጠልቅም ጨረቃሽም አይቋረጥም” ኢሳ 60÷18-21 እንደተባለላት እኛ አማኞች ለምንኖርባት መቅደስም በጉ የዘለዓለም ብርሃኗ ሆኖ ይኖራል።

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጕብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ዓይኑን ዘወትር ወደዚህ መቅረዝ /ኢየሱስ/ የሚያደርግ አማኝ ለዘለዓለም ጨለማም በማይታይበት ቦታ ያድራል። ምክንያቱም እኛ አማኞች ከብሉይ ኪዳን የዘር ውርስ ክህነት ወጥተን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመግችን ምክንያት በደሙ በተደረገልን የዝምድና ትስስር የክህነትን ማዕረግ አግኝተናል። እናም ወደ ሰማያዊት ቅድስት ገብተን የክህነት ሥራችንን የማከናወን ብቃት /ስለጣን/ አለን ራዕ 1÷61 ፣ 5÷10፣ 1ኛ ጴጥ 2÷5።

2.1.6.3.2. የህብስት ገበታ

የህብስት ገበታ በቅድስት ውስጥ ከሚገኙት ንዋየ ቅዱሳት ውስጥ ሁለተኛው ሲሆን ከመቅረዙ ፊት ለፊት ይቀመጣል። አገልግሎቱም በእግዚብሔር ፊት ሁልጊዜ የማይለዩ ወይም ሊታዩ የሚችሉ 12 ህብስቶችን/ ዳቦዎችን/ መሸከም ነው። ህብስቶችም እንዳይወድቁ የሚደግፍ አንድ ክንድ ተኩል ከፍታ ያለው በወርቅ የተለበጠ ክፈፍ አለው ዘፃ 25÷23-30። በገበታው ላይ ህብስቶቹ ስድስቱ በአንድ ረድፍ ስድስቱ ደግሞ በሌላኛው ረድፍ ይደረደራሉ።የህብስቱ ማስቀመጫ ገበታም ከግራር እንጨት የተሠራ ነው።

2.1.6.3.2.1. የገበታው ዓላማ

አስራ ሁለቱን ነገደ-እስራኤል ሊወክሉ የሚችሉ ህብስቶችን መሸከም ነው። እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ የተገለጠው የዓለምን ሕዝብ በመወከል በእግዚአብሔር /በአባቱ/ ፊት ሊታይልን ነው ዕብ 9÷24 ገበታው ህብስቶችን ተሸክሞ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ነበር ሁሉ ዘፃ 25÷30። ክርስቶስም የሰው ልጆችን ሃጢአት ተሸክሞ በአባቱ ፊት በመታየቱ ከእርሱ የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን እንድናገኝ አድርጐናል፡ ፡ የአሮን ልጆች /የሕገ-አሪት ካህናት፣ ወደ ቅድስት ሲገቡ ገበታው ህብስቱን እንደተሸከመው የሚያዩት ከመቅረዙ በሚወጣው የዘይት ብርሃን እንደሆነ ሁሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታም አስቃቂ የነበረውን ሀጢያታችንን ኢየሱስ ተሸክሞ ስለ እኛ ዕዳ በደል እንደተንገላታ መንፈስ ቅዱስ ያሳስበናል 1ኛ ቆሮ 4÷6።

2.1.6.3.3. የዕጣን መሰዊያ

በቅድስቱ ውስጥ ከሚገኙት ንዋይ ቅዱስት ውስጥ ይህ ሦስተኛው ነው። አሰራሩም ከግራር እንጨት ሆኖ በወርቅ የተለበጠ ነው። አገልግሎቱም አሮን / ሊቀ-ካህናቱ/ በየማለዳው መብራቶቹን በሚያዘጋጅበትና በምሽትም መብራቶችን በሚያበራበት ጊዜ ጣፋጭ የሆነውን የዕጣን ሽታ ለእግዚብሔር የሚያቀርብበት መሰዊያ ነው ዘፃ 30÷1-10። ይህ የዕጣን መሰዊያ ለእግዚአብሔር ፍፁም የተለየ ንዋየ ቅድሳት_ነው፡ ምክንያቱመ በዚህ መሰዊያ ላይ ከንፁህ በስቀር የሚቃጠል መስዋዕትም ሆነ የእህል ቁርባን እንዲሁም ባዕድ የሆነ ዕጣን፣ የመጠጥም ቁርባን እንዳይቀርብበት ጥብቅ የሆነ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነበር ዘፃ 30÷9-10።

በመስዊያው ላይ ባዕድ የሆነው እጣን ቢቀርብ መስዋዕቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም፣ እግዚብሔር በዚያ ለአሮን እንዳይገለጥለት መጋረጃም ይሆንበት ነበር፡ ፡ እግዚብሔር የወደደው እጣን ግን በመሰዊያው ላይ በቀረበ ጊዜ "እኔ እግዚአብሔር ለአሮን

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

በዚያ እገለጥለታለሁ" እንዳለ ዘፃ 30÷6። ዛሬም እንደ አሮን ክህነት ባልሆነ ነገር ግን እንደመልከ ጼዴቅ ሹመት የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን የተወደደ ንፁህ የመዓዛ ሽታ አድርጐ ስለእኛ ለእግዚአብሔር በማቅረቡ እግዚአብሔር በዚህ መስዋዕት ተገልጦልናል ኤፌ 5÷2።

2.1.6.4. ቅድስተ-ቅዱሳን

+ ቅድስት-ቅዱሳን ማለት ከተለዩት የተለየች ከተመረጡት የተመረጠች ልዩ ክፍል/ ቦታ/ ማለት ነው። በዚህች የተቀደሰች ቦታ "ለእግዚብሔር ወገኑ" ነን ብለው ወደ እግዚብሔር እራሳቸውን ካስጠጉ ካህናት መካከል የተመረጠው ሊቀ ካህናት/ አሮን/ ብቻ በዓመት አንድ ጊዜ ይገባባታል ዘፃ 32÷26፣ዘሌ 16÷2።

ቅድስተ-ቅዱሳን ከቅድስት የምትለየው በመጋረጃ ነው። መጋረጃውም ሰማያዊ፣ ሀምራዊና ቀይ ግምጃ/ ጨርቅ/ በቀጭንም የተፈተለ በፍታ ነበር። በመጋረጃው ላይም ኪሩቤል በጥልፍ ጥበብ ይሳሉበታል ዘፃ 26÷31። የዚህ መጋረጃ ጥቅምም በቅድስት የሚያገለግሉትን ካህናት የእግዚአብሔር ክብር በሙላት በሚገለጥባት በዚህች የመጨረሻዋ ክፍል እንዳይገቡም ሆነ እንዳያዩ የሚጋርድ ነበር ዘፃ 26÷33። ምክንያቱም ሰው የእግዚአብሔር ክብር ቢያይ ይሞታልና ዘፃ 33÷20 ሊቀ-ካህናቱ /አሮን/ በየቀኑ ወይም በፈለገው ጊዜ ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን እንዳይገባ ማስጠንቀቂያ በሙሴ አማካኝነት ተሰጥቶታል ዘሌ 16÷2። ይህንንም ትዕዛዝ ተላልፎ ቢገኝ የሞት ቅጣት ይጠብቀዋል ዘሌ 16÷2። መጋረጃው በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ለዘመናት ለይታን የኖረችውን የውርስ ኃጢአት ወይም መተላለፍ ታሳየናለች ኢሳ59÷2። ይህ የውርስ ኃጢአት ከአንዱ ወደ ሌላው ይተላለፍ የነበረው በዘር/ በውልደት/ ነበር። እነዚህ ካህናት ከዚህ የዘር ሐረግ በተለየ መንገድ ሰው ሆነው እስካልተገኙ ድረስ ማንኛውም ሰው ደክሞ በተገኘበት ኃጢአት እነርሱም ድካም ለብሰው ስለሚገኙ ይህን መጋረጃ ማለፍ/ መግለጥ/ ይከለከሉ ነበር። በዚህ ምክንያት ወደ ውስጠኛው ክፍል ገብተው የእግዚአብሔር ክብር ለማየት እጅግ ይጓጉ /ይመኙ/ ነበር።

ይህንን የዘመናት ናፍቆትና ምኞታቸውን ሊፈፅም ችሎታና ብቃት ያለው በደሀ ቤት ያደረ፣ ምስኪን፣ ደሀና ጥበበኛ የሆነ ከይሁዳ ነገድ ተገኘ መክ 9÷13-17 እነርሱም የሥጋ ፈቃዳቸውን ሊያሟላ በሚችል መንገድ ባለመገለጡ ተቃወሙት። ከሰፊር ውጭም አውጥተው ወንበዴዎች በሚቀጡበት የእንጨት መስቀል ሰቀሉት። ይሁን እንጅ እርሱ /የናዝሬቱ ኢየሱስ/ በመስቀሉ ለዘመናት ክልክሎአቸው የነበረውን መጋረጃ ለሁለት ቀደደላቸው ማቴ 27÷51 የዚህ መጋረጃ መቀደድ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለእኛም አሕዛብ ተብለን ለተጠራነው ጣዖት አምላኪዎች ወደ ምድራዊቱ ቅድስተ ቅዱሳን ሳይሆን ወደ ሰማያዊቱ ቅድስተ ቅዱሳን አልፈን እንድንገባ ብቃታችን ሆነልን በዚህም አሕዛብ የሚለውን ልዩነት አጠፋልን።

በወንጌል እንዲህ እንደተባለ "...ሁለቱን ያዋሀደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትዕዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥልን ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስ

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ሰው ይፈጥር ዘንድ...ጥልንም በስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን /እኛና አይሁድ ማለትም ሕዝብና አሕዛብ/ በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው" ኤፌ 2÷14-17 ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ሰው ሆነን ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀን በአንድ መንፈስም ወደ አብ መድረስ ሆነልን፡፡ በዚህች መጋረጃ ላይ ኪሩቤል ስዕል በጥልፍ ጥበብ ተስለው ይታዩባት ነበር፡፡ ኪሩብ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጡት ሰው የሕይወት ዛፍን በልቶ ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር በተከለከለበት ጊዜ ነበር ዘፍ 3÷24፡፡

በቅድስት- ቅዱሳን መግቢያ መጋረጀ ላይ ተስለው መታየታቸውም ከገነት ያስወጣችን ከእግዚአብሔር የለየችንን ኃጢአት እስከዚያ ዘመን ድረስ የሚያሳስቡን ነበሩ፡፡ ከዚህ መጋረጃ በስተጀርባም ሁለንተናዋ በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በአርሷ ውስጥም መና ያለባት የወርቅ መሶብ/ የበቀለች የአሮን በተርና የኪዳን ጽላትን እናገኛለን፡፡

2.1.6.4.1. የቃል ኪዳኑ ታቦ

ታቦት የሚለው ቃል በዕብራይስ "ቴብሃህ" ማለትም ሳጥን መሰል ባለመክደኛ፣ ለዕቃ ማስቀመጫ የሚያገለግል እንደማለት ነው፡፡"የቃል ኪዳን ታቦት" ማለትም ሳጥን መሰል ባለመክደኛ፣ ለዕቃ ማስቀመጫ የሚያገለግል እንደማለት ነው፡፡ ማደርያነቱም ለሁለቱ የደንጋይ ሰሌዳዎች ነው፡፡ ሰሌዳዎቹም /ጽላቶቹም/ በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ ሕግጋትን የያዙ ናቸው፡፡

+ **<u>ኪዳን</u>** ማለት ደግሞ ተካየደ ተስማማ ተማማለ ውል አደረገ ማለት ሲሆን፡- ቃል-ኪዳን ማለትም ሁለት ወይም ከሁለት በለይ በሆኑ አካላት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡ በዚህም ስምምነት ውል አቅራቢና ውል ተቀባይ አካላት/ ወገኖች/ መገኘታቸው የግል ነው፡፡ ውል አቅራቢ ማለት የውሉን ሰነድ አዘጋጅቶ የሚያቀርብ ሲሆን ውል ተቀባዩ ደግሞ በውል አቅራቢው በኩል የቀረበውን የውል ሰነድ ይጠቅመኛል ተስማምቼበታለሁ ብሎ ፈቃዱን የገለጠበት ነው ዘፃ 19÷3-8፡፡ ይህንን ውል ሁለቱም አካላት በፈቃደኝነት ከተስማሙበት በኋላ ለሁለቱም አካላት አስገዳጅነት ያለው ሕግ ይሆንባቸዋል፡፡

የቃል-ኪዳኑ /የስምምነቱ/ ውልም አስገዳጅነቱ የሚፀናው በውል አቅራቢውና በውል ተቀባዩ መካከል ብቻ ነው፡፡በአንጻሩ በውሉ አማካኝነት የሚገኘው ጥቅም ለሦስተኛ ወገኖች /አካላት/ ጠቀሜታን አይሰጥም /ኢትዮጵያን ጨምሮ/ በቃል ኪዳኑ ታቦት የተደረገውን የውል ስምምነትም ስናጠና ውል አቅቢቢው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሲሆን፣ የውል ተቀባዮቹ ደግሞ የእስራኤል ነገድ ብቻ ናቸው፡፡ እናም በቃል ኪዳኑ ታቦት አማካኝነት ከሚመጣው ግዬታም ሆነ ጠቀሚታ እንዲሁም በረከትና መርገም የሚያስገድዳቸው እስራኤላውያንን ብቻ ነበር፡፡ እግዚብሔርና እስራኤል በተስማሙበት የቃል-ኪዳን ታቦት መካከል ሦስተኛ ወገን ጣልቃ ሲገባ በቃል ኪዳኑ አማካኝነት ከሚመጣው በረከትና ጥቅም ተካፋይ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

በአንጻሩ በማይመለከተው የውል ሰነድ ጣልቃ በመግባት በምርኮም ይሁን በስርቆት ቢወስድ የእግዚብሔር የቁጣ እሳት በሦስተኛው ወገን /አካል/ ላይ ይነድበታል፡፡ ለዚህም

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጅት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

በፍልስጤማውያን ከተሞች የወረዱትን አምስቱን መቅሰፍቶች መመልከት በቂ ይሆናል 1ኛ ሳሙ 5 እና 1ኛ ሳሙ 6። በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደምንረዳው ምንም እንኳን የቃል ኪዳኑ ታቦት የተማረከችው በእስራኤላውያን ኃጢአት ቢሆንም ቅሉ ፍልስጤማውያን የማይመለከታቸውን የቃል-ኪዳን ውል በመውሰዳቸው የበረከቱ ሳይሆን የመቅሰፍቱ ተካፋይ ለመሆን በቅተዋል።

2.2. ክህነት ሐዲስ ኪዳን

የሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት የተጀመረው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ መስዋዕተ ኦሪትን ሽሮ መሥዋዕተ ሐዲስን ሰውቶ የሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎትን ባርኮ ቀድሶ ሰጥቶናል። የሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት በጥምቀት እና በሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት በሥጋ ወደሙ መሰጠት በምሴተ ሐሙስ ቢጀመርም ሥልጣነ ክህነት ግን ከጌታ ትንሳኤ በኋላ በአራተኛው ሳምንት በርክበ ካህናት ነው የተሰጠው። "ወዘንተ ብሂሎ ነፍኅ ላዕሌሆሙ ወይቤሎሙ ንሥኡ መንፈስ ቅዱስ ለእለ ኀደግሙ ኀጢአተ ይትኀደግ ሎሙ ወለእለሰ ኢኀደግሙ ኢይትኀደግ ሎሙ" "ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ኀጢያታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው" ዮሐ 20÷22-23። በዚህ ዕለት የሐዲስ ኪዳን ሥልጣነ ክህነትን ሰጣቸው።

2.2.1. ክህነት በሐዲስ ኪዳን

በቤተ ክርስቲያን የምሥጢረ ክህነት ትምህርት ካህን ማለት መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ዲያቆን ፣ ቄስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ (ጳጳስ) ማለት ነው። ክብረ ክህነት ስንልም ካህናት ፣ ምእመናንና ሌሎች አካላት ለካህናትና ለክህነት ሊኖራቸው የሚገባውን ክብር የሚመለከት ነው።

2.2.2. የሐዲስ ኪዳን ካህን ለመሆን የሚያስፈልጉ መሥፈርቶች

- ቅዱሳን ከእግዚአብሔር በተቀበሏት ቀጥተኛ በሆነችው አንዲት ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ማመን ፣
- መሠረታዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ማወቅ ፣ወፈድፋደስ አርባዕተ ወንጌላት (ፍ/ነ/ አንቀጽ ፮) ፤
- በውስጥ በአፍአ ፣ በነፍስ በሥጋ የሚያስነቅፍ የምግባር ጉድለት የሌለበት ሆኖ መገኘት፣
- ለቤተ ክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት ብቁ የሆነ ዕውቀት ያለው ፣
- ክህነትን ለምድራዊ ጥቅም ለማዋል የማይደራደር ፣
- ታጋሽ ፣ ቅን ፣ ትሑት ፣ መንፈሳዊ ሰብእናን የተላበሰ መሆን አለበት። ቲቶ.፩÷፭ -፰ ፣ ፩ጢሞ. ፫÷፩ -፯

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

2.2.3. ለክህነት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ለቅስና የሚመረጥ ዲያቆን ነውርና ነቀፋ የሌለበት፣በድንግልና የመነኮሰ ወይም አንዲት ድንግል ሴት ያገባ፣አብዝቶ የማይጠጣ፣ገንዘብ የማይወድ፣እንግዳን መቀበል የሚወድ በጎ ሥራን የሚያፋጥን፣ ከኃጢያት የነጻ፣ ደግና ቸር የሆነ፣ ሰውነቱን ከፍቶት የገታ፣ ወንጌልን በማስተማር ምዕመናንን የሚረዳ፣ መናፍቃንን በወንጌል ተከራክሮ የሚረታ መሆን አለበት (ፍት.ነገ አንቀጽ 7 ክፍል 1 ዘሌዋ 21÷7-16)። ዕድሜው ፴ ዓመት ያልሞላው፣ብሉያትን ሐዲሳትን ያልተማረ ይልቁንም ወንጌልን ያላወቀ፣ለቅስና ማዕረግ መብቃቱ ያልተመሰከረለት ክህነተ ቅስና አይሾምም (ፍት.ነገ አንቀጽ ፮) 1ኛ ጢሞ 3፡1 የማይነቀፍ የአንዲት ሚስት ባል ልከኛ ራሱን የሚገዛ እንደሚገባው የሚሰራ እንግዳ ተቀባይ ለማስተማር የሚበቃ የማይሰክር የማይጨቃጨቅ መሆን ይገባል። በዚህ ፈንታ ገር የማይከራከር ገንዘብ የማይወድ

❖ **የማይነቀፍ፡**

ካህን ሌላውን የሚጠብቅ ስለሆነ በቅድሚያ የራሱን ማንነት መቆጣጠር ይገባዋል። ዓለምን በሙሉ ከመግባት እራስን መቆጣጠር ይከብዳልና፣ በማንኛውም ጊዜሁሉ የሚያስነቅፈው ስራ ከመስራት የራቀ የታቀበ ቢሆን መልካም ነው፤

❖ **የአንዲት ሚስት ባል፡-**

እንዲሆን በሕግ ተፈቅዷል፤ ጋብቻ ቅዱስ ነው፤ ቅዱሳንን የሚያስገኝ ነው፤ እግዚአብሔር በጥንተ ፍጥረት የወሰነው ነው፤ ለአዳም ለሔዋን በመፍጠሩ፤ እንግዲህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገው ሰው ሊለየው አይችልም/ማቴ. ፲፱፡፫-፱፣ ዘፍ.፩፡፳፯፣ ዘፍ.፪፡፳፬/።

❖ **እንግዳ ተቀባይ፡-**

ካህን እንደነ አብርሃም፤ ሎጥ እንግዳ ተቀባይ ቢሆን ለመግቦት ስራው አመቺ ይሆንለታል /ዘፍ. ፲፰፡፩

❖ **ለማስተማር የሚበቃ፡-**

የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ምዕመናን የሚያስተምር የሚመራ ካህን የማስተማርና የመምራት ችለታው ከሚያስተምራቸውና ከሚመራቸው ሚስቱና ልጆቹ ላቅ ያለ እንዲሆን ያስፈልጋል፡ ያለዚያማ ማለት በቤቱ ያሉትን ሚስቱና ልጆቹን መምራትና ማስተማር

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ካልቻለ የነፍስ ልጆቹን እንዴት ሊመራና ሊያስተምር ይችላል። የነፍስ ልጆቹ በእውቀት ከእሱ የበለጡ ከሆኑ የዚያ ካህን ተልእኮ አይሰምርም፡፡ *“ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል፡፡”* ፩ ጢሞ. ፫ ፡፭ -፶/።

2.2.4. የሐዲስ ኪዳን የክህነት ደረጃዎች

የሐዲስ ኪዳን ዋና ዋና የክህነት ደረጃዎች ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም ጵጵስና ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ ፣ሊቀ ጳጳስና ፓትርያርክ የሚባሉ የሹመት ደረጃዎች አለ፡፡ እንደየማዕረጉ ሥርዓተ ሢመትና ጸሎት አለው፡፡ ፓትርያርክ (ሊቃነ ጳጳሳት) ቤተክርስቲንን ለመጠበቅ ክርስቶስ የሾማቸው የቅዱሳን ሐዋርያት ተከታዮች ናቸው የሐዋ.ሥራ 20÷28፡፡ ከሦስቱ በደረጃ በታች ደግሞ ንፍቅ ፡ አናጉንጢስ ፣ አጻዌ ኖህትና አንባቢ የመሳሰሉት አሉ፡፡ ከላይም ከታችም ያሉት ለሥራ ክፍፍል የተደረጉ እንጂ በክህነት ደረጃ ውስጥ የሚቆጠሩ አይደለም፡፡ እያንዳንዳቸው አንዱ በአንዱ የማይገባበት የራሱ የሆነ ሥላጣንና ኀላፊነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ፓትሪያርክ (ርእሰ ሊቀነ ጳጳሳት) ያወገዘውን ሊቀ ጳጳስ፣ሊቀ ጳጳስ ያወገዘውን ጳጳስ ፣ ጳጳስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ፣ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ቄስ በሕይወት ሳለም ከሞተም በኋላ አይፈታውም፡፡ ቄስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ ፣ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ጳጳስ፣፣ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳስ፣ሊቀ ጳጳስ ያወገዘውን ፓትሪያርክ (ርእሰ ሊቀነ ጳጳሳት) በሕይወት ሳለም ከሞተም በኋላ ይፈተዋል፡፡ ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ሌላ ሊቀ ጳጳሰሳት፣ ጳጳስ ያወገዘውን ሌላ ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ሌላ ኤጲስ ቆጶስ፣ቄስ ያወገዘውን ሌላ ቄስ አውጋዡ በሕይወት ሳለ አይፈታውም፣ነገር ግን አውጋዡ ከሞተ በኋላ መፍታት ይችላላ (ይፈታዋል)፡፡

2.2.5. የሐዲስ ኪዳን ካህናት ተግባር

- **እግዚአብሔርን ማገልግል፡-** ካህናት እንደመላእክት ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት ለአግልግሎት ይቆማሉ፡፡ይህም በማህሌቱ ፣በሰዓታቱ እና በመሳሰሉት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና ነው፡፡
- **ሰውን ማገለገል፡-** ካህናት በወንጌል መረብነት እያስተማሩና እያጠመቁ ደቀ መዛሙርት ከማድረግ ባሻግር ማጥመቅ፣ ማቁረብ ፣ መባረክ እና መናዘዝ የመሳሰሉትን ተግባራት ይተገብራሉ፡፡ ካህናት ጠቅለል ባለ መለኩ ከላይ በተገለጸው መለኩ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ከዚህ በታች ዘርዘር አድረገን እንየው፡፡

2.2.5.1. ካህን በግል ቤቱ

ካህን በግል ቤቱ ውስጥ የሚተግበረው ኃላፊነቱን በሦስት ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

ሀ. እራሱ

ለ. ሚስቱ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ሐ. ልጆቹ

❖ ካህን ራሱ

አንድ አማኝ ካህን ለመሆን የሚያስፈልገው መስፈርት (1ኛ ጢሞ 3፣1-5) የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ልከኛ፣ራሱን የሚገዛ፣እንደሚገባው የሚሠራ፣እንግዳ ተቀባይ ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣የማይሰክር፣የማይጨቃጨቅ፣ገር ፣የማይከራከር ፣ገንዘብን የማይወድ ፣ ልጆቹን በጭምትነት የሚያሳድግ እና ቤቱን በመልካም የሚያስተዳድር እንዲሁም ሌላውን የሚጠብቅ ኖላዊ በቅድሚያ የራሱን ማንነት መቆጣጠር ይገባዋል። የካህኑን ክፉ ስራ አይተው ምእመናን እንዳይበረግጉ የሃይማኖት ተቃዋሚዎች ሃይማኖትን የሚያጥላሉበት መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኙ ካህኑ ከክፉ ሥራ የራቀ መሆን ይኖርበታል። ካህን የአንዲት ሚስት ባል እንዲሆን በሕግ ተፈቅዷል። ጋብቻ ቅዱስ ነው። ቅዱሳንን የሚያስገኝ ነውና ቅዱስ ተብሎ ይጠራል። ማቴ 19፣3፤ ዘፍ 2፣24ለጋብቻ ቅድስና ምስክር ስለሆነ ካህኑ ባለ አንድ ሚስት ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የአንድ ወንድ ለአንድ ሴት ጋብቻ የክርስቶስና የቤተክርስቲያን ተዋሕዶ ምሳሌ ስለሆነ የሃይማኖትም ጠባይ አለው። ኤፌ 5፣28 በአንድ ሚስት በሕግ መኖር፤ በአንድ አምላክ የማመን፤ በብዙ ሚስት በብዙ ባል መኖር ደግሞ የአምልኮ ጣኦት ምሳሌ ነው።ካህኑ ይህን አስተማሪ ነውና በአንድ ሚስት ብቻ የተወሰነ ይሆናል። ካህን በኑሮው ሁሉ ልክ መጠን ያለው ነው። ላነጋገሩም ለአበላሉም ለአጠጣጡም መጠን ያለው እንደሆነ ሁሉ ይፈልገዋል። ሁሉ ይወደዋል። ቢናገርም በጥሞና ሁሉ ያዳምጠዋል። ራስን መግዛት ለካህን በጣም አስፈላጊ ነው። ለሕይወቱ ልክ መጠን የሌለው ከሆነ መንጋውን ያስደነብራል። ራስን ካለመግዛት የተነሳ ብዙ ስህተቶችን ይፈጽማል። ሊሰራው የሚገባውን የሚያውቅ ማለት ስጦታውን የሚያውቅ ማለት ነው። የካህን ሥራው ምእመናንን መጠበቅ መመገብ ስለሆነ በእግዚአብሔር በተሰጠው ጸጋ መጠን አንጂ ማን ከማን ያንሳል በሚል የሚሰራ ከሆነ ውጤት አይኖረውም። ካህን እንደ አብርሃም እንደ ሎጥ እንግዳ ተቀባይ ቢሆን ለመግቦት ሥራው አመቺ ይሆነዋል። ማቴ 25፣ 35 ምእመናንን የሚያስተምርና የሚመራ ካህን በይበልጥ ሚስቱንና ልጆቹን የሚመክርና በመልካም የሚመራ መሆን ይኖርበታል። በቤቱ ያሉትን ሚስቱንና ልጆቹን ማስተማርና መምራት ያልቻለ ካህን እንዴት ምእመናንን ሊመራና ሊያስተምር ይችላል። ለካህን ‹‹ከመጠምጠም መማር ይቅደም›› እንደሚባለው አገልግሎቱ እንዲሰምር መማር ግዴታው ነው፡ ፡ቁስ ከነስሙ መምሬ ማለትም አስተማሪዬ ማለት ስለሆነ የማስተማር ችሎታ እንዲኖረው ይገባል። የካህንን መግቦትና ትምህርት ከሚያዋርዱት ምክንያቶች አንዱ ስካር ነው። ስካርን አባቶች ‹‹ የፈቃድ እብደት›› ይሉታል። ስካር ትልቁን ትንሽ የሚያደርግ የተከበረውን የሚያዋርድ የሰው ልጅ ጠላት ነው። ምሳሌ ኖህ - ዘፍ 9፣20 ፤ ሎጥ - ዘፍ 19፣31 ስካር ከሰው ያጣላል። ከእግዚአብሔር ይለያያል። ጤናንም ያውካል። የስካር ሕይወት ጤንነት የጎደለው ነውና ካህን የማይሰክር መሆን ይገባዋል።ካህን ጨርሶ አይጠጣ ማለት አይደለም። ቢተው መልካም ነው። መጠጣት ከፈለገ ይጠጣ ፤ ነገር ግን ከመጠን አይለፍ። ራሱን የገዛ ካህን በመጠጥ አይሸነፍም። ካህን በቤቱ ከሚስቱ ከልጆቹ ጋርም ቢሆን በማናቸውም ምክንያት ከሰው ጋር ቢሆን የጨቅጫቃነት ጠባይ እንዲኖረው አይገባም። ጨቅጫቃነት ያሰለቻል።

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ያሰቅቃል። ያስንቃል፤ ልማደኛ ያስብላል። ካህን እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት በማለት የሚያስረዳ መመሪያና ሥርዓትን ሰጥቶ የሚመራ እንጂ በዘፈቀደ የሚንዝ አይደለም። ካህን ራሱ ቅን ገር መሆን ይገባዋል። የማያግባባ ነገር ቢገጥመው ሳይውል ሳያድር እርቅ የሚያወርድ እንጂ ቂመኛ መሆን የለበትም። ክርስቶስ ሲሰድቡት አንዳልተሳደበ ሲደበድቡት እንዳልተቀየመ ተከታዮቹ ካህናትም እርስ በእርስም ሆነ ከሌላውም ጋር ጋር ዕለታዊ ግጭት ቢያጋጥማቸው ቂምና በቀልን በልቦናቸው ማስገባት አይገባቸውም። በሆነው ባልሆነው ክርክር የሚወድ ኖላዊ ሊሆን አይገባም። ሃይማኖትን ለማስረዳት ከመናፍቃን ጋር መከራከር ተግባሩ ነው። በየዘመናቱ ሊቃውንት ከመናፍቃን ጋር ተከራክረዋል። ሐዋ 8፣18፤ ማቴ 19፣1 ካህኑ አንቀጽ አውጥቶ መጽሐፍ አልቦ ነቅቶ ተግቶ ተዘጋጅቶ በጎቹን የሚጠብቅ የመናፍቃንን ትምህርት በጠረን የሚያውቅ ቢሆን መልካም ነው።የኃጢአት ምንጩ ገንዘብን መውደድ ነውና ካህናት ገንዘብን የሚወዱ መሆን አይገባቸውም። ገንዘብን የሚወድ ለእግዚአብሔር መገዛት አይችልምና። 1ኛ ጢሞ 6፣10፤ ማቴ 6፣24 ካህን የእግዚአብሔር ተወካይ መልእክተኛ ነውና ለበጎቹ ምእመናን እውነትን ያስተምራል። ላንደበቱም ሐሰትን አያስለምድም። ሐሰትን የሚናገር ካህን በምእመናን ዘንድ ያለው ታማኝነት ይጠፋል። ምእመናንም አያምኑትም።

❖ የካህን ሚስቱ

የካህኑ ሚስት እንደ ካህኑ ክብሯን የጠበቀችና የታፈረች፣ ቤተክርስቲያን አብራ ከካህኑ ጋር የምትሄድ፣ በቤተ ክርስቲያን ሥነ ስርዓትን የምታስከብር፣ በቤቷም ልጆቿን ቀጥታየምታሳድግ፣ለጎረቤቶቿ ጥሩ ምሳሌነት ያላት፤ ጎረቤቶቿን የምትመክር፣ መሰረተ እምነትን የምታስተምር እና የተጣሉትን የምታስታርቅ ብትሆን የካህኑም ተልእኮና ትምህርቱ በይበልጥ ተቀባይነት ይኖረዋል። ካህኑ የኖላዊነቱን ሥራ ከቤት መጀመር ይኖርበታል። ምእመናን ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ የካህኑ ሚስት ቡና አፍልታ የምታንቃርር ከሆነ የዚህ ካህን ኖላዊነት ተቀባይ ያጣል። ኖላዊነቱን ከቤት ስላልጀመረ ትምህርቱንም እሱንም ይንቁታል። ካህኑ አምልኮ ጣኦትን ሲያወግዝ የእርሱ ባለቤት ወደ ጠንቋይ የምትሄድ ከሆነ፤ ካህኑ መስቀል ጨብጦ የምእመናንን ቤት ሲባርክ ባለቤቱ አላፊ አግዳሚውን የምትሳደብ ከሆነ ለኖላዊነት ተልእኮው እንቅፋት ትሆንበታለች።

❖ የካህኑ ልጆች

ተሰርተው ተቀጥተው ያደጉ፣በጎረቤትም የተመሰገኑና ጥሩ ምሳሌነት ያላቸው፣ ከካህኑ ጋር አብረው የቤተክርስቲያንን አገልግሎት የሚረዱ ፣ ታላላቆቻቸውን የሚያከብሩ ግብረ ገብነት ያላቸው ከሆኑ የካህኑ የኖላዊነት አገልግሎት ተቀባይነት ይኖረዋል። የካህኑ ልጆች ጠብና ክርክር መደባደብ የማይሰማባቸው ትእግስትና ትህትና የተላበሱ መሆን ይገባቸዋል። ይህ ካልሆነ ልጆቹ ለካህኑ የኖላዊነት አገልግሎት እንቅፋት ይሆናሉ። ይህም ካህኑ በምእመናን ዘንድ ያለውን ተቀባይነት አንዲቀንስ ጨርሶም እንዲጠፋ ያደርጋል።

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

2.2.5.2. ካህን በቤተክርስቲያን

ካህን በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን አገልግሎት ለ3 ከፍሎ ማየት ይቻላል

1ኛ. በቅዳሴ

2ኛ. በጸሎት

3ኛ. በማስተማር

ካህን የኖላዊነት ሥራ የሚሠራበት ዋነኛ ቦታ ቤተክርስቲያን ናት። ቤተክርስቲያን ለካህኑ

- ✓ ጥብርያዶስ ናት - ለምእመናን ስጋውን ደሙን የሚመግብባት
- ✓ የኢያኢሮስ ቤት ናት - ምእመናንን ከሞተ ኃጢአት እጃቸውን ይዞ የሚያነሳባት
- ✓ የዘኬዎስ እልፍኝ ናት - የኃጥአን ልጆቹን ኑዛዜ የሚሰማባት
- ✓ የሠርግ ቤት ናት - ምእመናን የተጋበዙባት
- ✓ ቀራንዮ ናት - የህይወት ዛፍ መስቀል የተተከለባት
- ✓ ፈለገ ሕይወት ናት - የሕይወት ውሃ የሚፈስባት

2.2.5.2.1. የካህኑ አገልግሎት በቤተክርስቲያን - በቅዳሴ ጊዜ

በቅዳሴ ጊዜ (ምሥጢረ ቁርባን የሚፈጸምበትን ሰዓት) አባታቸው ካህኑ ሲቀድስ ምእመናን ልጆቹ ተሳታፊዎች ይሆናሉ። ቅዳሴ ሰውና እግዚአብሔር ፣ ሰውና ሰው እንዲሁም ሰውና ስነ-ፍጥረት የተገኙበት የሚገናኙበት ምስጢር ነው። ይህም የሚሆነው **ሰውና እግዚአብሔር** - የእርሱን ስጋ በልተን ጠጥተን ከሱ ጋር እንዋሃዳለንና ነው።**ሰውና ሰው** - የጸታና የዘር ልዩነት ሳይኖር ከአንድ ማዕድ በልተን ከአንድ ጽዋ ጠጥተን የአንድ የሕይወት ዛፍ ተካፋዮች የአንድ እግዚአብሔር ልጆች ወንድማማቾች እንሆናለንና ነው። **ሰውና ስነ-ፍጥረት** ወይኑም መገበሪያውም ከማሳችን በቅሎ በእግዚአብሔር ፈቃድ አፍርቶ በካህኑ እጅ ተባርኮ የአምላካችን ቅዱስ ሥጋ ክቡር ደም ሆኖ ምእመናንም ያንን ተመግበው የዘለዓለም ሕይወት ያገኙበት ስለሆነ ነው። በቅዳሴ ሰዓት ካህኑ ለምእመናን የሚያስተላልፈው መልዕክት ተግተው እንዲከታተሉ፣ ሃሳባቸው እንዳይበታተን ካህኑ አበክሮ ያስጠነቅቃቸዋል። በመርዓዊ ክርስቶስ ማኅተም የታተመ ምእመን ካህኑ ለእርሱ ስርየት በሚለምንበት ጊዜ የካህኑን ቃል መስማት ይገባዋል።ካህኑ የቤተክርስቲያኑን አራቱንም ማእዘናት ባርኮ ልብሰ ተክህኖውን ባርኮ ይለብሳል። በቅዳሴ ጊዜ የሚጠቀምባቸውን ንዋያተ ቅድሳት ይባርካል። ምክንያቱም ለምእመናን ሕይወት የሚሆን የክርስቶስ ስጋና ደም የሚቀርብባቸው ንዋያተ ቅድሳት ናቸውና። ዕጣኑን ባርኮ ‹‹ የሕዝብህን ሁሉ ኃጢአት ይቅር በል›› እያለ ሲፀልይ ለአባታዕ ምእመናን አማላጅ ሆኖ ይታያል። ካህኑ በመቅደሱ መድረክ ወጣ ብሎ ምእመናንን ይባርካል። ምእመናን የንጽህና፣

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

የበረከት ማደሪያ እንዲሆኑ ደጋግሞ ይጸልይላቸዋል። በሕይወት ላሉት ብቻ ሳይሆን ለሙታንም ይጸልያል።በቅዳሴ የተሰበሰቡት ምእመናን ልባቸው አንዳይበተን አልፎ አልፎ ሰላም ለእናንተ ይሁን ይላቸዋል። በመካከላቸውም እየተመላለሰ ያጥናቸዋል። እነርሱም ከእሱ መንፈስ ጋር መሆናቸውን ያረጋግጡለታል። ካህኑ በሥርዓተ ቅዳሴው በሚያደርገው ጸሎትና አስተብቁዖት ሁሉ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ የምልጃ ሥራውን ያከናውናል። ምእመናን በጎቹ ለዘለዓለም በእግዚአብሔር መንግስት እንዲመዘገቡ በእግዚአብሔር ፍቅር እንዲጠበቁ ለእግዚአብሔር አደራ ይላል። ሥጋውን ደሙን ይመግባቸዋል። ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ያካፍላቸዋል። ሥጋውን ደሙን ከተቀበሉ በኋላ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን ብሎ ይባርካቸዋል። እነርሱም አሜን እኛ ባሮቹን በሰላም ይባርከን የተቀበልነው ሥጋና ደም ለሥርየት ይሁነን፤ የሰይጣንን ኃይልም ድል እንድናደርግ ሥልጣን ይሰጠን፤ ምህረትን የተመላች የቅድስት እጅህን በረከት ሁል ጊዜ ተስፋ እናደርጋታለን፤ ከክፉ ሥራ ሁሉ አርቀን ወደ መልካሙ ሥራ መድበን ሥጋውንና ደሙን የሰጠን አምላካችን የተባረከ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ኃይል ጸጋን ለበሰን ሕይወትንም አገኘን እያሉ የምስጋና መዝሙር ይዘምራሉ። በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሰረት የምእመናን (የአባግዕ) ና የካህኑ (ኖላዊ) ግንኙነት በቅዳሴ ጊዜ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል።

2.2.5.2.2. የካህኑ አገልግሎት በቤተክርስቲያን - በጸሎት ጊዜ

ምዕመናን (አባግዕ) ሥርዓተ ጸሎትን ካባታቸው ከካህኑ ይማራሉ። ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ስለሆነ ተግተው እንዲጸልዩ ይመክራቸዋል። ጸሎት በችግር ጊዜ ብቻ ሳይሆን በደስታም ጊዜ በዘወትር መጸለይ የሚገባ መሆኑን ያስተምራቸዋል። ጸሎት በሕይወት ላሉት ብቻም ሳይሆን ለሞቱትም እንዲጸልዩ ካህኑ መመሪያ ይሰጣቸዋል። በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሰረት የጸሎት ቦታ ቤተክርስቲያን ናት። ሥራ የሚበዛባቸው ምእመናን ግን በቤታቸው ጸሎት እንዲያደርሱ ያደርጋል። በሰላም ላሳደራቸው ለእግዚአብሔር ምስጋናን ያቀርባሉ ሥራቸውንም እንዲያከናውንላቸው ይለምናሉ። በማታም በደህና ስለዋሉ ምስጋናን ያቀርባሉ በሰላም እንዲያሳድራቸውም ይለምናሉ እግዚአብሔር ካልባረከው ቀኑም ይሁን ሌሊቱ ከባድ ነውና። በማህበር በቤተክርስቲያን በሚሰባሰቡበት ወቅት ሰፋ ያለ የጸሎት ጊዜ በካህኑ መሪነት ይኖራቸዋል። የቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ ሥራ እንዲቃና ይለምናሉ። ስለ ክርስቲያኖች አንድነት፣ አጋንንት እንዳይሰለጥኑባቸው፣ እንዳይከፋፍሏቸው ከወንድሞቻቸውና ከእህቶቻቸው እንዳይለያያቸው ይጸልያሉ። ምእመናን በጸሎታቸው የነቢያትን የሐዋርያትን የመላእክትን የቅዱሳንን ስም እያስታወሱ ‹‹ ስለ ወዳጅህ ስለ እገሌ ብለህ ማረን›› እያሉ እንዲጸልዩ ያስተምራቸዋል። ስለ ቤተክርስቲያን መሪዎች፣ ስለ ሕዝቡ፣ ስለ ሀገራቸው፣ ስለ መሪዎች ሁሉ፣ በባህር በየብስ በአየር ስለሚጓዙ፣ ስለተራቡ ስለተጠሙ፣ስለታመሙ፣ ስለተማረኩ ስለምድር ፍሬ በካህኑ መሪነት ይጸልያሉ። በቤተክርስቲያን የሚከናወን ጸሎት መሪ የሚሆነው ካህኑ ነው። በጸሎት ጊዜ የምእመናን የመቆሚያ ቦታ የተለየ ሆኖ መዘጋጀት አለበት። ሁሉም በጋራ በአንድነት ለጸሎት መትጋት ይገባዋል። በካህናት መካከል የተለያዩ ሁኔታዎች በጸሎት ጊዜ መታየት አይገባውም።ምእመናን (አባግዕ) በጸሎት ጊዜ በተለይም

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

በዕለተ ሰንበት ወደ ቤተክርስቲያን መሄድን ቢያስታጉሉ ካህኑ ፈልጎ ማምጣት ይጠበቅበታል። በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ከሌላቸው በቀኖና ይቀጣቸዋል።

2.2.5.2.3. የካህኑ አገልግሎት በቤተክርስቲያን - በትምህርት ጊዜ

ካህኑ በቤተክርስቲያን ምእመናንን **ቀድሶ ያቆርባቸዋል**። በጸሎት በምህላ መሪ ሆኖ **ሥርዓተ ጸሎትን ያስተምራቸዋል**። በወንጌል ትምህርት **ሕይወታቸውን ያበራላቸዋል**። እነዚህ ሦስቱ ካህኑ በጎቹን እንዲያውቅ የሚያደርጉት በጎቹም የጠባቂያቸውን የካህኑን ጥቅም እንዲያውቁ ትዝታን የሚያሳድሩባቸው የግንኙነት መለኪያዎች ናቸው። ካህን ተብሎ ተሹሞ የማያስተምር ወዮታ አለበት። ‹‹ ወንጌልን ብሰብክ እንኳ የምመካበት የለኝም፤ ግድ ደርሶብኝ ነውና ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ።›› 1ኛ ቆሮ 9፣16 ካህኑ ስብከት (ትምህርት) በሁለት ዓይነት መንገድ የሚከወን ይሆናል።

❖ ለአማንያን የሚሆን ትምህርት

የማነጽ፣ የማንጻት፣ የማጽናት ትምህርት ይባላል።በያዙት ሃይማኖት በተማሩት ትምህርት በምግባርና ትሩፋት ጸንተው ከክብር ወደ ክብር ከትሩፋት ወደ ትሩፋት አንዲራመዱ ወኔ የሚሰጥ ትምህርት ነው። ካህኑ ለመእምመናን (አባግዕ) ፍቅረ እግዚአብሔርን ፍቅረ ቢጽን ያስተምራቸዋል። ወደ ሥጋውና ደሙ የሚቀርቡ ናቸውና የንስሀ ትምህርትም ያስተምራቸዋል፡ ፡ ካህኑ ለጋብቻ የደረሱትንና እና በጋብቻ ለመኖር የወሰኑትን የቅድመ ጋብቻ ትምህርት መስጠት ይገበዋል።

❖ ለማያምኑ አሕዛብ የሚሆን ትምህርት

ከባእድ አምልኮ፣ ካለማመን ወደ ሃይማኖት ለመመለስ የሚሰጥ ትምህርት ነው። የመዘጋጃ የመመርመሪያና የማወቂያ ትምህርት ይባላል። ‹‹ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፤ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።›› 1ኛ ጢሞ 4፣16 ካህኑ ትምህርቱ ተቀባይነት እንዲኖረው የማስተማር ስልትን ማወቅ ይገባዋል። በርእስ አመራረጥ፣ በቃል አመራረጥና ለስብከት አስፈላጊ የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማጥናት አስፈላጊ ይሆናል።በቤተክርስቲያናችን ቅዳሴ፣ ጸሎትና ትምህርት አይለያዩም አንዱ ከሌላው ተለይቶ ትርጉም አይኖረውም። ቅዳሴውም እራሱ የትምህርት ክፍል አለው። የምእመናን (አባግዕ) ሕይወት የሚለመልመው የሚያብበውና ትሩፋትን አፍርቶ የሚገኘው በውሃ መፋሰሻ ላይ እንደ ተተከለች ተክል ዘወትር የእግዚአብሔር ቃል ሲመገብ ነው።

2.2.5.3. ካህን በምእመናን ቤት (በነፍስ ልጆቹ ቤት)

ካህን በምእመናን ቤት በሚሰጠው አገልግሎት የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች አንጻር በሦስት ክፍሎች ለይቶ ማየት ይቻላል።

ሀ) ከወላጆች ጋር

ለ) ከልጆች ጋር

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ሐ) ከቤት ሠራተኞች

ለክርስትና ሃይማኖት ማእከሉ ‹‹ የጠፋን መፈለግ›› ነው፡፡ ስለዚህም ካህኑ ምእመናንን በየቤታቸው እየሄደ ይጠይቃል፡፡ ቤታቸውንም ጠበል ይረጫል፡፡የካህኑ የቤት ለቤት አገልግሎት በይበልጥ ቤት ለዋሉ ምእመናን የመንፈስ ጥንካሬን ይሰጣቸዋል፡፡ በቤት ጉብኝት ወቅት ካህኑ አገልግሎቱን ለሁሉም ይሰጣል፡፡ እንደየቤቱ አቅም በምእመናን የተዘጋጀውን መስተንግዶ ምእመናን እንዳይከፋቸው ይሳተፋል፡፡ የካህኑ አገልግሎት በቤት ውስጥ ጠበል በመርጨት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የምእመናንን ሕይወት በሚመለከትም ውይይት ያደርጋል፡፡ ከቤት ባለቤቶች (ከወላጆች) ጋር ስለ ሥራቸው ይወያያል፤ ችግር ቢገጥማቸው ምክር ይሰጣቸዋል፡፡ በሥራቸው ሁሉ ከክርስቲያናዊ ሕይወት እንዳይወጡ ያስተምራቸዋል፡፡ በቤተሰብ ደረጃ ባልና ሚስት ተፈቃቅረው እንዲኖሩ ፤ችግርም ቢፈጠር በመመካከር እንዲፈቱ እንጂ ጋብቻቸውን እንዳያፈርሱ አጥብቆ ምክር ይሰጣቸዋል፡፡ (ኤፌ 5፣22፣ቆላ 3፣18፤ 1ኛ ጢሞ 2፣9፤ ዘፍ 18፣ 22) ልጆቻቸውን በክርስቲያናዊ ስነ ምግባር እንዲያሳድጉ ምክር ይሰጣቸዋል፡፡ በአግባቡ ባያሳድጉ ከእግዚአብሔር ቅጣት እንደሚያመጣ ያስተምራቸዋል፡፡ ቆላ 3፣21 ልጅን አግባብ በሆነ ሁኔታ መልካም ነገርን ብቻ በማሳየት እንዲያስተምሩና እንዲያሳድጉ ይመክራቸዋል፡፡ የቤት ሠራተኞቻቸውን መብት እንዲያከብሩ በእነርሱም ላይ ግፍ አንዳይፈጽሙ ቢፈጽሙ ደግሞ ግፍን የሚጠላ እግዚአብሔር የሚበቀላቸው መሆኑን ማስተማር የካህኑ ተግባር ነው፡፡ ኤፌ 6፣9፤ ቆላ 4፣1 ከጎረቤቶቻቸው ጋር በፍቅር በሰላም እንዲኖሩ እንጂ ጠብ ክርክር እንዳይሰማባቸው ዘወትር አደራ ሊላቸው ይገባዋል፡፡ 1ኛ ቆሮ 6፣1፤ ማቴ 18፣17 ምእመናን በየትኛውም ስፍራ ታማኞች እንዲሆኑ ማስተማር ይኖርበታል፡፡ ጉቦ እንዳይቀበሉ፣ ነጋዴዎች ቢሆኑ በስራቸው ታማኞች እንዲሆኑ ማስተማር የካህኑ ኃላፊነት ነው፡፡ ከሚያገኙት አስራትን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ማስተማር ይገባዋል፡፡ ደመወዝተኞች ከአስር አንድ፣ገበሬዎች ቀዳምያትን ማለት ከአዝመራቸው መጀመሪያ ከደረሰው በእንቅብ ወይም በስልቻ፣ ከብት አርቢዎች ቢሆኑ መጀመሪያ የተወለደውን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ በስጦታቸውም በረከትን ከእግዚአብሔር እንደሚቀበሉ ማስተማር ይገባዋል፡፡ ሥርዓተ ኖሎትን የተማሩ ካህናት በምእመናን ቤት ወላጆችን ብቻ ሳይሆን ልጆችንም ማስተማር ይገባቸዋል፡፡ በዕድሜ ደረጃቸው ያጋጠማቸውን ችግር ጠይቀው መፍትሔ መስጠት ይገባቸዋል፡፡ ልጆችን በመጠናቸው የሚያስፈልጋቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እና የሥነ ምግባር ትምህርት መስጠት አንዱ የኖላዊነት ተግባር ነው፡፡ በኖላዊነት ትምህርት ላይ ካህኑ ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባው በሀብታምና በድሃ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል ልዩነት እንዳያደርግ ነው፡፡ ካህኑ በጉብኝት ጊዜ የቤት ሠራተኞችን ማነጋገር በሥራቸው ትጉህ አንዲሆኑ ማበረታታት ይገባዋል፡፡ በአባወራውና በሰራተኞች መካከል አለመግባባት ከተፈጠረም መፍታት ማስታረቅ የካህኑ ተግባር ነው፡፡ ካህኑ በቤቱ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉ የጋራ አባት ነውና ሁሉንም በጋራ ማስተማር ይገባዋል፡፡ ካህኑ ወደ ምእመናን ቤት ከመሄዱ በፊት የሚገኙበትን ጊዜ አረጋግጦ የሚያስተምረውን ትምህርት ተዘጋጅቶ መሄድ ይገባዋል፡፡ አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎችም መስጠት ለአገልግሎቱ አጋዥ ይሆንለታል፡፡ ካህናት ማስፈራሪያዎች ሳይሆኑ አስተማሪዎች መሆናቸው በምእመናን ዘንድ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ሊታወቅ የሚችለው ካህናት የሚጠበቅባቸውን በአግባቡ መወጣት ሲችሉ ብቻ ነውና ካህናትም የኖላዊነት ሥነ ምግባርን ተላብሰው ማገልገል ይገባቸዋል፡፡

2.2.5.4. ካህን በአደባባይ (ሕዝብ በሚሰበሰብበት ስፍራ)

ካህን በአደባባይ የሚሰጠውን አገልግሎት ለ3 ከፍሎ ማየት ይቻላል

1ኛ. በበዓላት

2ኛ. በኃዘን

3ኛ. በሽምግልና ቦታ

ካህን በሥርዓተ ኖሎት በመቅረዝ ላይ እንዳለ መብራት (በተራራ ላይ እንደተሰራች መንደር) ሁሉ የሚመለከተው የሚያዳምጠው ነው፡፡ ኦርቶዶክሳዊ በዓላት በቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በአደባባይም የሚከበሩ በዓላት አሉ፡፡ በእነዚህ በዓላት መልኩና ባህሉ እንዳይበከል የሚቆጣጠር ካህኑ ነው፡፡ የበዓላቱ ጀማሪና ባራኪ እርሱ ነው፡፡ካህን የምእመናን ጠባቂ ስለሆነ በአደባባይ በአላት ምእመናን ከበዓሉ ዓላማ በተቃራኒ (ስካር፣ ሌብነት፣ ሴሰኝነት፣ ዝሙት የመሳሰሉት) እንዳይወድቁ እና እንደ ልምድ እንዳይዙ ትምህርት መስጠት መቆጣጠርና መከታተል ኃላፊነቱ ነው፡፡በዓላቱን ተከትሎ የጥንቆላና የክፉ መንፈስ አሰራሮች እንዳይደባለቁ ማስተማር ይጠበቅበታል፡፡ (በጥምቀት በዓል ባለዛሮች እንዲሁም በበዓላት ጋር ተያይዞ የሚፈጸም ቀለምን መሰረት ያደረገ እርድ) ካህኑ ለሞት በማጣጣር ላይ የሚገኘውን ምእመን የኑዛዜውን ቃል ይቀበላል፡፡ የውርሱን ቃል በምስጢር ጠብቆ በጽሑፍ ይዞ ለተፈቀደላቸው ሰዎች ያከፋፍላል፡፡ የንስሐ (የነፍስ) አባቱ ልጁ በሞት በሚለይበት ወቅት ጸሎተ ፍትሐቱን ይመራል፡፡ ኃዘን የሚያስረሳ የማጽናናት ትምህርት ይሰጣል፡፡ ምእመናን እንደ አረማውያን ደረታቸውን እየደቁ ሙሾ እየደረደሩ መሪር እንባን በማፍሰስ ኃዘናቸውን እንዳይገልጹ ያስተምራል፡፡ በሀገራችን በተለምዶ ደረት መድቃት፣ ፊትንና ጸጉርን መንጨት ጥቁር መልበስና መሬት ላይ በመውደቅና በመነሳት የሚፈጸም የሃዘን ሥርዓት ምእመናን እንዳይተገብሩ ማስተማር ይገባዋል፡፡ አነዚህ ድርጊቶችን በመቃወም ተስፋ ትንሳኤን በመናገር የአህዛብን ልማድ በቤተክርስቲያን እንዳይፈጸም ካህኑ የማስተማር ግዴታ አለበት፡፡ በበዓላትም ይሁን በኃዘን ቦታ የካህኑ የኖላዊነት ተግባር በክርስቲያኖች ሥርዓተ ትምህርት ላይ ሰርገው የሚገቡ አንዳንድ መጤ ሥርዓቶችን ለመቆጣጠርና ምእመናንን ከጥፋት ለማዳን የቤተክርስቲያንንም ትምህርት በትምህርቱ የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ካህን ሰውንና ሰውን ብቻ ሳይሆን ሰውንና እግዚአብሔርን ያስታርቃል ያስማማል፡፡ ስለዚህ የካህን ተቀዳሚ ስራ ማስታረቅ ነው፡፡ በምእመናን መካከል አለመግባባት ሲከሰት የማስታረቅ ሥራን ይሰራል፡፡ ማቴ 18፣17፤ማቴ 5፣9 ካህን ማስታረቅ ብቻ ሳይሆን ምእመናንንም የመቅጣት ስልጣን አለው፡፡ 1ኛ ቆሮ 6፣1-8 ካህናት ከማስታረቅ እና ትክክለኛ ዳኝነትን ከመስጠት ውጪ አንዱን ወገን የመጥቀም ሌላውን የመጉዳት ሥራ የሚሰሩ አንዳይሆኑ ስርዓተ ኖሎትን የተማሩ መሆን ይገባቸዋል፡፡

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

2.2.5.5. ካህን በማህበራዊ ሕይወት

ካህን በማህበራዊ ሕይወት የሚሰጠውን አገልግሎት ለ6 ከፍሎ ማየት ይቻላል

1. ከድሆች ጋር 2. ከሀብታሞች ጋር 3. አሳዳሪ ከሌላቸው የሙት ልጆች ጋር

4. ጧሪ ቀባሪ ከሌላቸው አረጋውያን ጋር 5. ከህመምተኞች ጋር (በሆስፒታል)

6. ከእስረኞች ጋር (በወህኒ ቤት) ካህን የሁሉ አባት መሆኑና እግዚአብሔርም ከፍጥረቶቹ የማይለይ ለመሆኑ የካህኑ አገልግሎት ማስረጃ ነውና አገልግሎቱ ለሁሉም ነው። እስራኤላውያንን ሙሴ ነፃ እንዲያወጣ ሙሴን እግዚአብሔር ሲልከው እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ብሎት ነበር። ዘፀ 3፣12 ለሐዋርያት ለካህናትም እኔ ከእናነተ ጋር እሆናለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል። ማቴ 28፣19 ለመልካም ሥራ እግዚአብሔር የጠራቸው የእግዚአብሔር መልእክተኞች ካህናትም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ላሉት ሁሉ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

❖ *ካህን ከድሆች ጋር*

ነቢዩ ኤልያስ ከእፍኝ ዱቄትና በማሰሮ ከተቀመጠ ከጥቂት ዘይት በስተቀር እንጀራ በሌላት በስራፕታ መበለት ቤት መግባቱን እና በቤቷም በረከት መሆኑን ይነግረናል። 1ኛ ነገ 17፣ 12በዚህ ዓለም የእግዚአብሔር ጉልህ ምሳሌና መጋቢ ስለሆነ የድሆች ዓይኖች ወደ ካህኑ ይሆናሉ። በነፍስ የተራቡ አስተምሮ ከረሀበ ነፍስ ያድነናል በሥጋ የተራቡትም ከረሀበ ሥጋ ያድነናል በማለት ወደ እርሱ ይመለከታሉ፤ካህን ሥራዎች አንዱ የድሆች ጓደኛ የድሆች ባልደረባ መሆን ነው። ‹‹ድሆችን ለማጽናናት ተልኬአለሁ።›› ብሎ የሚያስተምር ካህን በረሀብ የሚኖሩ ወገኖች የሚያሳዝኑት በእውነት የክርስቶስ ተማሪ ነው። የድሆችን ችግር መቅረፍ ባይችልም ምእመናንን እያስተባበረ ሰርተው መብላት የሚችሉትን እንዲሰሩ መስራት የማይችሉትን በአስተዋጽኦ እንዲጦሩ ያደርጋል። ድህነት የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳይመስላቸው እንዳያማርሩ ተስፋም እንዳይቆርጡ ድሆችን በቃልም በተግባርም የሚደግፍ መሆን የካህኑ ግዴታ ነው። ጌታችን ለአብነት ድሆችን ቤታቸው ድረስ እየሄደ ይጎበኛቸው ነበር። ካህኑም በቤታቸው እየተገኘ እንክብካቤ መስጠት ግዴታው ነው።

❖ *ካህን ከሀብታሞች ጋር*

እግዚአብሔር በሰጣቸው ጊዜ ሳይታክቱ የሠሩ ለሀብትና ብልጽግና የሚበቁ መሆናቸው እሙን ነው። የሀብታቸው ምንጭ እግዚአብሔር ነው። ‹‹ ብሩ የእኔ ነው ፣ወርቁም የእኔ ነው፡ ›› ሐጌ 2፣8 ይህም በመሆኑ ሀብታሞች በድሆች ላይ እንዲኩራሩ እና እንዲንቋቸው አይገባምና ይህንን ካህኑ በሚገባ ያስተምራቸዋል። ድሆች ለሀብታሞች የጽድቅ አውድማ ናቸው። ማቴ 25 ሀብታሞች በልግስና ሀብትና በረከት የሚገኝ መሆኑን እንዲሁም ሰማያዊ ዋጋ የሚያገኙበት መሆኑን አምነው ተረድተው እንዲፈጽሙ ማስተማር የካህኑ የመጋቢነት ግዴታው ነው። ምሳ 11፣24 2ኛ ቆሮ 9፣6 በሀብታቸው በአግባቡ የማይጠቀሙ እንደ ነዌ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

አስከፊ ቅጣት የሚጠብቃቸው መሆኑን በሀብታቸው እንዳሰቡት ሳይጠቀሙ በሞት መነጠቅ መኖሩን ካህን ሳይፈራና ሳይሳቀቅ ማስተማር ኃላፊነት አለበት። ሉቃ 16፣19 ካህን እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ሀብታሞችን ሹማምንትን ሲሳሳቱ ቢያይ ‹‹ መምህር ወመገስጽ ዘኢያደሉ ለገጽ›› እንዲሉ ሳያዳላ የሚገስጽ መምህር መሆን አለበት ማቴ 14፣4 በክርስቶስ አባትነት ሀብታሞች የድሆች ወንድሞች ጠባቂዎች መሆናቸውን የሚያውቁት ሀብቱን ከእግዚአብሔር በረከት ሲረከቡ ለወንድሞቻቸውም እንዲያካፍሉ የእግዚአብሔር አደራ ያለባቸው መሆኑን የሚገነዘቡት አደራውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ካህን ሲያስተምራቸው ነው።

❖ ካህን አሳዳሪ ከሌላቸው የሙት ልጆች ጋር

ካህን ለሙት ልጆችም አባት ነው። አሳዳጊና ጠባቂ ለሌላቸው እንደ እናት እንደ አባት ሆኖ የሚያሳድግ ካህኑ ነው። ካህን ይህንን የሚተገብረው በሰብአዊ ርህራሄ ሳይሆን ከእግዚአብሔር በተቀበለው አደራ ነው። ካህኑ ምእመናንን አስተባብሮ በቤቱ ወይም በቤተክርስቲያን የሙት ልጆችን የሚያሳድግበት የሚያስተምርበት መጠጊያ ማቋቋም ይገባዋል። የሙት ልጆች በቤተክርስቲያን አካባቢ ካደጉ የቤተክርስቲያንን ውለታ አይረሱም ለሀገራቸውም መልካም ዜጋ ሆነው ያድጋሉ። እነርሱም በተመሳሳይ በችግር የሚገኙ ወገኖቻቸውን የሚደግፉ ይሆናሉ። ካህኑ በዚህ ተግባር እግዚአብሔር እንዲመሰገን ያደርጋል። ቤተክርስቲያንም ያላትን መወደድ እንዶጨምር ያደርጋል።

❖ ካህን ጧሪ ቀባሪ ከሌላቸው አረጋውያን ጋር

ካህን ተልእኮው እግዚአብሔርን ለማመስገን ስለሆነ የእግዚአብሔርን ማዳን ተከትሎ ይሠራል። ሽማግሌዎች የውበትና ቁንጅና ወራት ያለፈባቸው ስለሆነ ብቸኝነት ያጠቃቸዋል። የሚያነጋግራቸውም አያገኙም። ለእነዚህ አረጋውያን የመጀመሪያ እርዳታ ቀርቦ ማነጋገር ነው። የአረጋውያን ምርቃታቸው በረከትን እርግማናቸው ጉዳትን የሚያመጣ በመሆኑ ካህን እየቀረበ ማጽናናት እና መጠየቅ የኖላዊነት ኃላፊነቱ ነው። ሥራ መስራት የሚችሉ አረጋውያን አንዲሰሩ የማይችሉም አንዲጦሩ ካህኑ በትጋት ምእመናንን ያስተምራል፤ እርሱም በቀዳሚነት ይህንን ይተገብራል።

❖ ካህን ከህመምተኞች ጋር (በሆስፒታል)

የሰውን ልጅ ወደ ተስፋ መቁረጥ ከሚመሩ ጉዳዮች አንዱ ሕመም ነው። ካህኑ የታመሙ ወገኖች እግዚአብሔር ተቆጥቶን ነው ባይወደን ነው ብለው አንዳያማርሩ ምክርና እንክብካቤ ማድረግ ይኖርበታል። ጌታችን ሀሙማኑ ባሉበት ስፍራ እየተገኘ ይፈውሳቸው እንደነበር ካህኑም ሀሙማኑ ባሉበት ቦታ ተገኝቶ ማጽናናት ይገባዋል። በነፍስ የታመሙትን በትምህርት በስጋ የታመሙትን በተአምራት የመፈወስ ሀብት ከጌታ ተሰጥቶታልና መተግበር ይገባዋል። ያዕ 5፣14 - ላይ አንደተጠቀሰው ካህኑ የታመመውን ዘይት እየቀባ መጸለይ ይገባዋል። ምስጢረ ቀንዲልን ይፈጽማል።ሕሙማኑ የገጠማቸው ሕመም ለሞት የሚዳርግ ቢሆንም ከሞት ወዲያ ያለውን ሕይወት በማስታወስ ማስተማር ሞትን አንዳይፈሩ በመንፈስ አንዲጠነክሩ ማስተማር ይኖርበታል። እንደየበሽታው ዓይነት የሚድኑበትን መንገድ ማሳየት

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ይገባዋል፡፡ ጸሎተ ቀንዲል በማድረስ ጸበል በማጥመቅ ሥጋውና ደሙን በማቀበል ሕመማንን መርዳት ይገባዋል፡፡ ምእመናን በሽታን ሊያባብሱ ከሚችሉ ጉዳዮች (መጠጥ ሲጋራ እንዲርቁ ካህኑ ተግቶ ማስተማር ይገባዋል፡፡

❖ ካህኑ ከእሰረኞች ጋር (በወህኒ ቤት)

ጌታችን በሲኦል በእስራት ያሉትን እንደፈታ እንዲሁ ካህን ደግሞ በእስር ቤት ያሉ ወገኖችን ካለባቸው እስራት በመንፈስ የተፈቱ እንዲሆኑ በማጽናናት ንስሀ እንዲገቡ ማድረግ ይገባዋል፡፡ በእስረኝነታቸው ምክንያት ተማረው ተስፋ እንዳይቆርጡ ጸሎትን ካህኑ ያስተምራቸዋል፡፡ ከእስራት ከወጡም በኋላ ዳግም ጥፋት እንዳይፈጽሙ ያስተምራቸዋል፡፡

❖ ካህን ከኃጢአተኞች ጋር

ካህን በኃጢአት ውስጥ ለሚኖሩና የሥነ ምግባር ችግር ላለባቸው የሚሰጠውን አገልግሎት ለ3 ከፍሎ ማየት ይቻላል

1. ከሌቦች ጋር
2. ከሰካራሞች ጋር
3. ከአመንዝሮች ጋር

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጠፋውን ለመፈለግ የመጣ ስለሆነ የሰውን ድካም ሁሉ ተሸከመ እንጂ አልተጸየፈም፡፡ ሰውን ሁሉ በመውደዱ የቀራጮችና የኃጥአን ወዳጅ ተባለ፡፡ ካህኑም የክርስቶስ እንደራሴ ነውና ሰዎችን ሁሉ ከወደቁበት የማንሳት የኃጢአት በሽታ የተያዙትን ለይቶ ወደ ሌላው መንጋ እንዳይተላለፍ በንስሐ የሚከላከል ነው፡፡ክርስቶስ ከሌቦች ጋር ተገኝቶ ታማኝነትን፤ ከሰካራሞች ጋር ተገኝቶ ትምህርትን ከዘማውያን ጋር ተገኝቶ ቅድስናን ማስተማሩን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ፡፡ክህኑም ሌሎችን አድናለሁ ብሎ በሚያደርገው መልካም ሥራ እራሱም እንዳይታመም አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ካህናት በንስሐ ልጆቻቸው ጥፋት ተጠያቂነት ስላለባቸው መንጋውን በአግባቡ መጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ሕዝ 34፣4 - በአግባቡ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ኖሎት ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡

➢ ካህን ከሌቦች ጋር

ሰው የሌብነትን ጠባይ ሊያዳብር የሚችለው በ3ት ምክንያቶች ነው፡፡

ሀ. **በልማድ የሚፈጸም**፡ - ከልጅነት ጀምሮ በሚፈጸም ጥቃቅን የሌብነት ተግባራት ልማድ ሆኖ በገዘፈ የሌብነት ሥራ ይገለጣል፡፡ ስለዚህ ልጆችን በጥቃቅን የሌብነት ተግባራት ሲፈጽሙ በአግባቡ እየቀጡና እያስተማሩ ማሳደግ ጠቃሚ እንደሆነ ካህኑ ተግቶ ማስተማር ይገባዋል፡፡

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ለ. **ከችግር የተነሳ የሚፈጸም፡** - መሰረታዊ ፍላጎቱን ማሟላት ካለመቻል የተነሳ ራብንና መጠማትን ለማስታገስ አማራጭ በማጣት ወደ ሌብነት መሰማራት ነው፡፡

ሐ. **በውንብድና መንፈስ በጥጋብ የሚፈጸም፡ -**

ሌብነት በማናቸውም መንገድ ይፈጸም ለህበረተሰብ በሽታ ነው፡፡ ሌላው ሊዘርፍ አንዱ ደግሞ ሊከላከል በሚደረገው ግብ ግብ የሰው ሕይወት እስከ መጥፋት የሚያደርስ ሌብነት ነው፡፡ ‹‹ የወንድምህ የሆነውን ሁሉ አትመኝ›› ተብሎ የታዘዘ በመሆኑ ማንም ሰው የባልንጀራውን ንብረት አለአግባብ ቢወስድ እግዚአብሔርን ያስቀይማል፡፡ ካህን የእግዚአብሔር ወኪል ስለሆነ የህብረተሰቡ አባት ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሕግ የማስከበር እንዲሁም የህብረተሰቡን ጸጥታና ሰላም የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ልጆች በስርዓት እንዲያድጉ የሌብነት ጠባይ እንዳያዳብሩ ምእመናንን ያስተምራል፡፡ለረሀብና ለችግር የተጋለጡ ምእመናንን ሰርተው እራሳቸውን የሚደግፉበትን ዘዴ መፍጠር የካህኑ ተግባር ነው፡፡ በሽፍትነት ማህበረሰቡን የሚያውኩትንም ከክፉ ሥራቸው የሚመለሱበትን መንገድ መቀየስ የካህኑ ታግባር ነው፡፡

➢ *ካህን ከሰካራምቾና ከዕፅ ተጠቃሚዎች ጋር* -

አባቶች ስካርን የፈቃድ እብደት ብለው ይጠሩታል፡፡ ስካር በሰዎች ሕይወት ላይ አራት ነገሮችን ያመጣል፡፡

1. **ያዋርዳል** - እነ ኖህ እነ ሎጥን የመሰሉ ታላላቅ አባቶችን ያዋረደ ነውና፡፡ ዘፍ 9፣20 ፤ 19፣30 ሰው ሰክሮ ከታየ የሚያከብሩት ያዋርዱታል፡፡ የሚፈሩት ይንቁታል፡፡ ለቤተሰቦቹም አሳፋሪ ይሆናል፡፡

2.2.6. መሥዋዕተ ሐዲስ

በሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎቶች አንዱና ዋንኛው መሥዋዕት ማቅረብ ነው፡፡ በሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት የሚያቀርብ ከህን ይባላል፡፡ በሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት በሦስት ዋና ዋና ክፍል ይከፈላል እነዚህም

2.2.6.1. መንፈሳዊ መስዋዕቶች

ክህነት መንፈሳዊ ነገር ነው፣ በአንጻሩ፣ማንኛውም አማኝ (ክርስቲያን) በትክክል ካህን ሳይሆኑ. መንፈሳዊ መስዋዕት እና መንፈሳዊ ዕጣን ሊያቀርብ ይችላል። መዝሙረኛው ዳዊት እንዲህ አለ “ጸሎቴ በፊትህ እንደ ዕጣን ይሁን እንደ ምሽት መሥዋዕት እጆቼን አነሳሁ” መዝ.141÷2፡፡ ይህ መንፈሳዊ መስዋዕት ነው፡ የዚህ አይነት ዕጣን ማቅረብ እና የዚህ ዓይነቱ መስዋዕትነት. ይህ ለሁሉም የተሰጠ። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ እንዲህ ብሏል። “እግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዘዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

አእርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው" ሮሜ 12÷1። እነዚህ ሁሉ መንፈሳዊ መስዋዕቶች የአምልኮና የጸሎት አካል ናቸው።

2.2.6.2. የምስጋና መስዋዕትነት

ከክህነት አገልግሎት ውስጥ የምሥጋና መስዋዕት ማቅረብ አንዱ ነው። ይህን መስዋዕት ማንውም ክርስቲያን ማቅረብ እንደሚገባው በቅዱሳት መጻሕፍት ተጠቅሷል። "የምስጋናን መስዋዕት አቀርብልሃለሁ። የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ።" መዝ 116÷17። "ነገር ግን መልካም ማድረግንና ማካፈልን አትርሳ እንደዚህ ባሉ መሥዋዕቶች እግዚአብሔር ደስ ይለዋል" ዕብ 13÷16 ። "በእርግጥም ሁሉ አለኝ ይበዛልኛል። ሞልቶኛል ፣ አለኝ ከአንተ የተላከውን ከአፍሮዲጦስ ተቀበልህ ደስ የሚያሰኝ መዓዛም ደስ የሚያሰኝም መሥዋዕት፥ እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኘው።" ፊልጵ 4÷18። እነዚህን አይነት መስዋዕቶች ማቅረብ የሁሉም ክርስስ,ተያኖች መንፈሳዊ ግዴታ እና የሁሉም አማኞች መንፈሳዊ ክህነት ነው። በመሆኑም ሁሉም ክርስቲያኖች መንፈሳውያን አገልጋዮች ተብለው ይጠራሉ "የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" 1ኛጴጥ 2÷9። "መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ከህናት እንድንሆን ላደረገ ለእርሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን አሜን" ራዕ 1÷6። "በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰወዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ከህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግካቸው" ራዕ 5÷10። "ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺሕ ዓመት ይነግሣሉ" ራዕ 20÷6።

2.2.6.3. አማናዊ መሥዋዕት (ቅዱስ ቁርባን)

ለቅዱስ ቁርባን መስዋዕት ልዩ ክህነት፣ልዩ ሥልጣን አለ። ይህ ክህነት ከእግዚአብሔር እግዚአብሔርን በዚህ መንገድ እንዲያገለግሉ ለሚመረጡ የተወሰኑ ሰዎች የሚሰጥ ሥልጣን ነው። በአዲስ ኪዳን እንደተረጋገጠው ካህን.ከእግዚዚብሔር የተመረጠ፣የተለየ አገልጋይ ነው። ይህ ክህነት ለሁሉም አይደለም፣አይሰጥም፣ እና ሁሉንም ሰው በዚህ ክህነት ማስቀመጥ አይችልም። ይህን መሥዋዕት የሚያቀርብ ካህን የሆነ ለዚህ አገልግሎት የተመረጠ ሰው ብቻ ነው።

2.2.7. የካህናት መብትና ግዴታ

2.2.7.1. መብት

- ከቦታ ቦታ የመዘዋወር፣ በፈለጉበት ቦታ ትዳር መሥርተው፣ ንብረት አፍርተው መኖር
- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተመረቁበት የመንፈሳዊ ሙያ ዘርፍ የማገልገልና ደመወዝ ማግኘት
- በመንፈሳዊና በዘመናዊ ትምህርታቸው የማደግ፣ ዕውቀታቸውን የማሳደግ
- በማረሚያ ቤት፣ በሕክምና ተቋማት ፣ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች በመረዳት ላይ የሚገኙ አርቶዶክሳውያንን የመጠየቅ ፣ የማስተማር ፣ የመምከር ማቴ. 25÷36፤

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

- ችግሮች በሚፈጠሩባቸው አካባቢዎች እንደ ማኅበረሰብ አካል ችግሮችን ለመፍታት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ
- የቤተ ክርስቲያንን መብትና ጥቅም ለማስከበር በመንግሥታዊ ተቋማት ተጠሪ ሆኖ የመገኘት መብቶች አሏቸው።

2.2.7.2. ግዴታ

- ቢቻላችሁስ ከሁሉም ጋር በሰላም ኑሩ በሚለው ሕግ ከሌሎች ጋር ተስማምቶና ተግባብቶ የመኖር ባህል እንዲዳብር ማስተማርና ማኅበራዊ ኀላፊነትን መወጣት
- ማኅበራዊ ቀውስንና አለመረጋጋትን የሚፈጥሩ የዘውግና የቋንቋ ጉዳዮች ውስጥ አለመሳተፍ እና እንደዚህ ያሉ ድርጊቶችን ማውገዝ ፤
- በሃይማኖት ዐውደ ምሕረት ላይ የፖለቲካ አጀንዳዎችን ርእሰ ጉዳይ አድርጎ ከማስተማር ወይም በፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ ከመግባት መቆጠብ ፤
- በሥጋዊ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ከመመሥረት መቆጠብ ፤
- የአገርንና የቤተ ክርስቲያንን ሀብት መጠበቅና ማስጠበቅ ፤ ከዘራፊዎች መከላከል
- ብሔራዊ፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕግጋትን ማክበር እና ማስከበር ፤

2.2.8. ካህናት ከመፈጸም ሊታቀቡባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- ካህናት የምድራዊ አሳቦች ደጋፊ መሆን አይችሉም ፤
- ከልክ በላይ ጠጥቶ መስከር አይገባቸውም/በተለይ ደግሞ በአጽዋማት ብሎም በዐቢይ ጾም ከሆነ ክህነት ያሽራል ፤
- አልባሌ ቦታዎች ላይ መገኘት በተለይም ልብሰ ተክህኖአቸውን እንደለበሱ ፤
- በጐጠኝነት ፣ በጎሳና በመሳሰሉት በመነጣጠል የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መፈታተን አይችሉም ፤
- የቤተ ክርስቲያንን ስም በክፉ ሊያስነሡና ሊያስወቅሱ የሚችሉ ድርጊቶች ከመፈጸም
- ውዳሴ ከንቱ ከመውደድ ፣ ትዕቢት ፣ አድመኝነት ፣ ጎጠኝነትና ስስት....ከመሳሰሉት
  ኢሳ. 52÷5፤ ሮሜ. 2÷24
- ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን ባልጠበቀ መንገድ ምድራዊ ሀበት ከማካበት ፤

2.2.9. ካህን ከሹመቱ የሚሻርበት ምክንያቶች

2.2.9.1. ዲያቆናት ከክህነት የሚሻሩበት ጥፋት (ፍ.ነ አንቀጽ 7)

ከሥርዓተ ቤተክርስቲያን ውጪ ከተሾመ፤ ሁለት ሴት ካገባ፤ ዘወትር የሚሰክር፤ አራጣ የሚቀበል፤ ባልንጀራውን የሚያማ በሰው ላይ የሚታበይ፤ ኑፋቄ ከተገኘበት ወዘተ...

2.2.9.2. ቀሳውስት ከክህነት የሚሻሩበት ጥፋት

‹‹ ቀሳውስት አደራቸውን ዘንግተው ችላ ብለው በምንደኝነት ግብር ከተሰማሩ እና መንጋውን የማያስተምሩ ሆነው ከተገኙ ከክህነታቸው ይሻራሉ።›› ፍ.መንፈሳዊ አንቀጽ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዧት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

6 ሁለት ጊዜ ጋብቻ የፈጸሙ ከሆነ፤ ጉቦ ሰጥቶ የተሾመ እንደሆነ የኃጢአተኛውን ንስሐ የማይቀበል ከሆነ፤ በሐሰት መስክሮ ሰው የሚያጣላ ከሆነ፤ የሚሰክር የሚኮራ እና የክፋትን ሥራ የሚሰራ፤ ኮከብ ቆጣሪ ከሆነ፤ አራጣ አበድሮ የሚቀበል፤ የጠንቋዮችን ነገር እውነት ነው ብሎ የሚቀበል፤ ከሴሰኛ ሴት የደረሰ፤ ሥር የሚምስ ቅጠል የሚበጥስ፤ ሰውን ለመጉዳት የሚደባደብ፤ ከመናፍቃን ጋር አብሮ የሚጸልይ ቁርባናቸውን የተቀበለ፤ አባላዘሩን በገዛ እጁ የሰለበ፤ ከአይሁድ ምኩራብ ከአላውያን ቤተ እምነት የሚገቡ የአይሁድን ጾም የሚጾም የበዓላቸውን እጅ መንሻ የሚቀበል ከተገዙ ሰዎች ጋር አብረው የሚጸልዩ በአገልግሎት አመካኝተው ያለ አግባብ ሚስታቸውን የፈቱና ያሰናበቱ ከሆነ ከክህነታቸው ይሻራሉ። ፍት.መን. አንቀጽ 6፤ 2ኛ ቀሌ 4፣3 እግዚአብሔርን ማገልገል - ካህናት መላእክትን መስለው በመዓልትና በሌሊት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና ነው። ሰውን ማገልገል፡ - ማጥመቅ፣ ማቁረብ፣ መባረክ፣ መናዘዝ፣ በሞት የተለዩትን ጸሎተ ፍትሐት ማድረግ ነው። ጳጳሱ የዲያቆኑንና የካህኑን ሥራ ተክቶ ማገልገል ይችላል። ቀሳውስት ሙሉ በሙሉ የዲያቆናትን አገልግሎት ተክተው ማገልገል ይችላሉ። ቀሳውስት በከፊል የኤጲስ ቆጶሳትን አገልግሎት ተክተው ይሠራሉ። ለምሳሌ ማጥመቅ፣ ማቁረብ፣ መናዘዝ፣ ምእመናንን መምራት እንደ ኤጲስ ቆጶሳቱ ሁሉ የቀሳውስቱም ድርሻ ነው። በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩትንና ከዚህ በታች ያሉትን የሚሠራ ከክህነቱ ይሻራል።

- ከሚስቱ ወጭ ወደ ሌላ ሴት ከሄደ ወይም ሁለተኛ ሚስት ካገባ (በዝሙት) ምክንያት።
- በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ሊጠብቀው የታዘዘውን የማይጠብቅ እንዲሁም እንዳይሠራ የተከለከለውን የሚሠራ፣ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ሕዝቡን የመማያስተምርና የማይመራ።
- ያለ ኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያን ከሰራ፣ ከሥልጣኑ ይሻራል።
- በቁጣ ወይም በማናቸውም ምክንያት ምዕመናን ሥጋ ወደሙን እንዳይቀበሉ ከከለከለ፣ በሥጋዊ ነገር ዋስ ተያዥ፣ምስክር ከሆነ ከሥልጣኑ ይሻራል (ፍት.ነገ አንቀጽ ፮)
- ሁለት ጊዜ የተሾመ.፣ሕዝቡን የማያስተምር የተቸገሩትን ካህናት የማየረዳ፣ጉቦ ሰጥቶ የተሾመ፣የኃጢያተኛን ንስሐ የማይቀበል፤በሐሰት የሚመሰክር፣ሰውን የሚያጣላ፣ የሚኮራ፣የክፋትን ሥራ የሠራ፣የሚሰክር፣ኮከብ የሚቆጥር፣አራጣ (ወለዶ) የሚቀበል፣ በሐሰት የሚምል፣የጠንቋዮችን ነገረ እውነት ነው ብሎ የሚቀበል፣ከሴሰኛ ሴት የደረሰ፣ ሥር የማሰ ቅጠል የበጠሰ፣ከመናፍቃን የተጠመቀ፣የመናፍቃንን ቁርባን የተቀበለ፣ አብሯቸው የጸለየ፣ በገበያ መካከል የሚበላ፣በመሸታ ቤት የሚጠጣ፣በአገልግሎት ምክንያት ሚስቱን የተለየና የፈታ፣ እመነኩሳለሁ ተባሕትዎ እይዛለሁ ብሎ ሚስቱን የተወ እና ያሰናበተ ካህን ከሹመቱ ይሻራል (ፍት፣ነገ አንቀጽ፮)

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

2.2.9.3. ኤጲስ ቆጶሳት (ፓትርያርክ) ከሹመት የሚሻርበት ምክንያት

‹‹ አንድ ኤጲስ ቆጶስ ከሀገረ ስብከቱ ውጭ ስልጣነ ክህነት መስጠት የለበትም፡፡ ሥልጣኑ ከሚመለከተው ጳጳስ ፍላጎትና ፈቃድ ውጪ ሥልጣነ ክህነት መስጠቱ ከተረጋገጠ ከሹመቱ ይሻራል፡፡ እንዲሁም ሥልጣነ ክህነትም ከእርሱ የተቀበሉ ከሹመታቸው ይሻሩ፡፡›› የሐዋርያት ቀኖና ቁጥር 35 ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ይፋ የሆነ የሃይማኖት ሕጸጽ ከተገኘበት በውግዘት ከቤተክርስቲያን ይለያል፡፡

2.2.10. ካህናት ለአገራዊ ሰላምና አንድነት የሚኖራቸው ሚና

በአንድ አገር ሰላም ውስጥ ግለሰቦች የማይናቅ ሚና አላቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በአንድ ሰው አካል ላይ ስለሚገኙ የሰውነት ክፍሎች የተናገረው ይህን ጉዳይ በደንብ ያስረዳናል 1ኛ ቆሮ.12፡፡ በአንድ አገር ውስጥ አገራዊ ሰላም ፣ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት፣ ማኅበረሰባዊ አንድነት፣የሕግ የበላይነትና እኩልነትን ማስፈን ቀላል አይደለም ፡፡ ይህም ለተመረጡ የመንግሥት ሹማምንት ብቻ የሚተው ተግባር አይደለም፡፡ በአገራዊ ግንባታ ሒደት ግለሰቦችም ሚናቸው ከፍ ያለ ነው፡ ፡ በተለይም የተማረውና ብሔራዊ ስሜት ያለው ግለሰብ ከቡድኖችና ከማኅበረሰቦች ያልተናነሰ ሚና ይኖረዋል፡፡

2.2.10.1. ካህናት ለአገር ሰላምና አንድነት ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና በአግባቡ ለመወጣት የሚፈጸሙ ጉዳዮች

- የአስታራቂነት ሚና - ጥላቻንና በቀልን ማጥፋት፣
- ሁለቱንም ወገኖች አሸናፊ የሚያደርግ ጥበባዊ ፍትሕ ፤
- የቤተ ክርስቲያንን የመማጸኛ ከተማነት ማስጠበቅ (ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ የተገኘ ሰውን በፍቅር በማቅረብ መጠጊያ መሆን
- ማኅበረሰባዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ላይ ሱታፌ ማድረግ ፤
- አንድነትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን በመስበክ ብዙ ልሳን በሚነገርባት አገር ውስጥ የአንድነት ምክንያት ሆኖ መገኘት ፤
- ችግሮች እንዳይፈጠሩ አስቀድሞ ሥራዎችን መሥራት

2.3. ማጠቃለያ

ካህናት የእግዚአብሔር እንደራሴ እና ባላደርዎች በመሆናቸው አሠረ ክህነታቸው ለማን እና ለምን እንደሆነ ማዎቅ ይኖርባቸዋል፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ እና የሕዝብ መሪ ሆኖ ለመቀጠል እጅግ መመረጥ ያሻል፡፡ በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁን ተመልከቱ እንደሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች ሃያላን የሆኑ ብዙዎች

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ባላባቶች የሆኑ አልተጠሩም “(1ኛ ቆሮ 1፡26) ብሎ አንደመከረን መጠራታችን ከእኛ የሆነ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቸርነት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የተሰጠንን ጥሪያችንን ማክበር የሁላችንም ካህናት ግዴታ ነው፡፡

ምዕራፍ ሦስት

3. ኖላዊነት

ኖሎት፡- ኖለወ ካለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ጠበቀ፣ መጠበቅ፣ ተንከባከበ ማለት ነው፡፡ ኖላዊ ደግሞ ጠባቂ ማለት ነው፡፡ ስለዚ ትምህርተ ኖሎት ማለት የኖላውያን ተምህርት ወይም ደግሞ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የጠነከረ እንዲሆን የሚያስተምሩ፣ የሚንከባከቡ፣የሚመክሩ መንፈሳውያን መምህራን ወይም አባቶች የሚማሩት ትምህርት ማለት ነው፡፡ ኖሎት የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የሚነገረው የካህናት ሥልጣንን አገልግሎትን ወይም የሥራ ድርሻ ለመግለጽ ሲፈለግ ነው ። ምክንያቱም የክህነት ሥራ ትምሕርት ማስተማርና የጥበቃ ሥራ ስለሆነ ቃሉ ለካህናት ክህነታዊ አገልግሎት በቂ መግለጫ ሆኖ በመገኘቱ ለትምሕርቱ እርእስ ሆኖ እንዲያገለግል ተመርጧል፡፡

ትምህርተ አበ ነፍስ ፡- ማለት የንስሐ አባት የሚሆኑ ሰዎች አባቶች የሚማሩት ትምህርት ነው፡፡ ትምህርተ ኖሎትም ሊባል ይችላል፡፡ የሰውልጅ የነፍሱም የሥጋውም ጠባቂ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ካህኑ ነውና ካህኑ አበ ነፍስ (የነፍስ አባት) ይባላል፡፡ ካህኑ ንስሐ ልጆቹን በአግባቡ እንዲጠብቅ፣ እንዲመክር፣ እንዲያስተምር የሚሰጠው ትምሕርት ትምሕርተ አበ ነፍስ ይባላል፡፡

3.1. የኖላዊነት አይነቶች

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ አብልጦ ስለሚወደው አጥብቆ ይጠብቀዋል፡፡ “ወአቀቦሙ እግዚአብሔር ለጻድቃን እለ ሎቱ ተቀንዩ በሕይወቶሙ” (ቅዱስ ያሬድ) እግዚአብሔር ጻድቃንን እንደ ዐይን ብሌን ይጠብቃቸዋ፡፡ ምክያቱም በሕይወታቸው ዘመን ለእርሱ ተገዝተዋልና በማለት አመስጥሮልናል፡፡ በዚህ ትምህርታችን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በሦስት መንገድ እንደሚጠብውና እንደሚንከባበከበው እናያለን፡፡

3.1.1. አምላካዊ እረኝነት

ኢሳ 40፡10-12 (መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል) ሕዝ 34፡5-25(እረኛን በማጣት ተበተኑ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ ተበተኑም) 1ኛ ጴጥ 1፡25 በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፡፡ እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል፡፡ መዝ 22፡1-5(እግዚአብሔር እረኛዬ ነው)፣ መዝ79፡1፣ ዮሐ 10፡11-17፣ ዕብ 13፡20-22፣ 1ኛ ጴጥ 2፡25 እና ዮሐ 15፡12

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

3.1.2. መልአካዊ እረኝነት

መዝ 33፡7፣ ማቴ 18፡10፣ ዕብ 1፡14 ማቴ 4፡3 መዝ 90፡10 በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል።

3.1.3. ሰበአዊ እረኝነት

ኤር 25፡32 ሕዝ 34፡1-10፣ ኤር23፡1-5 የማሰማርያዬን በጎች ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር ስለዚህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሕዝቤን ስለሚጠብቁ እረኞች እንዲህ ይላል። በጎቼን በትናችኋል አባርራችኋቸውማል አልጐበኛችኋቸውምም እነሆ፥ የሥራችሁን ክፋት እጐበኝባችኋለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር የመንጋዬም ቀሬታ ካባረርኋቸው ምድር ሁሉ ወደ በረታቸው ሰብሰቤ እመልሳቸዋለሁ እነርሱም ያፈራሉ ይበዙማል።

“እነ ውእቱ ኖላዊነ ኄር”

“መልከም እረኛ እኔ ነኝ” ዮሐ 10÷12

3.2. መልካም እረኛ

እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሚያደርገው ጥበቃ እና እንክብካቤ እረኛ ሆኖ በተለያየ መልኩ ተገልጿል። በዚህ መሠረት የእረኛ ተገግባርና ኃላፊነት እንዲሁም ፍቅር የተሞላበት የጥበቃ ሥራ መነሻ በማድረግ እግዚአብሔር እውነተኛው የሕዝብ እረኛና ጠባቂ መሆኑ በመጸሐፍ ቅዱስ በሰፊው ተገልጿል። በዚህም መሠረት እግዘአብሔር የሁሉ እረኛ የሁሉ ጠባቂ ነው እንላለን። ታላቁ የእምነት አባት ብጹእ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ በጻፉት “ቅስና” በተባለው መጽሐፋቸው እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ እረኛና መጋቢ ነው ብለዋል። በአሪት ዘፍጥረት ታሪክ ውስጥም እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከመፍጠሩ አስቀድሞ ያዘጋጀው የሚኖርበትን ለምለም የሆነችውን ሥፍራ ገነትን ነው **ዘፍ** 2÷7። ይህ ሥራ ጠባቂነቱን እረኝነቱን ያመላክታል። እግዚአብሔር የሕዝብ ጠባቂ እረኛ ነው። እግዚአብሔር ጠባቂ እረኛ መሆኑ በብሉይም በሐዲስም ተገልጿል።

3.2.1. የእረኛ ተግባር

በእረኝነት ሥራ ላይ የተሰማራ ጠባቂ እረኛ የሚፈጽማቸው፣የሚተገብራቸው የእረኝነት ተግባራትን በዝርዝር እንመልከት። **እረኛ** በጎችን፣ፍየሎችን፣ከብቶችን የሚጠብቅ፣

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

የሚያሰማራ፣ የሚመገግብ ጠባቂ ማለት ነው። እረኝነት በጥንት ዘመን በደንብ የሚታወቅና በዕለታዊ ሕይወት ውስጥ የሚተገበር የኑሮ ክፍል ነበር። ምክንያቱም በወቅቱ የሕዝቡ ኑሮ በዋናነት ከግብርና እና ከብት በማርባት ሥራ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው የአቤልና የቃየል የኑሮ ሁኔታ ነው። አቤል በግ ጠባቂ (እረኛ) ነው፣ ቃየል ግን ገበሬ ነው (ዘፍ 4÷2)። ወንድማማቾቹ አብርሃምና ሎጥ እረኞች ነበሩ (ዘፍ 13÷4-6)፣ ያዕቆብና ልጆቹ መንጋቸውን እያገዱ በእረኝነት ሥራ ውስጥ ተሰማርተው እንደነበር ይታወቃል። ሙሴ በምድያም ምድር በእረኝነት ሲያገለግል ነበር (ዘፀ 3÷1)። ነብየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት የአባቱን በጎች እረኛ በመሆን ከአንበሳ እና ከድብ እየታገለ የእረኝነት ሥራውን ያከናውን ነበር (1ኛሳሙ 17÷12) ። ነብይ አሞጽ ለነብይነት አገልግሎት ከመጠራቱ በፊት የበግ መንጋ ጠባቂ በመሆን በእረኝነት ያገለግል ነበር። በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የታወቁት ታላላቅ የእግዚአብሔር ምርጥ አገልጋዮች የእምነት አባቶች፣መሳፍንትና ነብያት አብዛኞቹ በእረኝነት ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ከእረኝነት የተመረጡ፣ለአገልግሎት የተጠሩ ናቸው። እረኛ በሕዝቡ ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ልዩ ሥፍራ የሚይዝ የአገልግሎት ሕይወት መሆኑን መገንዘብ ይገባል። በመሆኑም ጠቅለል ባለ አነጋገር የሚከተለውን እንመልከት።

3.2.1.1. በጎችን ማወቅ

ከእረኛ ተግባራት የመጀመሪያው በጎቹን ለይቶ ማወቅ ነው። በጎቹ እነማን ናቸው? ምን አይነት ባሕርይ አላቸው? በምን አይነት መልኩ ነው መጠበቅ የሚቻለው? ለሚሉት ጥያቄ መልስ ለማግኘት በጎችን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። እረኛ ብቻ አይደለም በጎችን ማወቅ የሚገባው፤ በጎችም እረኛቸውን ማወቅ አለባቸው። በተፈጥሮ በጎች እንስሳት ቢሆኑም እረኛቸውን ለይተው የማወቅና ድምጹን የመለየት ሥጦታ አላቸው። ጌታ በአንቀጸ አባግዕ ላይም የገለጸው ይህን ነው "በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃችኋለሁ ይከተሉኛል" ዮሐ 10÷27። በዚህ ቅዱስ ወንጌል በጎች የተባሉ ክርስቲያኖች ናቸው። "ድምጼን ይሰማሉ" ማለቱ ትምህርቴን ይሰማሉ ይቀበሉኛል ማለቱ ነው።"በጎቼን አውቃችኋለሁ" ማለቱ ለምዕመናን እሞትላቸዋለሁ፣መሥዋዕት እሆንላቸዋለሁ ማለቱ ነው። "በጎቼም ያውቁኛል ይከተሉኛል" ማለቱ እኔን ያውቁኛል፣ያምኑኛል፣እኔን አብነት አድርገው በስሜ መከራ ይቀበላሉ ማለቱ ነው። ቃሉን መስማት እርሱን መከተል ደግሞ የዘላለም ሕይወት ማግኛ መንገድ እንደሆነ በመጸሐፈ ድዲስቅሊያ ላይ ተጠቅሷል **"በጎቼ ቃሌን ይሰሙኛል እኔም አውቃቸዋለሁ። እነርሱም ይከተሉኛል የዘለዓለም ሕይወትንም እሰጣቸዋለሁ ብሏልና"** መጸ.ድዲስቅሊያ 6÷20።

ሌላው ማወቅ ማለት መለየት ማለት ነው እረኛው በጎቹን በመልክ፣ (ጥቁር፣ ቡራቡሬ፣ ነጭ፣ቀይ እያለ) በቁመት፣በተለያዩ ምልክቶች ይለያል። እረኛ ለበጎቹ ስም ሰጥቶ በየስማቸው ይጠራቸዋል ሶሪት፣ቆሪት፣ቀንዲት። **"በጎቹን በየስማቸው ይጠራቸዋል"** ዮሐ 10÷3 ተብሎ እንደተጠቀሰ ጌታችንም ደቀመዛሙርቱን ስምዖን ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ፣እንድርያስ፣ ዲድሞስ እያለ ይጠራቸዋል። ካህኑም በጎቹን ገብረማርያም፣ኃይለ ኢየሱስ፣ገብረጻድቅ፣ ገብረእግዚአብሔር፣ወለተ ማርያም ወለተ ኢየሱስ.፣አመተ እግዚአብሔር እያለ ይጠራቸዋል።

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

በጎቹን በስማቸው የሚጠራቸው ብዙውን ጊዜ ወደተሳሳተ ቦታ ሲጓዙ እንዲመለሱ፣እርሱ ወደሚፈልገው አቅጣጫ እንዲጓዙና በሚፈልገው ሥፍራ እንዲሰማሩ ለማድረግ ነው። እረኞችን እግዚአብሔር ወይም አበ ነፍሳችን ካህኑ የሚጠራን በክህደት፣በኃጢያት መንገድ እንዳንሄድ፣ ከሃይማኖት እንዳንወጣ ነው።:

3.2.1.2. በጎችን ማሰማራት (መጠበቅ)

“በጎቼን አሰማራ” ዮሐ 21÷17

የእረኛ ዋንኛ ተግባሩ በጎችን ማሠማራት፣በጎችን መጠበቅ ነው። እረኛ ለእለት የሚሆነውን ስንቅ በመያዝ ደበሎውን በመደረብ ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ የራሱንና የሌሎቹን ከብቶች፣በጎች፣እንስሳትን ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ወዳለ ሥፍራ በመውሰድ ግጦሽ እየፈለገ ያሰማራል **ኤር 43÷12**። ጌታችን በወንጌሉ **“ያሰማራቸዋል”** ብሏል ደግሞም **“በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፣ይገባልም፣ይወጣልምመሰማሪያ ያገኛልም”** ብሏል **ዮሐ 10÷9**። ጌታችንም ከትንሳኤ በኋላ ለቅዱስ ጴጥሮስ **“በጎቼን አሰማራ ሲል”** ማሰማራት ማለት ማስተማር፣‹መመገብ›፣መጠበቅ፣ መንከባከብ ማለት ነው። እርሱ አብነት ሆኖ ካስተማራቸው በኋላ ተሰቅሎ አድኗቸዋል። እነርሱም እርሱን አብነት አድርገው ያስተምራሉ፣ ያሰማራሉ፣ ሌሎችን በጎች ያፈራሉ፣ በስሙ መከራን ይቀበላሉ።

3.2.1.3. የጠፋውን መፈለግ

ከእረኝነት ተግባራት አንዱ የጠፋውን መፈለግ የባዘነውን፣የተበተነውን መሰብሰብ፣ የተሰበረውን መጠገን፣የታመመውን ማዳን ነው። የጠፋውን በግ ይፈልጋል ባገኘው ጊዜ በትከሻው ይሸከመዋል፣እጅግ ታላቅ ደስታ ይሰማዋል “የጠፋው በጌ ተገኝቷል” ብሎ ለጎረቤቶቹ ያውጃል “መቶ በግ ያለው ከእነርሱ አንዱ ቢጠፋ ዘጠናዘጠኙን በዱር ትቶ የጠፋውን ሊፈልገው ከእናንተ የማይሄድ ማነው? ባገኘው ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል” ሉቃ 15÷4-5። “የሰው ልጅ የጠፋውን ሊያድንና ሊፈልግ መጥቷልና” ሉቃ 19÷10። የጠፋው በግ አዳም ነው፣ “መቶ በግ” ያለው ዘጠናዘጠኙ ነገደ መላእክትና በዲያብሎስ ፈንታ የተፈጠረው ከነገደ መላእክት የተደመረው አንዱ ነገድ ነገደ አዳም የሰው ልጅ ነው። “በጫንቃው ይሸከመዋል” ማለት የሰውን ባሕርይ ባሕርዩ ያደርገዋል፣አንድም ሥጋውን ይዋሐዳል፣አንድም “ወነሳ ደዌነ ወጾረ ሕማምነ” “ እኛ እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ” ተብሎ በነብዩ በኢሳይያስ እንደተነገረ፣ እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልዕክቱ “በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛ ተመልሳችኋል” ብሎ እንደመሰከረው የሰውን ልጅ ኃጢያት ይሸር ዘንድ፤ኃጢያት የሌለበት ንጹሐ ባህርይ ክርስቶስ የአዳምን ኃጢያት ተሸክሞ ኃጥኣ ተብሎ በሞቱ ሞትን ኃጢያትን እንደ ደመሰሰለት ለመግለጽ “በጫንቃው ይሸከመዋል አለ” (ኢሳ 53÷6 1ኛጴጥ 2÷25)። እረኛ የጠፋውን የባዘነውን መፈለግ ተቀዳሚ ተግባሩ እንደሆነ ሁሉ የምዕመናን እረኞች ካህናትም የጠፋውን መፈለግ፣የተበተነውን

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

መሰብሰብ፣በኃጢያት የወደቀውን ማንሳት ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። መልካም እረኛ ለበጎቹ መሥዋዕትነትን መከፍል እንዳለበት በመጸሐፈ ዲድስቅልያ ተገልጿል "ኤጲስቆጶሱ እንደዚህ ሲያደርግ ያየው ቢኖር ኃጢያትህን እኔ እሸከማለሁ ክርስቶስ ስለ ዓለም ኃጢያት እንደሞተ ስለ አንተ እሞታለሁ ይበለው፣ከዚህ በኋል ወደ ንስሐ እስኪመለስ ድረስ ከእርሱ ጋር ይድከም መከራንም ይቀበል። ቸር እረኛ ስለ በጎቹ ቤዛ ሆኖ ሰውነቱን አሳልፎ ይሰጣልና" መጸ.ዲድስቅልያ 6÷34።

3.3. መልካም እረኛ ማነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ለነፍሳት ስለሚደረግ ጥንቃቄ ጥሩና ሙላት ያለው ስእል የሚሰጠን የእረኛ ስራ ነው። የእረኛ ትልቁ መታወቅያው በጎቹን መመገብ መጠበቅና መንከባከብ ነው። በጎች ከምግብ ሌላ የሚዉልበት እና የሚያርፉበት ጸጥ ያለ ስፍራ ፡ማታ የሚሰባሰቡበት በረት ሲታመሙ መድሐኒት፡ሲደክሙ አና ሲሰበሩ የሚሸከማቸው፡ሲጠፉ የሚፈልጋቸው፡በአደጋ ላይ ሲሆኑ የራስን ሕይወት መስዋዕት በማድረግ የሚታደጋቸው እረኛ ይፈልጋሉ። ያለ እረኛ የበጎች ሕይወት በሁሉም አንጻር በአደጋ ላይ ይወድቃል። ከዚህ የተነሳ እረኛ ከበጎቹ ሳይለይ ለረጅም ጊዜ አብሮ ይኖራል። በዋናው በር ማለት በትክክለኛው መስመር ማለት ነው። ዋናው በር የተባለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በዋናው በር በክርስቶስ አምኖ የሚገባ "በረኛው ይከፍትለታል" ማለት ክርስቶስ በእለተ ምጽአት ይቀበለዋል ማለት ነው፣በጎቹ ይሰሙታል ማለት ትምሕርቱን ይቀበሉታል በእርሱ ያምናሉ። ተብሎበመጽሓፍ እንደተነገረው መለካም እረኛ በበሩ የሚገባ ነው።

3.4. የመልካም እረኛ ባሕርያት

መልካም እረኛ የሚገለጽባቸው ዘርፈ ብዙ ባሕርያት ቢኖሩትም ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

3.4.1. ለበጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ መስጠት

መልካም እረኛ ከሚገለጽባቸው ተግባራት አንዱና ዋንኛው ለበጎቹ ሕይወቱን ኣሳልፎ መስጠት ነው። መልካም እረኛ ከበጎቹ ፊት ለፊት የሚሄድበት ምክንያት በጎቹን ከሚመጣባቸው ተኩላ እና አውሬ ለመጠበቅ፣ ለማዳን የራሱን ሕይወት አሳልፎ ለበጎቹ ለመስጠት ነው። በአካባቢው ከሚገኙ እንደ ተኩላ፣አንበሳ፣ድብ ከመሳሰሉት መንጋውን መጠበቅ መንከባከብ ነው።ለዚህ በዘመነ ኦሪት ምሳሌ ሆኖ የተጠቀሰው ነብየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ነው። ቅዱስ ዳዊት በሕፃንነቱ በእረኝነት የአባቱን በጎች ሲጠብቅ አንበሳም ሆነ ድብ ጥቦቶችን፣ ግልገሎችን በሚነጥቅበት ጊዜ ተከትሎ በመሄድ አደጋ በመጣል ያስጥለው ነበር፣፤ ክንደ ብርቱ በመሆኑ አንበሳው ወይም ድብ ወደ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ ጉሮሮውን አንቆ በመምታት ይገለውና በጎቹን ከጥቃት ያድናቸው ነበር 1ኛሳሙ 17÷35። ይህ ምሳሌ ነው.፣ ዳዊት፡- የጌታ፣ አንበሳና ድብ የዲያብሎስ፣ አባግዕ የምዕመናን ምሳሌ ነው። ዳዊት ለሕይወቱ ሳይሣሣ፣ ሳይፈራ አንበሳውን ድቡን ገሎ በጎቹን በአንበሳ፣በድብ ከመበላት እንዳዳነ ሁሉ ጌታም ነፍሱን

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ሰጥቶ በመስቀል ሞቶ፣ዲያብሎስን በመስቀል ድል አድርጎ ገሎ፣ምዕመናንን ከግብርናተ ዲያብሎስ ነጻ እንዳወጣ ያመላክተናል፡፡ **“መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል”** ዮሐ 10÷11፡፡ ይህ ማለት መልካም እረኛ ቸር ጠባቂ ነፍሱን ሰውነቱን ለበጎቹ ቤዛ አደርጎ ይሰጣል፡ ፡ “እውነተኛ መምህር የምሆን እኔ ለምዕመናን እራሴን ቤዛ አድርጌ ለሞት አሳልፌ እሰጣለሁ፡፡ ምንደኛ ጠባቂ (ተቀጣሪ እረኛ፣በጎቹ የእርሱ ያልሆኑ) ተኩላ ነጣቂ በመጣ ጊዜ በጎቹን ጥሎ ይሸሻል፡፡ ከዚህ በኋላ ተኩላ መጥቶ ይነጥቃቸዋል በጎቹን ይበትናቸዋል፡፡ ምንደኛ ጠባቂ የበጎች ጥፋት አያሳዝነውም” ብሎ ጌታችን እንዳስተማረ መልካም እረኛ ነፍሱን ለበጎቹ አሳልፎ ይሰጣል፡፡

እነዚህ ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ አራት የዘረዘርናቸው የመልካም እረኛ ተግባራት ናቸው፡፡ ዛሬም በእረኝነት የተመሰሉ ካህናት ሊተገብሯቸው የሚገባ ተቀዳሚ ተግባራት ናቸው፡ ፡ እረኛ ኃላፊነት ላለባቸው ሁሉ ምሰሌ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የማይጠብቁ ባለ ሥልጣናት፣ከባድ ፍርድ ይገባቸዋል ፡፡

3.4.2. በጎቹን ከፊት ሆኖ ይመራል

በእስራኤል ሀገር እረኛ በጎቹን ከበረት ካወጣ በኋላ ለማሰማራት ከፊት ለፊታቸው ይሄዳል ግልገሎቹን ወይም የተጎዳውን፣የታመመውን ይሸከማል ለምለም ሣርና ጥሩ ውኃ ባላበት አካባቢ ሲደርስ በለምለም ሣሩ ላይ ቁጭ ይላል በጎቹም እሱን ከበው ያንን ለምለም ሳር ይግጣሉ፤እሱ ሳይንቀሳቀስ ከዛ ቦታ አይንቀሳቀሱም፡፡

እረኛ ከበጎች ፊት መሄዱ መሠረታዊ ምክንያቶች

- አርዓያ ለመሆን
- ከጠላት ለመጠበቅ
- በጎች እርሱን እንዲከተሉ ለማድረግ
- ለምለም ሥፍራን ለይቶ ለማሳወቅ

3.5. እረኛ ያላቸው በጎች

ምእመን - ደግ ሰው፣ በቃሉ የሚውል፣ ተናግሮ የማይበድል፣ ሃይማኖቱ የጸና፣ ጎዳናው የቀና፣ በተማረው ትምህርትና በተሠራለት ሥርዓት እግዚአብሔርን በማመንና በማምለክ ጸንቶ የሚኖር የቤተክርስቲያን አገልጋይ ማለት ነው፡፡ ምእመናን (አባግዕ) የሚከተሉትን መፈጸም ይገባቸዋል፡፡ ቅድስት ቤተክርስቲያንን እና የካህናቱን ተልእኮ በሚችሉት ሁሉ መደገፍ፤ እያንዳንዱ ምእመን የንስሐ አባት የመያዝ እና የሚሰጠውን መንፈሳዊና ማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ በመሳተፍ መደገፍ፤ ከንስሐ አባቱ ጋር ያለው መቀራረብ እንዳይርቅ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከንስሐ አባቱ ጋር ምክክር ማድረግ፤ የንስሐ አባቱ የቤተሰቡን አባላት በሙሉ እንዲያገኝ ሁኔታዎችን ማመቻቸት (ባለቤት፣ ልጆች፣ ዘመዶች፣ ሠራተኞችና ጥበቃዎች ወዘተ) የንስሐ አባቱ በሚያዘው መሰረት ለቤተክርስቲያን አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ የንስሐ አባቱ የሚሰጠውን ቀኖና በአግባቡ መፈጸም፤ (ለምክረ ካህን ለትእዛዘ ካህን መገዛት) በንስሐ አባቱ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ምክርና በቅዱሳት መጻህፍት ትምህርት መመራት በተወሰነለት የምእመንነት ደረጃ መኖር፤ የንስሐ አባቱ የሚያደርገውን መንፈሳዊ አገልግሎት ሁለንተናዊ ድጋፍ (በሞያው፣በገንዘቡና በጉልበቱ) በማድረግ እርሱም ተጠቃሚ መሆን ይገባዋል።

3.6. ምንደኛ እረኛ

በምድር ላይ ሕዝብን ኃላፊነት በተሞላበት መንፈስ በጥሩ ስነምግባር እንዲመሩ፣ እንዲያስተምሩ የተመረጡ ሰዎች እንደ ሕዝብ እረኛ፣ጠባቂ ተደርገው ይቆጠራሉ። ከእነዚህ የሕዝብ እረኞች መካከል የተወሰኑት እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ በመልካም እረኝነት ሕዝቡን የመሩና፣ያስተማሩ፣ከስህተት የመለሱ፣በአምልኮተ እግዚአብሔር ያጸኑ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ በእግዚአብሔር የተመሰገኑ ምሳሌነታቸው እየተጠቀሰ የእረኝነት ሥራቸው ሕያው ሆኖ የሚኖር አሉ። ለምሳሌ ያህል ቅዱስ ዳዊት፣ነብያት በሙሉ፣ንጉስ ሕዝቅያስ 2ኛነገ 18÷3፡ በአንጻሩ ደግሞ ኃላፊነታቸውን፣መምህርነታቸውን በሚገባ ሳይወጡ ቀርተው ምንደኛ፣ ኃላፊነት የጎደላቸው ሆነው የተሰጣቸውን ኃላፊነት ወይም ሹመት በሚገባ ሳይወጡ ቀርተው በእረኝነታቸው የተወቀሱ ብዙዎች ናቸው። የተወቀሱበትም ምክንያት ምንደኛ ጥቅመኛ ሆነው ሕዝቡን በተሳሳተ መንገድ ስለመሩና ኖላዊነታቸውን በሚገባ ስላልተወጡ፣በጎቻቸውን በትነው ለተኩላ ለአውሬ አሳልፈው ስለሰጡ ነው። እነዚህ ኃላፊነት የጎደላቸው ምንደኞች፣ጥቅመኛ እረኞች ላይ እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። **“ትታረዱና ትበተኑ ዘንድ ቀናችሁ ደርሷልና እንደ ተወደደም የሸክላ ዕቃ ትወድቃላችሁና እናንተ እረኞች አልቅሱ ጩሁም እናንተ የመንጋ አውራዎች በአመድ ውስጥ ተንከባለሉ”** ኤር 23÷34። (ሕዝ 34÷11-17 ዘካ 11÷17)

3.6.1. ምንደኛ እረኛ ባሕርይ

- ከመንጋው ይልቅ ራሳቸውን ይጠብቃሉ
- ጥቅም ለማካበትና በድሎት ለመኖር በመንጋው በበጎቹ ላይ ተገቢ ያልሆነ ብዝበዛ ያካሂዳሉ ሕዝ 34÷3።
- በጎችን በትነው ለአራዊት ይዳርጋሉ
- የበጎችን ጉልበት ይበዘብዛሉ፣ገንዘባቸውን ሐብታቸውን ፣ንብረታቸውን ይወስዳሉ።
- ችግር በተከሰተ፣ ነጣቂ ተኩላ በመጣ ጊዜ ሕዝቡን ትተው ይሸሻሉ ። **“መልካም እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል ተኩላ ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል።”** ዮሐ 10÷12።
- ለበጎቹ ግድ አይላቸውም፣ቸልተኞች ናቸው።

3.7. እረኛ የሌላቸው በጎች (መንጋ)

ጠባቂ እረኛ የሌላቸው መንጋ (ጠባቂ የሌላቸው በጎች) ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡ፣ የተዳረጉ ናቸው። እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች በዝርዝር እንመልከታቸው።

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመሻት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማይልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

3.7.1. ለሌባ እና ለዱር እንስሳት የተጋለጡ ናቸው፡-

እረኛ የሌላቸው መንጋ አደጋ በገጠመው ጊዜ መንጋው ተበትኖ ወደ ተለያየ አቅጣጫ ይጠፋል የተቀረውም በአውሬ ይበላል። እንዲሁም እረኛ (አበ ነፍስ) የሌለው ምዕመን በመናፍቃን፣በከሀዲዎች ይወሰዳል፣በኃጢያት፣በአምልኮ ጣዖት ተነጥቆ ለሰይጣን ተገዢ ሆኖ ይጠፋል።ሙሴ ሲጸልይ "የሕይወት ሁሉ ምንጭ የሆንክ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ሕዝቡን መምራትና በጦር ሜዳ ማዘዝ የሚችል አንድ ሰው ምረጥ በዚህ ዓይነት የአንተ ጉባኤ እረኛ እንደሌለው በግ ከመሆን ይድናል" ዘኁል 27÷11። እያለ እግዚአብሔር ለመንጋው መሪ እረኛ እንዲሰጥ ይጸልይ ነበር።

3.7.2. ባዘነው ይጠፋሉ ከባድ ችግር ውስጥ ይገባሉ ፡-

አንድ መንጋ ወይም በጎች ካሉ እረኞች መኖር ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ ይቻል ይሆናል። እግዚአብሔር በነብዩ በሕዝቅኤል ላይ አድሮ ሲናገር "በጎቼ በከፍተኛ ኮረብታዎችና ተራራዎች ተንከራተቱ፣በምድር ገጽ ተበተኑ፣የሚጠብቃቸውና ፈልጎ የሚያገኛቸው የለም" በማለት እረኛ የሌለው መንጋ ከባድ ችግር ውስጥ ሊሆኑ እንደሚችል ተናገረ ሕዝ 34÷5። እንግዲህ አበ ነፍስ ጠባቂ እረኛ ካህን የሌላቸው በጎች ምዕመናንም እንዲሁም ተቅበዝባዥ የሚባዝኑ ናቸው። ከዚህም የተነሳ ይጠፋሉ ከባድ ችግር ውስጥ ይወድቃሉ፣ጥፋታቸው የከፋ ይሆናል። መልካም እረኛ የሌለው ምዕመን እንደሚቅበዘበዝና እንደሚጠፋ ነብዩ ዘካርያስ ይናገራል ዘካ 10÷2። እረኛ የሌለው መንጋ መበታተኑና ችግር ውስጥ መግባቱ የታወቀ ነው። በመሆኑም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው እረዳት አጥተው ባያቸው ጊዜ እንደራራላቸው በቅዱስ ወንጌል ላይ ተጠቅሷል ማቴ 9÷36 (ዘካ 13÷7 ማር 14÷22)።

3.8. እረኝነት በብሉይ ኪዳን

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው በለመለመ መስክ ያሰማራኛል" መዝ 22÷1 መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት እግዚአብሔር በለመለመ መስክ እንዳርፍ ያደርገኛል ወደ ጥሩ ውኃ ምንጭ ይመራኛል። እግዚአብሔር እረኛዬ ሳለ የሚያስፈልገኝንም ሁሉ አላጣም፣ክፉ ነገር ሁሉ ይደርስብኛል ብዬ አልፈራም በማለት የእግዚአብሔርን እውነተኛ እረኝነት ይገልጻል። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ እረኛ እንደሆነ ገልጿል። "እግዚአብሔር ይርኤየኒ" "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው" "እግዚአብሔር ያየኛል" ይህን ቅዱስ ዳዊት ስለ ሁለት ነገር ተናግሮታል። አንደኛው ስለ ትሩፋን ወይም እስራኤላውያን ወደ ባቢሎን መውረዳቸው ሲሆን ሁለተኛው ስለ ምዕመናን (ስለ አዳም) ተናግሮታል። ስለ ትሩፋን ስለ አእስራኤኤውያን ሲናገር "እናንተ ባቢሎናውያን በመከራ በስደት ወደ ባቢሎን ወደ ቆላተ ጎባር ብታወርዱኝም እረኛዬ እግዚአብሔር ከሰባ ዘመን በኋላ ከባቢሎን ያወጣኛል ወደ ኢየሩሳሌም ይመልሰኛል ፣ ልብስ፣ምግብ ብትነሱኝ እረኛዬ እግዚአብሔር ይጠብቀኛል፣,ይመግበኛል። በስደት የሚተውበት ፣በምግብ የሚያሳጣበት የለም። ከሰባ ዘመን በኋላ በዘር፣በተክል በለመለመች መስክ ማየ

እረፍት ባለበት በኢየሩሳሌም ያኖረኛል።" ስለ ምዕመናን (ስለ አዳም) ሲናገር **"እግዚአብሔር ይሬእየኒ"** **"በእጸ በለስ ምክንያት በዲያብሎስ ተታልዬ ወደ ገሃነም ብወርድም ከአምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት ያገባኛል፣ይመልሰኛል"።** **"ወአልቦ ዘየኀጥአኒ"** እኔን የሚያጣበት ቦታ የለም። አንድም እግዚአብሔር እረኛዬ ምግበ ነፍስ ልብሰ ነፍስ ልስጥ በማለት ይጠብቀኛል። ከምግበ ነፍስ ከልብሰ ነፍስ ወገን እኔን የሚያሳጣበት የለውም **"ውስተ ብሔር ስዑር ኅየ የኀድረኒ"** አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ሙሉ ለጅነት በታጣበት በገነት ያኖረኛል፤ አንድም ከአምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን በኃላ በልጅነት በለመለመው ሥፍራ በገነት ያኖረኛል። **"ወኀበ ማየ ዕፍረት ሐፀነኒ"** ልጅነትን ማየ ዕረፍት አለው፤ ልጅነት የሚሰጠው በጥምቀት ምክንያት ነውና ማየ ዕረፍት ማየ ሕይወት ባለበት በገነት ያኖረኛል አለ። **በዘመነ አበው የነበሩ ቅዱሳን አባቶች ሁሉ** እንደ ካህን ሆነው አገልግሎት ይሰጡ ነበር። ዘፍ 8፤20 **ሀብተ ክህነት ለመጀመሪያው ሰው ለአዳም** ተሰጥቷል። አዳም በሀብተ ክህነቱ መስዋእት ይሰዋ ነበር። ኩፋሌ 5፣**የሳሌም ንጉስ የመልከጼዴቅ ክህነት ግን** በዘመነ ሐዲስ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለተሰጠው እውነተኛ ክህነት ምሳሌ ነው። ዕብ 7፣20 መልከ ጼዴቅ ክህነቱን ከእገሌ ተቀበለ እንደማይባል ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ክህነቱን መቀበል ከማንም ያልተቀበለው የባሕርይ ገንዘቡ ነው።የሕገ ልቦና አገልግሎት በሕገ ኦሪት ሲተካ የክህነት አገልግሎት አንድ የመንፈሳዊ አገልግሎት ዘርፍ ሆነ። ሌዋውያኑ ብቻ ካህናት ተበለው በመጠራት የቤተ መቅደሱን አገልግሎት ያከናውኑ ነበር። ሥጋዊውን የፍትሕና የመሪነት ሥራ መሳፍንቱ ያከናውኑ ነበር በኋላም በሕዝቡ ጥያቄ የመሳፍንት አመራር አክትሞ በነገስታት መመራት ተጀመረ። እግዚአብሔር ኖሎትን ከሕዝቡ መካከል መርጦ የሚሾማቸው ሕዝባቸውን ከትእዛዘ እግዚአብሔር ውጪ ሆኖ መከራ እና ችግር እንዳይገጥመው መጠበቅና የማስተማር አደራ እና ኃላፊነት በመስጠት ነው። ሙሴ እስራኤላውያንን ይመራ ዘንድ እግዚአብሔር መረጠው። ሙሴም ሕዝበ እስራኤልን እንደ መስፍን ሲያስተዳድር እንደ ካህን ሲመክርና ሲገስጽ ቆይቷል። በዘመነ ብሉይ ኖሎት የሚባሉት ካህናት ፣ ነገስታትና ነቢያት እንዲሁም መሳፍንት ሲሆኑ አባግዕ የሚባሉት ደግሞ ሕዝቡ ናቸው። 1ኛ ዜና 21፣17 የሙሴን መስፍነነትና ነብይነት እግዚአብሔር በክህነት አገልግሎት ለመደገፍ ሙሴን አንዲህ ብሎ አዘዘው። ‹‹ አንተም ወንድምህም አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ አሮንን የአሮንን ልጆች ናዳብን አብዩድንም አልአዛርንም ኢታምርንም አቅርብ።›› ዘፀ 28፣1-2 ‹‹ በክህነትም ያገለግሉኝ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን ቀባቸው ቀድሳቸው።›› ዘፀ 30፣30

- በዚህም መሰረት የሙሴ ወንድም አሮን በቅብዓ ክህነት ተሹሞ የመጀመሪያው ካህነ አሪት ሆነ።

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

- የብሉይ ኪዳን የክህነት አገልግሎት ለሐዲስ ኪዳን ክህነት አብነት ምልክትና ምሳሌ ነው፡
- በሕገ ልቦና አበው የክህነትን በረከት ከእግዚአብሔር ተቀብለው መስዋዕት የሚያቀርቡበት ዘመን ሲያበቃ ከአስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የሌዊን ነገድ መርጦ በክህነት እንዲያገለግሉ አድርጓል፡፡ ዘጸ 28፣1 ከሌዊ ነገድ የሚመረጡ ካህናት እየተቀቡ ይሾሙ ነበር፡፡ ዘሌ 22፣10
- ዓመታዊ አገልግሎት የሚፈጸመው በሊቀ ካህናቱ ነበር፡፡ ሊቀ ካህናቱ አስቀድሞ የራሱን በኋላም የሕዝቡን ኃጢአት ለማስተስረይ የእህል ቁርባንና የእንስሳት መስዋዕት በዓመት አንድ ቀን በቅድስተ ቅዱሳኑ ያቀርብ ነበር፡፡ ዘሌ 9፣6

3.8.1. የብሉይ ኪዳን የኖላዊነት አገልግሎት

የብሉይ ኪዳን ካህናት አገልግሎታቸው በአራት ዓበይት የአገልግሎት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡

- የቤተ መቅደስ አገልግሎት ዘጉ 16፣40 18፣15- ዕለታዊ አገልግሎት (ጠዋትና ማታ የሚቃጠል መስዋዕት መሰዋት፣በቅድስት መብራት ማብራት፣ ዕጣን ማጠን ፣አማኞች መስዋዕት ሲያመጡ እንደ ዓይነቱ ማቅረብ) ፣ ሳምንታዊ አግልግሎት (12 ገጸ ሕብስት በገበታ ላይ ማስቀመጥ) ፣ ዓመታዊ (ሕዝቡ ኃጢአታቸውን ይናዘዛሉ፣ ደሙ በቅድስተ ቅዱሳኑ ይረጫል፣ በፍየሉ ላይ ካህኑ ጭኖ ይጸልያል ኃጢአትም በፍየሉ ላይ ያልፋል ፍየሉም በምድረ በዳ ይለቀቃል፡፡ዘሌ 16፣23)
- ሕግን ለሕዝብ ማስተማር - 2ኛ ዜና 15፣3 ሕዝ 7፣27
- ማህሌተ እግዚአብሔርን ማድረስ፡ - 1ኛ ዜና 25፣6 1ኛ ዜና 15፣6 1ኛ ዜና 15፣3
- በኡሪምና ቱሚም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ፡ ኡሪምና ቱሚም ሊቀ ካህናቱ በሚለብሰው በኤፉዱ ላይ ባለው የደረት ኪስ ውስጥ የሚቀመጡ ንዋያተ ቅድሳት ናቸው፡፡ ዘጸ 28፣30
- ተላላፊ በሽታ ያለባቸውን መለየት - ዘሌ 13፣1-3

3.8.2. የብሉይ ኪዳን ኖላውያን አይነቶች

የብሉይ ኪዳን ኖላውን በሦስት አይነቶች ይመደባሉ፡፡

ኖሎት ካህናት ዋና ዋናዎቹ

ካህን አሮን ከሌዊ ወገን የተወለደ የእንበረም ልጅ ነው፡፡ በእስራኤላውያን ሐረገ ትውልድ “ምስፍና ወምልክና” “መስፍንነትና ንግስና” ከይሁዳ ዘር የማይወጣ ሲሆን፤ክህነት ደግሞ ከሌው ዘር የሚገኝ ነው፡ ካህን አሮን ከነገደ ሌዊ ሲሆን ለክህነት አገልግሎት የተመረጠ ሊቀ ካህናት ሆኖ የተሾመ የመጀመርያው የብሉይ ኪዳን (የህገ ኦሪት) ካህን ነው ዘጸ 29÷1፡፡

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ልጆቹም ካህናት እንዲሆኑ ተቀድሰዋል ዘሌዋ 8÷9፡፡ አሮን ካህን ሲሞት በእርሱ ፈንታ ሊቀ ካህናትነቱ ለልጁ ለአልአዛር ተሰጥቷል፡፡ በዚህም በዘመነ ብሉያ ሊቀ ካህናት የሚሾመው ከአሮን ዘር ብቻ ነው፡፡ ካህን አሮን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ተገልጿል ወይም ተቆጥሯል ዕብ 5÷4-5፡፡ የካህን አሮን የክህነት አገልግሎት ዓላማ የሰው ልጅ የፈጠረውን ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት፣የሚያመልክበት፣እንዲታዘዝለት፣ለአምላኩ ተገዢ የሚሆንበትን መንገድ ለማስፈጸም ክህነት ስለሚያስፈልግ ከእግዚአብሔር ይህ የክህነት ሥራ ለካህን አሮን ተሰጥተውታል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን መውሰድ እንችላለን፡፡

- የአንበረም ልጅ አሮን -ዘሌ 8፣1
- የአሮን ልጅ አልአዛር - ዘኁ 20፣27
- አፍኒንና ፊንሀስ አባት ካህኑ ኤሊ - 1ኛ ሳሙ 1፣11
- ካህኑ አቤሜሌክ - 1ኛ ሳሙ 21፣2
- ካህኑ አብያታር - 1ኛ ሳሙ 22፣11
- ካህኑ ሳዶቅ - 2ኛ ሳሙ 8፣17
- ካህኑ አዛርያስ - 2ኛ ዜና 26፣17

ኖሎት መሳፍንት ዋና ዋናዎቹ

መስፍን ማለት ገዢ ወይም ዳኛ ማለት ነው፡፡ በእስራኤል ነገሥታታ ማስተዳደር ከመጀመራቸው በፊት ሀገሪቱን ከጠላት ወራሪ የሚያድን፣ የንጉሥ ዘር የሌለው ሰው ነው፡፡ በተለይም ቤተ እሥራኤል ወደ ሀገራቸው ከገቡና ኢያሱ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔርን ትተው የአሕዛብን አማልክት በማምለክ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ እየሠሩ እግዚአብሔርን ያስቆጡት ነበር፡፡ እርሱም ሊመልሳቸው ብሎ ተጸጽተው ወደ እግዚአብሔር ይጮሁ ይጸልዩ ነበር፡፡ እርሱም ይመራቸውና መሳፍንት እያስነሳ ከሚማርኳቸው እጅ ያድናቸው ነበር፡፡ እስራኤልን መሳፍንት ያስተዳድሩበት የነበረው ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ከ1644 እስከ 1083 ዓመት /ከ3856-4417 ዓ.ዓ/ ያለው ጊዜ ዘመነ መሳፍንት ይባላል በመሳፍንት ግን የተዳኙት ለ450 ዘመን ነበር የሐዋ.13-20፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤልን ያስተዳደሩ 17 መሳፍንት ነበሩ፡፡

- ሊቀ ነብያት ሙሴ - ዘጸ 3፣15
- የነዌ ልጅ ኢያሱ - ዘዳ 31፣7
- ነቢዩ ሳሙኤል - 1ኛ ሳሙ 7፣15

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ኖሎት ነገስታት ዋና ዋናዎቹ

- ሳዖል - 1ኛ ሳሙ 12፣1
- ዳዊት - 1ኛ ሳሙ 16፣1
- ሰሎሞን - 1ኛ ነገ 2፣1
- ሕዝቅያስ - 2ኛ ነገ 18፣5
- ኢዮስያስ - 2ኛ ነገ 22፣1

3.9. እረኝነት በሐዲስ ኪዳን

እግዚአብሔር መልካም እረኛ ጠባቂ እንደሆነ በሐዲስ ኪዳን በሰፊው ተብራርቶ ተጠቅሷል። ስለ እግዚአብሔር እረኝነት የሚገልጸው የወንጌል ክፍል ቀድሞ በብልይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱትን መሠረት ያደረገ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ እረኛ ኖላዊ ሆኖ እንደሚመጣ ትንቢት ተነግሯል። በሐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ ክርስቶስ እረኝነት በወንጌልና በመልዕክታት ወስጥ በሰፊው ተገልጿል። በተለይ የዮሐንስ ወንጌለ ምዕራፍ አስር ይህን የሚያብራራ በመሆኑ "አንቀጸ አባግዐ" ተብሎ ተሰይሟል። በዚህ ወንጌል የተዘረዘሩት አብዛኛዎቹ ማለትም እረኛ፣ እውነተኛ እረኛ፣ኃላፊነት የጎደለው እረኛ፣,መንጋ የመሳሰሉት በዚህ የወንጌል ክፍል የተካተቱ ናቸው። የዚህ ወንጌል ክፍል ታሪክም መሠረት አድርገ የሚያብራራው እነዚህ ቀድሞ በብሉይ ኪዳን በተለያየ መልክ የተገለጹትን በመመርመር ነው።፡ የዚህ ወንጌል ክፍል ታሪክ የመልካም እረኛ ማንነትና ተግባር ብቻ ሳይሆን የሚገልጸው ሌባ እና ወንበዴ የተባሉትንም ማንነትና ድርጊት ይገልጻል። የአዲስ ኪዳን ኖሎት የሚባሉት ካህናት ናቸው። የኖላዊነት ምንጩ ከባለቤቱ ከክርስቶስ ነው። ዮሐ 10፣11 ‹‹ መልካም እረኛ እኔ ነኝ።›› እርሱም የእረኞች አለቃ ነው። በመጀመሪያ የአዲስ ኪዳን ኖላዊነት የተሰጠው ለሐዋርያት ነው። ዮሐ 21፣16 የሐዋርያት ሥልጣን በምድርም በሰማይም የሚሠራ ነው። ማቴ 18፣18 የኖላዊነት ሥራ የራቁ የሚቀርቡበት የረከሱ የሚቀደሱበት የከበረ አገልግሎት ነው። ኤፌ 4፣11 — 14 ሐዋርያት ሰባቱን ዲያቆናት በአንብሮተ እድ ሾመዋል። ሐዋ 6፣3 በመንፈስ ቅዱስ ለወለዷቸው ደቀመዛሙርት የኖላዊነት ሥልጣን ሐዋርያት ሰጥተዋል። ሐዋ 14፣23፤ 1ኛ ጢሞ 1፣3፤ 4፣14‹‹ በየከተማውም እኔ አንተን እንዳዘዝኩህ ቀሳውስትን እንድትሾም በቀርጤስ ተውኩህ።›› ቲቶ 1፣5 የአዲስ ኪዳን ኖላዊነት በመጀመሪያ የተፈቀደው ለሐዋርያት ነው "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ትወደኛለህን አዎን ጌታ ሆይ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ" "ግልገሎቼን፣ጠቦቶቼን፣ በጐቼን አሰማራ" (ዮሐ. ፳፩.፲፮) የመጀመሪያው የኖላዊነት መመሪያም ይህ የክርስቶስ ቃል ነው:: የመመሪያው ይዘትም:- ወጣቶችን በሰንበት ት/ቤት እያደራጁ፣ በትምህርት እየመገቡ፣ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እየኮተኮቱ ማሳደግ፣ ሕፃናትን እያጠመቁ፣ ወደ ሥጋ ወደሙ እያቀረቡ ወደ ወጣቶቹ ወንድሞቻቸውና እ□ህቶቻቸው የሚደርሱበትን መንገድ እያመቻቹ ለወላጆቻቸው የሕፃናት አስተዳደግን ትምርህት እየሰጡ መንከባከብ፣ በጎችን /አባቶችንና እናቶችን/ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ፣ ከአምልኮ ባዕድ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር በመመለስ ከግብረ አሕዛብ ወደ

"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::" (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

ግብረ ክርስትና እንዲመለሱ የማድረግ ኃላፊነት የአዲስ ኪዳን ኖሎት ተግባር መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው።

3.9.1. የሊቀ ኖሎት ኢየሱስ ክርስቶስ ኖሎታዊ አገልግሎት

የክርስቶስ የክህነት ሥልጣን ከእገሌ ተቀበለ የማይባልበት የባህርይ ገንዘቡ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚከተለው መልኩ የኖላዊነት (የክህነት) አገልግሎቱን ፈጽሟል። ሐዘባዊ መዓርግ - በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማና ሲጠይቃቸውም ነበር። ሉቃ 2፣41 የአናጉንስጢስነትን (ታዛኝ አከናውኖ የሚያነብ የንባብ ስልት የሚያውቅ) ሥራ ሲሰራ ነበር - የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ነበር። በንፍቀ ዲያቆንነት - የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ ፈጽሟል። ዮሐ 13፣5 በመዓርገ ዲቁና፡ - ህብስተ አኮቴት በማበርከት የዲያቆናትን ተልእኮ ፈጽሟል። ማቴ 14፣19 በመዓርገ ቅስና፡ - ሥጋውና ደሙን በማቀበል - ማቴ 26፣26 መዓርገ ጵጵስና፡ - ሥልጣነ ክህነትን በመስጠት - ዮሐ 20፣22 ሰያሜ ካህናት ሊቀ ኖሎት ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን መዓርጋተ ክህነት በየደረጃው መፈጸሙን እርሱን አብነት በማድረግ የእርሱ ታማኝ ባሪያ ሆነው ለማገልገል የቆረጡ ሰዎች መዓርጋቱን ተራ በተራ ሊቀበሉ እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው።

3.9.2. የሐዲስ ኪዳን እረኝት ዓላማ

- መንጋው እንዳይጠፋ መጠበቅ
- ከጠላት በጎቹን ማዳን የጠላትን ቀንበር መስበር
- መንጋውን የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ ማድረግ ዮሐ 10÷28
- በእግዚአብሔር የተመረጡ ቅዱሳን የእግዚአብሔር ካህናት እንዲሆኑ ማድረግ

በሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ክህነቱ ዘላለማዊ የሆነ ከመልከጼዲቅና ከአሮን የበለጠ ሿሚ ሻሪ የሌለው ዘላለማዊ ካህን ነው። መሥዋዕቱን የሚሰዋ፣መሥዋዕቱ፣ተወካፌ መሥዋዕት እርሱ ነው። እርሱ እውነተኛ እረኛ ነው ።

3.10. የኖላውያን ወቀሳዎች

ኖላውያን የእግዚአብሔር አንደራሴ እንደመሆናቸው መጠን እግዚአብሔር በአራት ነገሮች ይወቅሳቸዋል። እነሱም

- መንጋዎች እየባዘኑ ራሳቸውን ስላለማሩ
- የደከሙትን ባለ ማጽናናታቸው የታመሙትን ባለማከማቸው
- የተፋውን ባለ መፈለጋቸው
- የመንጋውን ምግብ በማደፍረሳቸው

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብጉት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)

3.11. የኖላውያን ዋጋ

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4) ተብሎ እንደተጻፈ የክብር አክሊል ይጠብቀናል።

3.12. ማጠቃለያ

ኖላዊነት እግዚአብሔር ሲመርጥ የሚያገኙት እንጂ በራስ ጥረት የሚመጣ አይደለም። ኖላዊነት ባላደራነት ነው። አደራን አለመጠበቅ ከአደራ ሰጪው የሚያስጠይቅ በመሆኑ ጠንክረን ልንሠራ ያስፈልጋል። አባቶቻችን በተጋድሏቸው ለእኛ ያስተላለፉልንን ሃይማኖት ጠብቀን ለልጆቻችን ማስተላለፍ ታሪካዊም መንፈሳዊም ዐደራ አለብን። ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔርን ታላቅ አደራ የተቀበሉና ቤተክርስቲያንን የሚያስተዳድሩና የሚጠብቁ ካህናት እጥፍ ድርብ ኀላፊነት እንዳለባቸው ተረድተው ጊዚያዊውንና ምድራዊውን ነገር ሳይሆን ዘላለማዊውንና ሰማያዊውን ነገር ሊያሳስባቸውና ከትንናቱ የበለጠ በእግዚአብሔርም በምዕመናንም ዘንድ ታማኝ ባላደራነታቸውን ሊያሳዩ ይገባል።

3.13. ዋቢ መጻሕፍት

- አባ ሀብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፤ትምህርተ አበ ነፍስ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1953 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (ፕሮፌሰር)፤የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1974 ዓ.ም.
- አባ አበራ (ሊቀ ጉባኤ)ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ህይወት አዲስ አበባ ፤ማህበረ ቅዱሳን 2008 ዓ.ም
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) የኢትዮጵ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲን ታሪክ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1974 ዓ.ም.
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሃይማኖተ አበው፣አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1986 ዓ.ም.
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም.
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ስርዓተ አምልኮ እና የውጭ ግንኙት፣ አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም.
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ያሬድ ድጓ ፣አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1997 ዓ.ም.
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው ፣አዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም.

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፍትሐ ነገሥት ፣አዲስ አበባ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1992ዓ.ም.
- ክንፈ ገብረኤል አልታየ (ሊቀ ካህናት) ሥራዓተ ቤተክርስቲያን አዲስ አበባ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት
- አባ ሺኖዳ (ፓትርያርክ) ቅስና
- አባ ሺኖዳ (ፓትርያርክ) መንፈሳዊ ውጊያዎች
- አባ ሺኖዳ (ፓትርያርክ) የዲያቢሎስ ውጊያዎች
- አባ ሺኖዳ (ፓትርያርክ) ጉዞ ወደ እግዚአብሔር
- የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የትምህርተ ኖሎት ማስተማሪያ ያልታተመ
- የሐዋሳ ደብረ ታቦር መንፈሳዊ ኮሌጅ የትምህርተ ኖሎት ማስተማሪያ ያልታተመ
- የዝዋይ ሐመረ ኖሕ መንፈሳዊ ኮሌጅ የትምህርተ ኖሎት ማስተማሪያ ያልታተመ
- የመቀሌ ክሳቱ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ የትምህርተ ኖሎት ማስተማሪያ ያልታተመ
- የቅድስት ሥላሴ ዩንቨርሲቲ የትምህርተ ኖሎት ማስተማሪያ ያልታተመ

በሰ.ቅ.ጳ.መ.ኮ.የት.ኖሎት መማሪያ በመ.ር ጌታባለው (B.Th. MA Adm)

“በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጉብዥት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን ክብርና አክሊል ትቀበላላችሁ::” (1ኛ ጴጥ 5፣2-4)